አደራ መብላት...
ገጽ 11

የምስጋና ኃይል
ገጽ 14

የከተማዋን የካዳስተር ምዝገባ ሥርዓት ወደ ሙሉ ትግበራ የሚያሸጋግረው የመጨረሻው ምዝገባ
ገጽ 18




አዲስ ዘመን
ኢፕድ
84ኛ ዓመት ቁጥር 109 ታኅሣሥ 19 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ: ዳኜ አበራ

# “መቄዶንያ ብዙዎችን ተስፋ ከመቁረጥ አውጥቶ ሕይወት የዘራ ማዕከል ነው”

- ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ

**ነጻነት አስሙ**

አዲስ አበባ፡- መቄዶንያ ብዙዎችን ተስፋ ከመቁረጥ አውጥቶ ሕይወት የዘራ ማዕከል ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ።ፕሬዚዳንቱ የመቄዶንያ የበላይ ጠባቂነትን ጥያቄ ተቀብለዋል።

ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ የመቄዶንያ አረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከልን ትናንት በጎበኙበት ወቅት እንደገለጹት፤ መቄዶንያ ብዙዎችን ተስፋ ከመቁረጥ አውጥቶ ሕይወት የዘራ ማዕከል ነው።የልመናና የጉስቁልና ማርከሻው ለሀገር በርትቶ መሥራት በመሆኑ በትብብር መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

የሕይወትና የመኖር ትርጉም የሚገለጸው ለሌሎች ሰዎች በጎ

“መቄዶንያ ብዙዎችን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ‹‹ኢትዮጵያውያን የግብፅን ሴራ ለማክሸፍ ሁሌም ዝግጁ መሆን አለባቸው››

- ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ

ገጽ 3



## የካፒታል ገበያ ሥርዓት ለስታርትአፕ ንግዶች አዲሱ በረከት

**ዳግም ከበደ**

**ዜና ሐተታ**

የካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ ተደግፎ ወደ ተግባር ለመግባት ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ይገኛል። በመጪው ጥር 2017ዓ.ም በይፋ ሥራውን እንደሚጀምር ተገልጿል።በጅምር ላይ ያሉ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራ ንግዶች ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያሳድጉ ጉልህ

የካፒታል ገበያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከግጭት አዙሪት ወደ ዘላቂ ሰላም

**ማርቆስ በላይ**

**ዜና ሐተታ**

በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና የሰላም መንገድን በመረጡ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አመራሮች መካከል የሰላም ስምምነት መደረጉ ይታወሳል።በዚህ መሠረትም በተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ የሠራዊቱ አባላት ወደ ተዘጋጁላቸው ማዕከላት እየገቡ ይገኛል።ታዲያ በክልሉ ከግጭት አዙሪት ወደ ዘላቂ ሰላም ግንባታ መምጣት የሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ 40ኛው የጉሚ በለል የውይይት መድረክ ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ክልሉን ከግጭት አዙሪት ለማውጣትና የጥይት ድምጽ የማይሰማበት ለማድረግ ወሳኝ መሆኑን ይገልጻሉ።

በኦሮሚያ ምድር ላይ የጥይት ድምጽ እንዳይሰማ፣ የክልሉ ሕዝብ ሰላም ለሁሉም እንደሚያስፈልግ ጥሪ ሲያቀርብ መቆየቱን አውስተው፤ የአመለካከት ልዩነቶችን



በቀደምት እውቀቶችና በምክክር መፍታት እንደሚቻል ያስረዳሉ።

በግጭቶች ሳቢያ በርካቶች ተፈናቅለዋልና ሀብት ንብረታቸው መውደሙን ይናገራሉ።በዚህ ምክንያትም ጦርነት አከሳሪ እንጂ አማራጭ መሆን እንደማይችል መረዳት ተችሏል ይላሉ።የኦሮሞ ሕዝብ ጦርነት ይበቃናል ታረቁ በማለት ማረሻና ቀንበር በመያዝ

ከግጭት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ዘንድሮ ከበጋ መስኖ ስንዴ 173 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ ምርት ይጠበቃል

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 172 ሚሊዮን 951 ሺህ 738 ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። እቅዶችን ለማሳካት በየደረጃው ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ከአርሶ አደሩ ጎን ሆነው አስፈላጊውን እገዛ እያደረጉ መሆኑን ገለጸ።

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በ2017 ዓ.ም አራት ሚሊዮን 277 ሺህ 230 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት እየተሠራ ነው። ከዚህም 172 ሚሊዮን 951 ሺህ 738 ኩንታል ምርት ይጠበቃል ብለዋል።

የመስኖ ስንዴ ልማት በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፤ ደቡብ-ኢትዮጵያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ፣ ትግራይ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ላይ አራት ሚሊዮን 277 ሺህ 230 ሄክታር መሬት ለማረስ መታቀዱን አመልክተዋል።

እስካሁን ድረስ በባህላዊ ሁለት ሚሊዮን 649 ሺህ 184 ሄክታር፣ በትራክተር 365 ሺህ 65 ሄክታር መሬት በድምሩ ሦስት ሚሊዮን 14 ሺህ 249 ሄክታር መሬት ታርሷል። ከዚህ ውስጥም ሁለት ሚሊዮን 390 ሺህ 88 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል ብለዋል።

የክልሎችን ድርሻ ስንመለከት ኦሮሚያ ክልል አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት 163 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ማቀዱን አስታውሰው፤ ከዚህ ውስጥ ሁለት ሚሊዮን 819 ሺህ 539 ሄክታር መሬት ታርሷል። ሁለት ሚሊዮን 202ሺህ 674 ሄክታር መሬቱ በዘር መሸፈን መቻሉን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ የአማራ ክልል 230 ሺህ 100 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት 8 ሚሊዮን 535 ሺህ 800 ኩንታል ምርት ለማግኘት ማቀዱን ገልጸው፤ እስካሁን ድረስ 183 ሺህ 981 መሬት ታርሶ፣ 115 ሺህ 40 ሄክታሩ በዘር መሸፈኑን አስታውቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ አፋር 23 ሺህ 500 ሄክታር፣ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ስድስት ሺህ 04 ሄክታር፣ ሶማሌ ክልል አምስት ሺህ 100፣ ደቡብ ኢትዮጵያ አምስት ሺህ ሄክታር እንዲሁም ማእከላዊ ኢትዮጵያ ሦስት ሺህ 116 ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ይለማል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ በትግራይ ሁለት ሺህ ሄክታር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አንድ ሺህ 60 ሄክታር መሬት፣ ጋምቤላ ክልል አንድ ሺህ እና ሲዳማ ክልል 350 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ እንደሚለማ አመላክተዋል።

እንደ ሀገር የተቀመጡ እቅዶችን ለማሳካት በየደረጃው ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ከአርሶ አደሩ ጎን ሆነው አስፈላጊውን እገዛ እያደረጉ መሆኑንም መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጨምረው ገልጸዋል።




# የጀርሞች መድኃኒቶችን መላመድ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት በእጅጉ እንደሚቀንስ ተጠቆመ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የጀርሞች መድኃኒቶችን መላመድ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በእጅጉ እንደሚቀንስ የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አስታወቀ።

ኅብረተሰቡ ያለ ህክምና ባለሙያ ትዕዛዝ መድኃኒቶችን እንዳይጠቀም በስፋት ሊሠራ እንደሚገባም አመልክቷል።

በባለሥልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባና ፍቃድ ባለሙያ ዶክተር ኃይሉ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ መድኃኒትን ያለ ባለሙያ ትእዛዝ መጠቀም የጀርሞች መድኃኒቶችን መላመድ ይፈጥራል፤ ይህም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በእጅጉ ይቀንሳል።

መድኃኒቶችን ለምን ያህል ጊዜ ለምን አይነት በሽታ መወሰድ አለበት የሚለውን መወሰን ያለበት በባለሙያ ነው ያሉት ዶክተር ኃይሉ፤ በዘፈቀደ መድኃኒቶችን መጠቀም ፤በሽታ አምጪ ጀርሞች መድኃኒቶች እንዲላመዱ እድል ይሰጣቸዋል ብለዋል።

የበሽታ ተህዋሲያን ራሳቸውን ለማኖር ባላቸው ተፈጥሯዊ የመቋቋሚያ መንገዶች ምክንያት በሚከሰት የጀርሞች መድኃኒቶችን መላመድ፤በዓለም አቀፍ ደረጃ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት በእጅጉ ሊቀንስ እንደሚችል አመልክተዋል።

በአሁኑ ሰዓት ያለው የጀርሞች መድኃኒቶችን መላመድ በዚህ ፍጥነት ከቀጠለ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የእንስሳት ምርትና ምርታማነት በ11 በመቶ እንደሚቀንስ ጥናቶች መጠቆማቸውንም ዶክተር ኃይሉ ገልጸዋል።

የመድኃኒቶች በጀርሞች የመላመድ ችግርን ለመቅረፍ በችግሩ ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ያመለከቱት ዶክተር ኃይሉ፤ ኅብረተሰቡ ያለ ህክምና ባለሙያ ትዕዛዝ መድኃኒቶችን እንዳይወስድ በስፋት ሊሰራ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

መድኃኒቶችን በአግባቡ መጠቀም ሌላኛው ችግሩን መከላከያ መንገድ መሆኑንም አስታውቀው፤ በሽታን አስቀድሞ መከላከልም የመድኃኒትን መላመድ ለመቀነስ ሌላኛው አማራጭ እንደሆነ አመልክተዋል።



# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሌማት ትሩፋት ከ210 ሚሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት ተገኘ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት በሌማት ትሩፋት ከ210 ሚሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት መገኘቱን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ እና የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያና የመኖ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አባይነህ ከዳ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በሌማት ትሩፋት በአምስት ወራት ከ232 ሚሊዮን 857 ሺህ ሊትር በላይ የወተት ምርት ለማግኘት ታቅዶ ከ210 ሚሊዮን ሊትር በላይ ተገኝቷል። ይህም የእቅዱ 89 በመቶ ነው።

በክልሉ የወተት ምርት መጠን ለመጨመር የተሠራው ሥራ ውጤታማ መሆኑን አመልክተው፤ ይህም ከተሞች ይታይ የነበረውን የወተት ዋጋ ንረትን ማረጋጋት መቻሉን ነው የገለጹት።

እንስሳትን በማድለብ ረገድም 526 ሺህ 277 የዳልጋ ከብት፣ 359 ሺህ 663 በግ እና ከ362 ሺህ በላይ ፍየል ማሞከት ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ በዚህም 143 ሺህ 13 ወንድና ሴት አርብቶ አደሮች መሳተፋቸውን ኃላፊው ገልጸዋል።

አባይነህ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ የዶሮ እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል በተሰራው ሥራ 147 ሚሊዮን 260 ሺህ የእንቁላል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ በቁጥር 128 ሚሊዮን 100 ሺህ እንቁላል እንቁላል መሰብሰብ ተችሏል። ይህም የእቅዱ 87 በመቶ ነው።

የዶሮ ስጋ ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል በተሠራው ሥራም 2 ሺህ 867 ቶን የዶሮ ስጋ ምርት ለማምረት ታቅዶ 2 ሺህ 351 ቶን ተመርቷል።

በአጠቃላይ በዶሮ ሀብት ልማት 221 ሺህ 735 ወንድና ሴት አርብቶ እና አርሶ አደሮች ተሳትፈዋል ሲሉ አስረድተዋል።

የማር ምርትን በተመለከተ 3 ሺህ 240 ቶን የማር ምርት ለማግኘት ታቅዶ፤ 2 ሺህ 521 ቶን ማር ተገኝቷል። ይህም የእቅዱ 78 በመቶ መሆኑን አስረድተዋል።

ከተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ የውሃ አካላት እስከ ጥቅምት ወር 8 ሺህ 370 ቶን ዓሳ ምርት ለማምረት ታቅዶ 7 ሺህ 700 ቶን ማምረት ተችሏል። በዘርፉ በተሠራው የኤክስቴንሽን ድጋፍና ክትትል 3 ሺህ 241 የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል።

በክልሉ በሌማት ትሩፋት እየተሠራባቸው በሚገኙ የምርት አይነቶች ከ2015 እስከ 2018፤ 10 ሺህ 743 መንደሮችን ለማደራጀት የታቀደ ሲሆን፤ 8 ሺህ 296 መንደሮች ለማደራጀት ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

የእንስሳት መኖ ዋጋ ከሚጠበቀው በላይ መጨመር ተግዳሮት መሆኑን የተናገሩት ኃላፊው፤ ችግሩን ለመቅረፍ ተጨማሪ የመኖ ማቀነባበሪያ ለማቋቋም ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም አርቢው ኅብረተሰብ ግብዓት ሳይቸገር የሚያገኝበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እና የንብ ቀፎዎችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ፤ የተደራጁ ሥራ ፈጣሪዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ቀፎ እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያውያን የግብፅን ሴራ ለማክሸፍ ሁሌም ዝግጁ መሆን አለባቸው››

- ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን በግብፅ ሴራ በብዙ መልኩ መጎዳታቸውን በማስታወስ፤ ለግብፅ ሴራ ነቅተው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ አስታወቁ።

ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ላይ እንዳስታወቁት፤ ግብፆች በየመን፣ ሊቢያ፣ ሰሞኑን በምሥራቅ አፍሪካ በተለየ ሁኔታ በሶማሊያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ችግር እየፈጠሩ ነው።

የግብፅ ዲፕሎማቶችም ሆኑ ሌሎች ከግብፅ የሚመጡ ምሁራን እና አጠቃላይ ሠራተኞች ስለ ውሃው መመሪያ ተሰጥቷቸው የሚመጡ ናቸው ያሉት ፕሮፌሰር አሕመድ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከውሃ ጋር ተያይዞ የሚከወን እያንዳንዱን ድርጊት በተለያየ መንገድ ይከታተላሉ።ኢትዮጵያን ለማደናቀፍ በብዙ መልኩ ይጥራሉ ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን የግብፆችን የተለመደውን የማዋከብ እንቅስቃሴ ስፍራ ባለመስጠት፤ መሥራት ያለባቸውን በደንብ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን የቤት ሥራ መሥራት ከቻሉ በሕዳሴው ግድብ ላይ እንደታየው ግብፆች የትም ቢሮጡ ምንም ማምጣት እንደማይችሉ አመልክተዋል፡፡



እንደ አሕመድ(ፕ/ሮ) ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ካደገች ግብፅ ድሃ ትሆናለች የሚል የመንፈስ ጭንቀት አለባቸው።በዚህ ምክንያት ከኢትዮጵያ የቀረበውን አብረን እንደግ የሚለውን አስተሳሰብ ከመቀበል ይልቅ፤ እናንተ ድሃ ሆናችሁ እኛ ብቻ እንብላ፤ ‹‹እኔ በበላሁት አንተ ተፈወስ›› ከሚል በሽታ መውጣት ስለተሳናቸው አሁንም ሴራ በተሞላበት መልኩ እየተንቀሳቀሱ ነው።

ከናይል ጋር ተያይዞ በሚሠሩ ሥራዎች ዙሪያ፤ የቴክኒክ ድጋፍ በሚል ስም ውሃውን ለመቆጣጠር እንደሚሞክሩ እና ኢትዮጵያ ውስጥም ይህንን ለማድረግ መጣራቸውን ጠቁመው፤ እያንዳንዷን ኢትዮጵያ ውስጥ የዘነበውን የዝናብ ጠብታ የመቆጣጠር ፍላጎት እንዳላቸው አስታውቀዋል።

ይህንን ፍላጎታቸውን በእሳት ላይ ቤንዚል እያርከፈከፉ ኢትዮጵያን በብዙ መልኩ ሲጎዷት መቆየታቸውን አብራርተዋል።አሁንም እየጎዷት እንደሚገኙ ጠቁመዋል።ይህንን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ሊረዳው እንደሚገባ አሳስበዋል።

ግብፅ የኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛ ውሃ ከኤርትራ ጀምሮ ትግራይን ይዞ እስከ ጋምቤላ እንዲሁም የኦሮሚያን እና የአማራ ክልልን በአጠቃላይ የሚያካትት ሰፊ ተፋሰስ ወደ ሀገሯ እንደሚገባላት አስታውሰው፤ የኢትዮጵያ አፈር ተራቁቶ እየተከላ ለምርት አስቸጋሪ የሆነው ወደ ዓባይ በሚገቡ ወንዞች ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል።

ግብፅ ከኢትዮጵያ የተሻለ የውሃ ክምችት እንዳላት ሊዘነጋ አይገባም የሚሉት አህመድ (ፕ/ሮ)፤ የሜዲትራኒያንን ሆነ የቀይ ባሕርን ውሃ በቴክኖሎጂው መጠቀም እንደምትችል አመልክተዋል።

እንደ እስከ አሁኑ 130 ሚሊዮን ሕዝብ ያላትን ሀገር ውሃውን አትንኩ ቢሉም፤ ኢትዮጵያ መንካቷ እንደማይቀር ተናግረዋል። የሚሻለው ተባብሮ በሥነሥርዓት የፈጣሪን ስጦታ መቀበል እና መጠቀም ብቻ ነው ብለዋል።



ወይዘሮ አስቴር ሰለሞን

# የመሪዎች ጉባኤ እንግዶችን ለመቀበል ሆቴሎች ዝግጅት እያደረጉ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- 38ኛውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ለመሳተፍ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ሆቴሎች በበቂ ሁኔታ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን የአዲስ አበባ ሆቴል ባለንብረቶች ማህበር አስታወቀ ።

የማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢና ፕሬዚዳንት ወይዘሮ አስቴር ሰለሞን በተለይ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ለአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ስብሰባ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል በሆቴሎች በኩል በቂ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በርካታ እንግዶች ወደ ሀገር ቤት ሲመጡ በቀዳሚነት ተጠቃሚ ከሚያደርጓቸው መካከል ሆቴሎች ይጠቀሳሉ ያሉት ወይዘሮ አስቴር፤ የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ በከተማዋ ለሚገኙ ሆቴሎች በዓመቱ ትልቅ ሥራ የሚሰሩበት እና ከፍተኛ ገቢ የሚያገቡበት እንደሆነ አመልክተዋል።

ከዚህ ቀደም የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባዎችም ሆኑ ሌሎች ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች ሲካሄዱ የተለየ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከሌላው ጊዜ በተለየ በመንግሥት በኩል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራበት ይገኛል ብለዋል።

በቅርቡም ከንቲባ አዳነች አቤቤና የቱሪዝም ሚኒስትሯ በተገኙበት ከባለ ኮኮብ ሆቴሎች ጋር ዝግጅቱን በተመለከተ፤ ከዚህም በኋላ የጸጥታ አካላትን ጨምሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሠሩ በሚገባቸው ሥራዎች ዙሪያ ውይይቶች መደረጋቸውን ጠቁመዋል።

የመብራትና የውሃ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶች ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች በጋራ የሚከናወኑ ስለመሆናቸውም ገልጸዋል።

አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ እየሆነች መምጣቷ ለሆቴሎችም ሆነ ለእንግዶች መልካም እድል ይዞ መምጣቱን ያመለከቱት ፕሬዚዳንቷ፤ ከዚህ ቀደም የመጡ እንግዶች አሁን ቢመጡ ከአየር ማረፊያ ጀምሮ የሚያዩት አዲስ ፣ የተለወጠ እና ያማረ ነገር ነው ብለዋል።

በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎችም በከተማዋ ለምተዋል፤ ይህ ደግሞ የእንግዶቹን የቆይታም ሆነ የመንቀሳቀስ እድላቸውን በማስፋት ሆቴሎች እና ሌሎችንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። ይህም በራሱ እንግዶቹ በተሻለ ሁኔታ እንዲስተናገዱ፤ ስለከተማዋ ጥሩ መረጃ እና የተሻለ ምስክርነት ይዘው ሌሎችን እንዲጋብዙ እድል እንደሚፈጥር አስታውቀዋል።

በተወሰነ ደረጃ በአንዳንድ ሆቴሎች የተጋነነ ክፍያ ስለሚታይ በሆቴሎችና በመንግሥት በኩል ምክክር በማድረግ የሚስተካከልበት ሁኔታ እንዲፈጠር የሚሠራ መሆኑንም ፕሬዚዳንቷ ጠቁመዋል።



# የሰሜን ወሎ ዞን የጸጥታ ሁኔታ መሻሻሉ ለተረጂዎች ድጋፍ ለማድረስ እንዳስቻለ ተገለጸ

## - ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ድጋፎችን ራሱ ለመሸፈን ወደ እርሻ ሥራዎች ገባ

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- የሰሜን ወሎ ዞን የጸጥታ ሁኔታ መሻሻል ማሳየቱ ለቡግና ወረዳ እና ለአካባቢው ተረጂዎች የአልሚ ምግብ፣ የጤና አገልግሎት እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስን ተደራሽ ለማድረግ እያስቻለ መሆኑን የአማራ ክልል የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ገለጸ።ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለውም ኮሚሽኑ ወደ እርሻ ሥራዎች መግባቱን አስታውቋል።

በአማራ ክልል የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይዘሮ ፍቅሬ ሙሉጌታ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ የሰሜን ወሎ ዞን የጸጥታ ሁኔታ መሻሻል ማሳየቱ በቡግና ወረዳና አካባቢው የአልሚ ምግብ እጥረት አጋጥሟቸው በችግር ውስጥ ለነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ አስችሏል።

ቡግና ወረዳ በሰቆጣ ዲክላሬሽን ስር ታቅፈው የአልሚ ምግብ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ወረዳዎች አንዱ መሆኑን የተናገሩት ወይዘሮ ፍቅሬ፤ በጸጥታ ችግር ምክንያት ለእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች አልሚ ምግቦችን ማድረስ ባለመቻሉ በችግር ውስጥ እያሳለፉ እንደነበር አውስተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው አንጻራዊነት የጸጥታው ሁኔታ መሻሻል በማሳየቱ በቡግና ወረዳ 110 ሺህ ለሚሆኑ ተረጂዎች በፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር በኩል 414 ነጥብ 6 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 4ሺህ 446 ኩንታል ስንዴ ማጓጓዝ እንደተቻለ ጠቅሰዋል።ቀደም ሲልም የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል የእርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮው የምርት ዘመን የሰሜን ወሎ ዞን ምርታማነቱ የተሻለ ነው ያሉት ወይዘሮ ፍቅሬ፤ ይሁንና በ2015/16 የምርት ዘመን በአካባቢው አጋጥሞ የነበረው ድርቅ የዘንድሮው ምርት እስኪሰበሰብ ድረስ ተጽዕኖ አሳድሯል ብለዋል።በዚህም ምክንያት ከአልሚ የምግብ እጥረት በተጨማሪ አስቸኳይ የምግብ ርዳታ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች እንዳሉ ጠቅሰዋል።

እንደ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዋ ገለጻ፤ የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ የተለያዩ መርሃ-ግብሮችን ቀርጾ እየሠራ ነው፤ ከዚህም አንዱ ኮሚሽኑ ለተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት እንዲያስችለው እራሱ በእርሻ ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ወደ ማምረት የገባ መሆኑ ነው።በክልሉ ያለው የጸጥታ ሁኔታ ተግዳሮት ቢሆንም በተወሰኑ ቦታዎች ላይ በሰራው ስራ ማምረት መጀመሩን ወይዘሮ ፍቅሬ ተናግረዋል።

በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም ‹‹ከተረጂነት ወደ ማምረት›› በሚል መሪ ሃሳብ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የመስጠት ስራ መሰጠቱን አስረድተዋል።ከወረዳ እስከ ዞን፣ ከሴፍቲኔት ተረጂዎችና ተፈናቃዮች እስከ አመራር ድረስ ለ3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሰዎች ሃሳብን የማስረጽ ስራ ተሰርቷል ነው ያሉት።

ዜና



# በአዳማ ከተማ በበጋ መስኖ ስንዴ ሰላሳ ሺህ ሄክታር እየለማ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በአዳማ ከተማ በበጋ መስኖ ስንዴ ሰላሳ ሺህ ሄክታር ለማልማት እየተሰራ ሲሆን፤ እስካሁን ሃያ ሶስት ሺህ ሄክታሩን በዘር ለመሸፈን መቻሉን የከተማው ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ አለሙ ቂልጦ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ ከተማዋ በመስኖ ሊለሙ የሚችሉ ሰፋፊ መሬቶችን ከምሥራቅ ሸዋ ዞን ተቀብላ በማስተዳደር ላይ ትገኛለች።

ከዚህም ውስጥ በተጀመረው በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሰላሳ ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤ እስካሁን ሃያ ሶስት ሺህ ሄክታሩ በዘር መሸፈኑን አስታውቀዋል።

በአዳማ ከተማ የከተማ ግብርና ለማከናወን ከፍተኛ አቅም ያለ ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር ያሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ወቅት ግን በመንግሥት በኩል በየደረጃው ከፍተኛ ትኩረት በመሰጠቱ አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በከተማዋ ሃያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሄክታር ሊለማ የሚችል መሬት መኖሩን ያመለከቱት ኃላፊው፤ ባለፈው ዓመት መሬቱን ሙሉ በሙሉ በሰብል በመሸፈን ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ እህል ለመሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል።

ዘንድሮም በፍራፍሬ ልማት ረገድ ስልሳ ሦስት ሄክታር ሙዝ፣ አርባ ስምንት ሄክታር ፓፓዬ፣ አስራ ስድስት ሄክታር ብርቱካን፣ አስራ ሁለት ሄክታር ዘይቱን፣ ስድስት ሄክታር አቡካዶ በክላስተር እየለማ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

ሁለት ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎችን በማዘጋጀትና ሥር አጥ ወጣቶችን በማደራጀት ከተማዋን በከበበው ተራራ ላይ የንብ ማነብ ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝ፤ በዶሮ እርባታ ረገድም በመንግሥትና በህብረት ስራ ማህበራት አምስት መቶ አርባ አራት የዶሮ ማርቢያ በማዘጋጀት ለአምራቾች መከፋፈሉን አስታውቀዋል ።

በዚህም ባለፈው ዓመት አስራ ሶስትና አስራ አራት ብር ይሸጥ የነበረውን አንድ እንቁላል ዘጠኝ ብር ማድረስ ተችሏል። በአሳማና በአሳ እርባታም ረገድ የተጀመሩት ስራዎች አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ ይገኛሉ ብለዋል።

የከተማ ግብርና በየወቅቱ ቁጥሩ የሚጨምረውን የከተማ ነዋሪ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና ከፍተኛ ቁጥር ላለው የሰው ኃይል የስራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል ነው። ባለፈው አመት የተፈጠረው የስራ እድል ሃያ ሶስት ሺህ ብቻ ነበር። ዘንድሮ ግን በከተማ ግብርና ብቻ ለሰላሳ አምስት ሺህ ሰው የስራ እድል ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ እስካሁን ለአስራ ስድስት ሺህ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር መቻሉን አመልክተዋል።

ይህም ሆኖ በከተማዋ ካለው ምቹ ሁኔታና አምራች የሰው ኃይል አኳያ በርካታ ስራዎች የሚቀሩ በመሆኑ ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ የሚሰሩ ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆኑን ጠቁመዋል።

# የካፒታል ገበያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ድርሻ እንደሚኖረውም ይጠበቃል። የዝግጅት ክፍላችን ‹‹ለችግር ፈቺ ቴክኖሎጂ ነክ ፈጠራ ንግዶች የፈንድ አማራጭ ከማስፋት አኳያ ምን ድርሻ ይኖረዋል›› ሲል ባለሙያዎችን አነጋግሯል።

በጅምር ላይ ያሉ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራ ንግዶች የተለያዩ የፈንድና የመዋዕለ ንዋይ ማሰባሰብ ደረጃዎችን ያልፋሉ የሚሉት የኢንቬሽንና ስታርትአፕ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሰላምይሁን አደፍርስ፤ ከመንግሥት አሊያም ከተለያዩ ድርጅቶች የሚደረግ ነፃ ድጋፍ አንደኛው የፈንድ አማራጭ ሲሆን በዚህኛው ደረጃ የፈጠራ ሃሳቦቹን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚደረግ ትርፍ የማይጠበቅበት ሂደት መሆኑን ያስረዳሉ።

በሁለተኛነት የፈጠራ ሥራ ንግዶች (startups) ፍሬያማ የሚሆኑበት የኢንቨስትመንት ደረጃ መሆኑን ያነሳሉ። የካፒታል ገበያ ሚና ከፍተኛ የሚሆነው እዚህ ጋር መሆኑን ይገልፃሉ። የቴክኖሎጂና አዳዲስ የንግድ ሥራ ፈጠራ ንግዶች ውጤታማ ሲሆኑ ንግዳቸውን ለማስፋፋት በካፒታል ገበያ አማካኝነት ለማህበረሰቡ፣ ለኢንቨስተሮችና ልዩ ልዩ ኩባንያዎች የድርጅቶቻቸውን ድርሻ የማከፋፈል መብት ይኖራቸዋል ነው ያሉት።

አቶ ሰላምይሁን፤ ይህም ንግዳቸውን ለማሳደግ የሚያስችል መዋዕለ ንዋይ ያለ ችግር እንዲያገኙ እድል እንደሚሰጣቸው ይገልጻሉ። ከዚህ ቀደም በኢንቨስተሮች እና በፈንድ እጦት በአጭሩ የሚቀጩና የሚጠፉ የፈጠራ ሃሳቦችና ጅምር ንግዶች በዚህ የካፒታል ገበያ ሥርዓት ውስጥ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ያስረዳሉ።

‹‹በጅምር ላይ ያሉ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራ ንግዶች ትርፋማነትና አቅም የሚለካው ለወደፊት ይኖራቸዋል ተብሎ በሚቀመጥ ግምታዊ ስሌት ነው›› የሚሉት አቶ ሰላምይሁን፤ ይህንን ግምታዊ ስሌት የሚቆጣጠር አካል (security exchange body) እንደሚኖር ይገልጻሉ።

የካፒታል ገበያ ሥርዓት መዘርጋቱ ከዚህ ቀደም ችግር ፈቺ የፈጠራ ሃሳቦች በገበያው ላይ ይገጥማቸው የነበረውን የገንዘብ ችግር በዘላቂነት የሚቀርፍና አዳዲስ ንግዶች እንዲያድጉ የሚያበረታታ መሆኑን ያነሳሉ። ንግዶቹን ለማስፋፋት ከባንኮች ብድር ማግኘት ውስብስብ ሂደት የሚጠይቅ መሆኑ በካፒታል ገበያ ሥርዓቱ ተጠቃሚ መሆናቸው ተመራጭ መሆኑንም ያነሳሉ።

አቶ ዳንኤል በቀለ የአሸዋ ቴክኖሎጂ አክሲዮን ማህበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። የካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመር በጅምር ላይ የሚገኙ ችግር ፈቺ የንግድ ፈጠራ የፋይናንስ አቅም በማጎልበት ወደ ፍሬያማነት እንዲቀየሩ ትልቅ እድል ይዞ መምጣቱን ይናገራሉ።

የስታርትአፖቹ ማደግ ለኢንቨስተሮችም ሆነ ለሀገር ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ገልጸው፤ ለዚህ የካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ውስጥ መተዋወቅ ቅድሚያ ተጠቃሚ ከሚያደርጋቸው ውስጥ ቀዳሚ እንደሆኑ ያስረዳሉ።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሃሳብ፤ የስታርትአፖች ትልቁ ማነቆ አቅማቸውን የሚያጎለብቱበት የፋይናንስ ድጋፍ እጦት ነው። የካፒታል ገበያ ሥርዓት መጀመሩ ይህንን ማነቆ በመፍታት ከማህበረሰቡ በቦንድና በአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ በማከናወን ወደ ቀጣዩ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያግዛል።

‹‹አብዛኛዎቹ በአዳዲስ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂ ነክ የሥራ ፈጠራ ላይ የተሰማሩት ወጣቶች ናቸው›› የሚሉት የአሸዋ ቴክኖሎጂ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፤ እነዚህ ፈጣሪዎች ከእውቀት በዘለለ የመሰረቱትን ስታርትአፕ ወደ ከፍተኛ እድገት ለማሸጋገር የፋይናንስ አቅም እንደሌላቸው ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት ስታርትአፖች ወደ ትላልቅ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የንግድ ድርጅትነት እንዳይሸጋገሩ የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ዋናው ማነቆ መሆኑን ያስረዳሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ የሥራ ፈጠራ ሃሳብ የያዙ ስታርትአፖች እየተፈጠሩ ነው። በመሆኑም ከምንጊዜውም በተለየ የፋይናንስ አማራጭ መፈለግ የግድ ይላል። ለዚህም የካፒታል ገበያ ሥርዓት መጀመሩ እንደ አንድ መፍትሔ ሊወሰድ ይችላል ይላሉ።

የካፒታል የገበያ ሥርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ በይፋ ሥራ ሲጀምር ስታርትአፖች የፋይናንስ ማነቋቸውን የሚፈቱበትን አማራጭ እንደሚፈጥር ተረድተው በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚኖርባቸው ሁለቱም የዘርፉ ባለሙያዎች ምክረ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የስታርትአፕ ፈንድ ማሕቀፍ ማዘጋጀቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

# ከግጭት አዙሪት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ይቅርታን ለምኗል ያሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ጊዜ የኦሮሚያ ክልልን ከግጭት ወደ ዘላቂ ሰላም ለማሸጋገር እየተሠራ መሆኑን ይናገራሉ።

ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ጠንካራ ቁርጠኝነት፣ከግልና ከቡድን ፍላጎት ወደ ሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄ መሸጋገር እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ ለዚህም ሂደት ጦርነትን ማቆም፣የቀድሞ ታጣቂዎችን ተሀድሶ በመስጠት ወደ ኅብረተሰቡ መቀላቀል፣የማህበራዊ ኑሮ ስብራትን በምህረትና በይቅርታ መልሶ መገንባት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

የቀደምት እውቀቶቻችን ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ስብራቶቻችንን ለመጠገን የሚያስችሉ ናቸው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ የጦርነት ምዕራፍን በምህረትና በይቅርታ ለመዝጋት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ነው ያሉት።

ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት፣ፍትሐዊነትን ለማስፈን፣ ሰብዓዊ መብቶችን ለማክበርና እኩልነትን ለማረጋገጥ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው፤ በኦሮሚያ የተጀመረው የሰላም መንገድ አዲስ ምዕራፍ መክፈት መቻሉን ነው የገለጹት።

የኦሮሞን ሕዝብ ሰላም ማረጋገጥ በኦሮሚያ ክልል ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ ጠንካራ የበለጸገችና ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን መገንባት መሆኑን ይናገራሉ።

የሰላም ስምምነቱ በክልሉ ቀጣይነት ያለው ሰላምን ለማረጋገጥና የሚፈለገውን እድገት ለማምጣት መሠረት የሚጥል መሆኑን በመግለጽ፤ እሴቶችን በመጠቀም ማህበራዊ ስብራቶችን በይቅርታ ለማከም መሥራት የሁሉም ኃላፊነት እንደሆነ ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ክልሉን ከግጭት አዙሪት ወደ ዘላቂ ሰላም ለማሸጋገር በሚደረገው ጥረት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሕዝብ እየተመኘ ያለውን ዘላቂ ሰላም በማምጣት ወደ ልማት መሸጋገርና የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ሊያገኙ ይገባል ያሉት ደግሞ በውይይቱ ላይ የመነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት አቶ ደበላ ፊጡማ ናቸው።

ሕዝብ ተረጋግቶ፣ መንግሥት ወደ መደበኛ ሥራው ተመልሶ ልማትን ማረጋገጥ የሚቻለው ዘላቂ ሰላም ሲኖር ነው ያሉት አቶ ደበላ፤ ዘላቂ ሰላምን በማምጣት ወደ ልማት ለመሸጋገር የትጥቅ ማስፈታ እና መልሶ ማቋቋም ተግባር ወሳኝ ነው ይላሉ።

ትጥቅ ማስፈታትና መልሶ ማቋቋም ፖለቲካዊ፣ወታደራዊ፣ሰላምና ጸጥታን ጨምሮ፣የሰብዓዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

የቀድሞ ታጣቂዎችን ትጥቅ ማስፈታትና መልሶ ማቋቋም ጦርነት ተመልሶ እንዳይመጣ መፍትሔ የሚሆን መሆኑን ጠቅሰው፤ ሰላም፣ ጸጥታ ፣ልማትና እድገት እንዲረጋገጥ የሚያስችል እንደሆነ ነው የገለጹት።

በመንግሥትና ታጥቀው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ ታጣቂዎች ጋር ፖለቲካዊ መተማመን እንዲኖር ለማድረግ ትጥቅ ማስፈታትና መልሶ ማቋቋም ወሳኝ መሆኑን በመግለጽ፤ ቀጣይነት ያለው ሰላም ለማምጣትና ልማትን ለማረጋገጥ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

ዘላቂ ሰላም ሕዝብ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖረው በር እንደሚከፍትና መንግሥትም ለመደበኛ ሥራዎቹ ትኩረት እንዲሰጥ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችም በሰላማዊ መንገድ ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮ እንዲመሩ ያስችላል ነው ያሉት።

# “መቄዶንያ ብዙዎችን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በማድረግ መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህ ደግሞ የመቄዶንያ አረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል አርዓያ የሚሆን እንደሆነ ገልጸዋል።

በጉብኝቱ የሰውን ልጅ ብርታት ተመልክቻለሁ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ተስፋ መቁረጥም እንደሚሸነፍ ተረድቻለሁ። ከተባበርንና ከተጋገዘን ተስፋ መቁረጥም ያልፋል፤ ሞትም ይሸነፋል።እዚህ ያየሁት ይህንን ነው ብለዋል።

ማዕከሉ የኢትዮጵያዊነት ብርታት ከሚለኩባቸው ተግባራት አንዱ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ወገንን መታደግ ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ብርታት አንዱ መገለጫ እንደሆነ ተናግረዋል።

ማዕከሉ ቅርንጫፎቹን ወደ 240 ለማድረስ ማቀዱን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ በ60 ሰዎች ጀምሮ ስምንት ሺህ መድረሱና ከአዲስ አበባ አንስቶ ወደ 44 ከተሞች መድረሱ ወደፊት ይህን ዕቅዱን ለማሳካቱ ማሳያ እንደሆነ አመልክተዋል።

ማዕከሉ የካቲት 1 ቀን 2017 ዓ.ም በሚጀምረው የሕንፃ ግንባታ ማጠናቀቂያ የገቢ ማሰባሰቢያ ላይም የማዕከሉን በጎ ሥራ የተመለከተ ሁሉ በወገን ተቆርቋሪነት መንፈስ ድጋፉን እንዲለግስ ጥሪ አቅርበዋል።

መስጠት የተቀባዩን ልብ የሚሞላውን ያህል የሰጪውንም መንፈስ ይሞላል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህን ተቋም መርዳት ለወገኖቻችን፣ ለእናት ለአባቶቻችንና ለተጎሳቆሉ ሁሉ የሚውል በመሆኑ እገዛ ማድረግ እንደሚገባም ተናግረዋል።

በጎነትን መንገድ ያደረገና ቅንነትን የተላበሰ ሁሉ በመቄዶንያ ለተጀመሩ የወገን አድን ሥራዎች እንዲተባበሩ ጠይቀው፤ ይህ ተቋም ትናንት ያልነበረ፣ ዛሬ ያለ ለወደፊቱ የሚተጋ ነው። በረከቱ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን በመሆኑ በዚሁ በርትታችሁ እንድትቀጥሉ አደራ እላለሁ ብለዋል።

የሚዲያ ባለሙያዎችም ይህን ሃሳብ በማገዝና ወደ ሕዝብ የማድረስ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ የማዕከሉን ሃሳብ እውን ለማድረግ እንዲተባበር ለመላው ኢትዮጵያውያን፣ ለመንግሥት ሠራተኞችና ለኩባንያ ኃላፊዎች በፊትም ታደርጉት እንደነበረው ልግስናችሁ እንዳይለይ አደራ እላለሁ የሚል መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል።

ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል አረጋውያን ያቀረቡላቸውን የበላይ ጠባቂነት ጥያቄ ተቀብለዋል።

እንደ ርዕሰ ብሔር የሁሉም ተቋም የበላይ ጠባቂ መሆናቸውን ገልጸው፤ ከአረጋውያኑ እንደማይለዩና ሁሉም ሰው ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጥሪ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

የአረጋውያኑ ሁለተኛ ጥያቄ የሆነውና በየዓመቱ ታኅሣሥ 18 ቀን እየመጡ እንዲጎበኟቸው የቀረበውን ጥሪም በተመለከተም ፕሬዚዳንቱ በየዓመቱ በዚሁ ቀን ወደ ማዕከሉ እየመጡ እንደሚጎበኟቸው ቃል ገብተዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “የአክሲዮን ገበያ የኢንቨስትመንት ማሳለጫ ነው”

- ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቦርጂ (ዶ/ር)
በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ



አስቴር ኤልያስ

የዛሬው የዘመን እንግዳችን ተወልደው ያደጉት በሲዳማ ክልል ዳራ ወረዳ ሲሆን፣ ልዩ ቦታው ሰፈረ ኬሳ በመባል የሚታወቅ ነው። አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው በተወለዱት አካባቢ ሰፈረ ኬሳ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን፣ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍልን የተማሩት ደግሞ በአለታ ወንዶ ከተማ ነው። ዘጠነኛና 10ኛን ዲላ ከተማ የተከታተሉ ሲሆን፣ 11ኛ ክፍልን ለመቀጠል ግን ካሉበት ክልል ርቀው ወደ ምሥራቁ የሀገራችን ክፍል ማቅናት የግድ በመሆኑ ወደ ጅግጅጋ ከተማ አቅንተው 11ኛ ክፍልን ተማሩ።

እዚያው ምሥራቁን አካባቢ ሳይለቁ ድሬዳዋ ደግሞ 12ኛ ክፍልን መማር ችለዋል። እኚህ የዛሬው የዘመን እንግዳችን በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቦርጂ (ዶ/ር) ናቸው።

እንግዳችን በደርግ ዘመን 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ከመቀጠላቸው በፊት የዚያኔው ተማሪ ብርሃኑን በ1969 ዓ.ም ለአየር ኃይል ትምህርት ወደራሽያ አቀኑ። እስከ 1971 ዓ.ም ድረስም በዚያው በራሽያ ቆዩ። ልክ ራሽያ ቆይተው ወደሀገራቸው እንደተመለሱም የተመደቡት አሰብ ነበር። አሰብ ለመማር እምብዛም ምቹ ስላልነበር 11ኛ ክፍል ላይ ያቋረጡትን ትምህርታቸውን መቀጠል አልቻሉም።

ነገር ግን በአየር ኃይል በኩል የተሰጣቸውን የአሰብ የቆይታ ግዳጃቸውን ጨርሰው ወደ ጅግጅጋ በማቅናታቸው 11ኛ ክፍል እዛው መማር ቻሉ። የጅግጅጋ ግዳጃቸውን እንዳጠናቀቁ የተዘዋወሩት ወደ ድሬዳዋ ነበርና 12ኛ ክፍልን ደግሞ በዚያው ለመማር በቁ። በወቅቱ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱት በ1982 ሲሆን፣ ያመጡትም ነጥብ ሶስት ነጥብ ስድስት ነበር። ይህን ከፍተኛ ነጥብ ይዘው በ1983 ዓ.ም የደርግ መንግሥት ከመውደቁ በፊት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ለመቀላቀል በቁ።

የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የያዙት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ ማኔጅመንት ነው። በኋላ ላይ ግን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሲሰሩ ስፔሻላይዝድ ያደረጉት ማርኬቲንግ ማኔጅመንትን ነው። ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የሠሩት በሰሜን ህንድ ሲሆን፣ ሶስተኛ ዲግሪያቸውንም በዚያው በህንድ በማርኬቲንግ ማኔጅመንት ነው።

እንግዳችን፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቡት እኤአ 2001 ላይ ነው። በዩኒቨርሲቲ መምህርነት 25 ዓመት ያህል ማገልገል ችለዋል። የፕሮፌሰርነትን ማዕረግ ካገኙ አስር ያህል ዓመት ያስቆጠሩ ሲሆን፣ ስፔሻል ያደረጉት የትምህርት ዓይነት ደግሞ ማርኬቲንግ ማኔጅመንት ላይ ነው። በአሁኑ ወቅት የሚስተምሩትም የማርኬቲንግ ተማሪዎችን ነው። ምርምርም የሚያካሔዱት በዚሁ በማርኬቲንግ ዘርፍ ላይ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ብዙ አርቲክሎችን ለሕትመት ያበቁ ናቸው። ለሕትመት ያበቁት አርቲክል ወደ 17 ያህል የሚጠጋ ሲሆን, “Impact of Liberalization on Ethiopian” በሚል ርዕስ አንድ መጻሐፍም ለንባብ ማብቃት ችለዋል። እንግዳችን እንዳሉት ከሆነ፤ በመላ ኢትዮጵያ በማርኬቲንግ ፕሮፌሰር ያሉት እርሳቸው ብቻ ናቸው። የሚያስተምሩትም የሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ነው። አዲስ ዘመን እኚህን አንጋፋና በዘርፉ ከፍተኛ ምሁር እና ተመራማሪ የሆኑትን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቦርጂ (ዶ/ር)ን የዛሬው የዘመን እንግዳ አድርጎ አቅርቧቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ በዋናነት ምርምር ሲያካሄዱ የነበረውና አሁንም እያካሄዱ ያሉት ማርኬቲንግ ማኔጅመንት ላይ ነው፤ በዚሁ ዘርፍ ውስጥ የአክሲዮን ገበያ ሲባል ምን ማለት ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የአክሲዮን ገበያ (ስቶክ ማርኬት) ሲባል ትርጓሜው ሰፊ ነው። በአጭሩ ለማስቀመጥ ያህል ግን አክሲዮን ለመሸጥና ለመግዛት የተመዘገቡ ኩባንያዎች ማለትም በይፋ የሚሸጡ ኩባንያዎች (Publicly Traded Companies) እንደ ማለት ነው። ይህ ማለት በሕጋዊነት የተመዘገቡ እና ሕጋዊነት የተሰጣቸው አካላት ናቸው። በጥቅሉ ኩባንያዎች የሚሸጡበትና የሚገዙበት ገበያ ማለት ነው።

በይፋ የሚሸጡ ኩባንያዎች (Publicly traded companies) በጣም ሰፊ ናቸው። እነዚህ ኩባንያዎች ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች አሉ። እነዚያን ሁሉ አሟልተው ደግሞ አክሲዮኑን እንዲሸጡና እንዲገዙ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት የሚባል አለ፤ ይህ ማለት ለምሳሌ ልክ እንደኒዮዎርክ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት እንዲሁም ለንደን ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት የሚባለው ዓይነት ነው። እነዚያ ተቆጣጣሪ አካላት (Regulatory bodies) ናቸው። ተቆጣጣሪ አካላት ሲባል ደግሞ ለስቶክ ማርኬት ሕግ የሚያወጡ ናቸው። እንደዚያ ሲባል ደግሞ ኩባንያዎች አክስዮናቸውን የሚሸጡበትና የሚገዙበት ገበያ ማለት ነው።

አክሲዮን የሚገዙት እና የሚሸጡት ኢንቨስተሮች ብቻ አይደሉም፤ ሕዝብም ይገዛል። ስለዚህ ገበያው ክፍት ነው ማለት ነው። ክፍት ገበያ ነው ሲባል በሩ የተዘጋ አይደለም ማለት ነው፤ አንድ አካል አክስዮን ገዝቶ ገበያ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ሁኔታውን አይቶ የሚያሰጋው ከሆነ ወዲያኑ ለሌላ ሰው መሸጥ ይችላል።

የአክሲዮን ገበያ በጣም ትርፋማ ስለሆነ ሌላው ማለትም ገዥው አካል ሳያቅማማ ይገዛል። በርግጥም ገዥዎችም ሆኑ ሻጮች ስቶክ ማርኬቱን ለመሸጥና ለመግዛት ገበያውን ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። ገበያውን ከወዲሁ መገመት ያስፈልጋል። ገበያው እያደገ ነው ያለው ወይስ እየወደቀ ነው ያለው ወይ? የሚለው መጠየቅ አለበት፤ እየወደቀ ካለ ደግሞ የስቶክ ማርኬቱ ዋጋ ሊረክስና ሊቀንስ ይገባል። ስለዚህ ይህን ከወዲሁ መገመት የሚችል ሁሉ ስቶክ ማርኬቱን ኢንቨስተሮችም ሌላው ሕዝብም ሊገዛ ስለሚችልና ከገዛም በኋላ ደግሞ መልሶ ሊሸጥ ስለሚችል በጣም ጥሩ የሚባል ገበያ ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የአክሲዮን ገበያ ዋና ዓላማው ምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የስቶክ ማርኬት ዓላማ ገንዘብ ማመንጨት ነው። ይህ ስቶክ ማርኬት በኩባንያዎች ሊሰበሰብ ይችላል። አንድ ኩባንያ ሌላ ኢንቨስትመንት ለማካሔድ ወይም ደግሞ ለመሥራት በሚፈልግበት ጊዜ ገንዘብ በእጁ ላይኖር ይችላል፤ በዚያን ጊዜ በስቶክ ማርኬት ውስጥ ስቶክ ሊሸጥ ይችላል። ልክ ቀደም ሲል እንደተደረገውና መንግሥት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድን እንደሸጠው ዓይነት ሊሆን ይችላል። ይህ የዓባይ ግድብ ቦንድ የተሸጠበት ዓላማ መንግሥት ከሕዝብና ከኢንቨስተሮች ለመበደር በማሰቡ ነው።

ለምሳሌ አንድ ሰው ፋብሪካ የሚያቋቁም ከሆነ ስቶክ ይሸጣል፤ ስቶክ የገዛው አካል የዚያ የሚቋቋመውን ፋብሪካ የሆነች ያህል ባለቤትነትን ገዝቷል ማለት ነው። ለአብነት ያህል እኔ አንድ የስሚንቶ ፋብሪካ ማቋቋም እፈልጋለሁ ልበል፤ ነገር ግን ገንዘብ ደግሞ የለኝም። ገንዘብ ስለሌለኝ ለሕዝብ ስቶክ ሸጬ ገንዘብ ማሰባሰብ አለብኝ ማለት ነው። ስቶኩን የገዛው ሕዝብ ለዚያ ለሲሚንቶ ፋብሪካ የተወሰነውን ያህል ማለትም በገዛው ስቶክ ልክ ባለቤት ነው ማለት ነው። ስለዚህም ገንዘቡ ለሲሚንቶ ፋብሪካ ባለቤቱ፤ በዚህ መልክ የሚሰበሰብ ይሆናል። ስለዚህ የስቶክ ማርኬቱ ዓላማ ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማሰባሰብ የሚያስችል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአክሲዮን ገበያ ባህሪያት ምን ምን ናቸው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የስቶክ ማርኬት ባህሪያት ናቸው ከሚባሉት አንዱ ለምሳሌ የሚሸጠው ስቶክ በዚያ በሚሸጠው ኩባንያ ውስጥ ባለቤትነት እንዲኖረው ማድረጉ ነው። ገዥው ግለሰብ ሊሆን ይችላል፤ አሊያም ኢንቨስተር ሊሆን ይችላል። አንድ ስቶክ በሚገዛበት ጊዜ ስቶኩን በሚሸጠው ኩባንያ ውስጥ የራሱ የባለቤትነት መብት ይኖረዋል ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት የሚባለው ነው። በዚህ በስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት ውስጥ ተቆጣጣሪ አካል (Regulatory body) አለ። እንዲህ ሲባል ይህ አካል ገበያውን የሚቆጣጠር ነው ማለት ነው። ገበያውን መቆጣጠር ማለት ደግሞ አንደኛ ገበያው ሰላማዊ በሆነ መንገድ የተሳለጠ እንዲሆን ማድረግ ነው፤ በገበያው ውስጥም ማጭበርበር እንዳይኖርም ቁጥጥር ያደርጋል። በሻጭ እና በገዥ መካከልም መተማመን እንዲኖር ለማድረግ የሚያግዝ ነው። ለምሳሌ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት የሚባለው ለምሳሌ ቀደም ብዬ ልጠቅስልሽ እንደሞከርኩት ኒዮዎርክ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት ወይም ለንደን ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት የሚባል አለ፤ እነዚህ ስቶክ የሚሸጡት በእነዚያ ማርኬት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው። በዚያ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ከሆኑ ተዓማኒያን ናቸው ማለት ነው።

ለምሳሌ አንዳንድ አካላት አዲስ አበባ ውስጥ ሪል ስቴት በሚል ቤት እንሠራለን ብለው ገንዘብ ከሕዝብ ከሰበሰቡ በኋላ አድራሻቸውን የሚያጠፉ እንዳሉ ብዙ ጊዜ ይሰማል። ይህ ግን እንደዚያ ዓይነት አይደለም። ሻጮቹ በስቶክ ማርኬቱ ዝርዝር ውስጥ የገቡ ስለሆነ በማጭበርበር የትም መድረስ ስለማይችሉ ተዓማኒነት ያለው ነው። ከዚህ የተነሳ አክስዮን ገበያ (ስቶክ ማርኬቱ) ተዓማኒነት ያለው ነው። ለምን ከተባለ በስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት ውስጥ ዝርዝራቸው የተካተተ በመሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የስቶክ ማርኬት የአካሄድ ስልቱ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የስቶክ ማርኬት አካሄድ ግልጽ ነው። ማርኬት መካኒዝሙን በተመለከተ፤ ማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ መንግሥት ማርኬቱን አያስተጓጉለውም። የስቶክ ማርኬቱ ዋጋ የሚወሰነው በአቅርቦቱና ፍላጎቱ ላይ ነው። ማርኬቱ ዋጋ የሚመራው በእነዚህ በሁለቱ ነው። ለምሳሌ ገበያ ውስጥ ዋጋው የሚወርደውና የሚጨምረው በአቅርቦቱና ፍላጎቱ አማካይነት ነው።

ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ስቶክ ማርኬት ይቋቋማል ሲባል ማንም ምንም ጫና መፍጠር አይችልም። መንግሥት በዚያ ውስጥ ድርሻ አይኖረውም። የሚገዙ አካላት ከመንግሥትም ሆነ ከሌላው አካል ጫና ነፃ የሆኑ ናቸው። ከማንም ነፃ ስለመሆናቸው ሊተማመኑ ይችላሉ ማለት ነው። ምክንያቱም ይህን መሸጥና መግዛት የሚችሉት ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬቱ ውስጥ ተመዝግበው ዝርዝራቸው ያሉ አካላት ናቸው።

ሌላኛው ስቶክ ማርኬት የኢንቨስትመንት ማሳለጫ (Investment vehicle) ነው ሊባል ይችላል። ይሁንና እንዲያ ማሳለጫ መሆን ሲገባው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ኢንቨስተሮች ወይም ኩባንያዎች ግን ለዚህ ለዚህ ዓይነት አካሔድ ሁኔታዎች የተመቻቹላቸው አይደሉም።

እንዲያውም ስቶክ ማርኬት ኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ ቀደም የነበረው በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው። ይሁንና በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመንም ቢሆን ገና በማቆጥቆጥ ላይ እያለ መንግሥት ስለወደቀ ሊቀጥል አልቻለምና ፈርሷል። ከእርሳቸው መንግሥት መውደቅ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ስቶክ ማርኬት የሚባል በጭራሽ አልነበረም። ስለዚህ አሁን እነዚህ ኢንቨስተሮች ስቶክ ማርኬት ለመግዛት የግድ ጉዳዩ ራሱ ሊኖር ይገባዋል ማለት ነው። የአክስዮን ገበያው ሲኖር ደግሞ ለኢንቨስተሮቹ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ዘዴ ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው። ለዚህም ነው ስቶክ ማርኬት የኢንቨስትመንት ማሳለጫ (Investment vehicle) ነው የሚባለው። ምክንያቱም ኢንቨስትመንትን ይፈጥራል።

የተመቻቸ ሁኔታ ያገኙት አካላት ስቶክ ማርኬት ይገዛሉ። ስቶክ ማርኬት ላይ ገንዘብ ይሰበሰባል። ገንዘብ የሚሰበሰበው ደግሞ ከኢንቨስተርና ከሕዝብ ነው። ከዚያ የካፒታል ቀመር ይሠራል። ወይም ደግሞ ካፒታል እንዲከማች ይደረጋል። የተከማቸ ካፒታል ለሌላ ኢንቨስተር በብድር መልክ ይሰጣል ማለት ነው። አንድ አካል ያን ብድር በሚወስድበት ጊዜ በመጀመሪያ ምን እንደሚሠራበት ያስጠናል፤ በዚህ ጊዜ መርቻንት ባንከር (Merchant banker) የሚባል አለ፤ መርቻንት ባንከር ማለት ለኢንቨስተሮች የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ አፈላልጎ እና የቢዝነስ ፕላን ሰርቶ ኢንቨስተሩን ከአበዳሪው ጋር የሚያገናኝ እንደ ማለት ነው። ስለዚህ እንደ እነዚህ ዓይነት ምቹ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ከዚያ ከተከማቸው ገንዘብ ይበደርና ይሠራል።

ለምሳሌ ኢንቨስተሩ ብድር ወሰደ እንበል፤ ብድር ከወሰደ በኋላ ማሽነሪዎችን ገዛ፤ ከዚያም ማሽን ብቻ መግዛት ሥራውን የሚያሳልጥለት ባለመሆኑ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## “የአክሲዮን ገበያ የኢንቨስትመንት...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ባለሙያዎችን ይቀጥራል። በድርጅቱ የተቀጠሩት ባለሙያዎችም የራሳቸውን ገቢ ማግኘት ይጀምራሉ። ካገኙት ገቢ ደግሞ የሚጠቀሙትን ተጠቅመው የሚተርፈውን (Discretionary income) ገንዘብ በባንክ ያስቀምጣሉ። ባንክ ደግሞ ልክ የዚህ ዓይነቱን የብዙዎቹን ሰብስቦ ለሌላ ኢንቨስተር ያበድራል። ሌላውም ኢንቨስተር በተመሳሳይ የራሱን ቢዝነስ ይከፍትና እንደዚያው በተመሳሳይ መልክ ይሄዳል። ሌሎችም እንዲሁ ደግሞ ይከተላሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ያድጋል። ስለዚህ የአክስዮን ገበያ (ስቶክ ማርኬት) የኢንቨስትመንት ማሳለጫ ነው ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የስቶክ ማርኬት ዋናው ፋይዳ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የስቶክ ማርኬት አንደኛው ጠቀሜታ ካፒታል ምስረታው (capital formation) ነው። ማለትም የካፒታል ክምችትን መፍጠሩ ነው። ምክንያቱም የካፒታል ክምችት ባይፈጠር ኖሮ ኢንቨስተሩ የሚበደረው ነገር አይኖርም። ያዘጋጀው ጥሩ የሚባል የቢዝነስ ፕላን ቢኖረውም፣ ከፕላን ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ የሚሆነው ገንዘብ ሲኖር ነው። ገንዘብ የሚያበድረው ከሌለ ደግሞ ያንን ቢዝነስ ፕላን ማካሔድ አይችልም።

ስለዚህ የካፒታል ክምችት መፈጠር አለበት፤ የካፒታል ክምችት ደግሞ ከየት ነው የሚፈጠረው ከተባለ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ግለሰቦችና ኢንቨስተሮች አክሲዮን ሲገዙ ሲሆን፣ በዚያን ጊዜ የካፒታል ክምችት ይፈጠራል ማለት ነው። ክምችቱ ሲፈጠር ሌሎች መበደር ቻሉ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ያሳድጋል። ስለዚህ ስቶክ ማርኬት አንደኛው ፋይዳ የካፒታል ክምችት መፍጠሩ ነው።

ሁለተኛው ጠቀሜታ የኢኮኖሚ እድገት ነው። ምክንያቱም የካፒታል ክምችት ሲኖር፤ ብድር ይፈጠራል፤ ብድር ተፈጠረ ማለት ደግሞ የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር ያደርጋል። ምክንያቱም ተበድሮ የሆነ ኢንቨስትመንት ይከፍታል። ኢንቨስትመንት ተከፈተ ማለት ደግሞ ባለሙያዎች ተቀጠሩ ማለት ነው። ባለሙያዎቹ ሠሩ ማለት ደግሞ ትርፋማ መሆን ቻሉ እንደማለት ነው። ከሠሩት ላይ እነርሱም መቆጠብ ይጀምራሉ። በዚህ ውስጥ የሥራ እድል ተፈጠረ ማለትም ጭምር ነው። የሥራ እድል ተፈጠረ ማለት ደግሞ ሠራተኛው ለመንግሥት የሥራ ግብር መክፈል ቻለ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ውስጥ መተላለፍ ሲቻል ኢኮኖሚው ያድጋል ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ ለኢንቨስትመንት መልካም አጋጣሚዎች (lncrease lnvestment Opportunities) እንዲፈጠሩ ያደርጋል። ኢንቨስተሩ የቢዝነስ ፕላን ካለው ይበደርና መሥራት ይችላል። ስለዚህም የስቶክ ማርኬት ውጤቱ ብዙ ኢንቨስትመንቶች መልካም አጋጣሚዎች እንዲፈጠሩ ማድረጉም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአክሲዮን ገበያው ቀጥተኛ የሆነ የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አኳያ የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ስቶክ ማርኬት የውጭ ኢንቨስትመንትን የሚስብ ነው። የውጭውንም ካፒታል ይስባል፤ እንዲሁም አስቀድሜ እንደጠቀስኩት የስቶክ ማርኬቱ ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች በሚሸጥበት ጊዜ ይስብና የካፒታል ክምችት እንዲፈጠር ያደርጋል። የስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት መፈጠሩ ደግሞ መልካም አስተዳደር እንዲጠናከር ያደርጋል፤ ስለዚህ ይህ ሌላኛው ጥቅሙ ነው። በተለይም ግልጽነትና መተማመን እንዲኖር ያደርጋል። ግልጽነትና መተማመን ሲኖር አሠራሩ የተሳለጠ ይሆናል። ሌላኛው ጥቅሙ ደግሞ ለሁሉም የሚጠቅመው የስቶክ ማርኬቱን እያንዳንዱ ግለሰብ ስለሚገዛው ነው፤ በገዛው አክሲዮን ላይ የሚያገኘው ትርፍ ይኖራል፤ ስለዚህም እያንዳንዱ ግለሰብ የግል ሀብት (personal wealth creation) መፍጠር ይችላል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስቶክ ማርኬት ጉዳት ይኖረው ይሆን?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ወደ ጉዳቱ ስንመጣ የስቶክ ማርኬት ዋጋ የሚዋዥቅ መሆኑ ነው። ዋጋውን



የሚወስነው አቅርቦቱና ፍላጎቱ ነው ብለናል። ወሳኙ አቅርቦቱና ፍላጎቱ በመሆኑ የስቶክ ማርኬት ዋጋ ወጥ አይደለም። መንግሥትም የሚቆጣጠረው አይደለም፤ የሚቆጣጠረው አቅርቦቱና ፍላጎቱ ነው። በመሆኑም ዋጋው እንደ አየሩ ጸባይ፣ እንደ ገዥው ሕዝብና እንደ ገበያው ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው። ገበያው አንድ ጊዜ ከፍ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ሊል ይችላል። ስለሆነም የገበያው ተለዋዋጭ መሆን በራሱ ጉዳት ነው።

ምክንያቱም አንድ ሰው የስቶክ ማርኬቱ ዋጋ ነገ እንደዚህ ይሆናል ብሎ መወሰን አይችልም። የሚወስነው የወቅቱ የገበያ ሁኔታ ነው። ስለዚህ አንድ ግለሰብ አክሲዮኑን ገዝቶም ሊያተርፍ እንደሚችለው ሁሉ ሊከስር መቻሉ ደግሞ ጉዳት መኖሩን ያሳያል። ስለዚህ በመጀመሪያ ለመግዛት ሲታሰብ ሁኔታዎችን በማጥናት መሆን አለበት። ምክንያቱም ገበያው ነገ እንዲህ ይሆናል፤ ከነገ ወዲያ ደግሞ እንዲዚህ ይሆናል ብሎ የተወሰነ ነገር አይኖረውም። የሚቆጣጠረው ራሱ ገበያው ነው። በመሆኑም የገበያ መረጋጋትን ሊያስተጓጉል ይችላል። ይህ ሲሆን ደግሞ በመካከል ሻጩም ሆነ ገዥው ይጎዳል።

ሌላው የኢንቨስትመንት ግንዛቤ እጥረት (lack of lnevstment awareness) መኖሩ ነው። በኢትዮጵያ ነገሮች ሲታዩ እኛ ኋላቀር ነን ማለት ያስደፍራል። ምክንያቱም ስቶክ ማርኬት በሌሎች ሀገራት የቆየ ሲሆን፣ እኛ ዘንድ በኃይለሥላሴ ጊዜ ነበር ስንል በብዙ ዘግይቶ የመጣ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የእኛ ኢንቨስተሮች የዚያን ያህል ግንዛቤው የላቸውም። የስቶክ ማርኬት እውቀት የላቸውም። ትንሽም እንኳ ጭላንጭሉ ያለው ቦንድ በመግዛት ረገድ ነው ማለት ይቻላል። የገዛነው ቦንድ አደግ ሲል ደግሞ ገንዘብ እያገኘን የመሄዳችን ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በስቶክ ማርካት ያለን መረዳት ገና ብዙ የሚቀረን እንደሆነ አስባለሁ።

ስለዚህ የስቶክ ማርኬት ግንዛቤው በሌለበት ኢንቨስተሮች ደግሞ ደካማ የኢንቨስትመንት ውሳኔ (poor investment dicission) ሊወስዱ ይችላሉ። ደካማ ውሳኔ በሚወስዱበት ጊዜ ደግሞ ወደ ኪሳራም ሊያስገባቸው ይችላል። ምክንያቱም አሁን ባለው ልምድ መሠረት የሚገዙት ጥናቱን ሰርተውና እሱን አስልተው ነው። ምናልባት ውሳኔያቸው ደግሞ ሊጎዳቸው ይችላል ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ ቁጥጥሩ የሚፈተንበት (Regulatory challenge) ጊዜ አለ፤ እንደ እኛ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች ያለው አስተዳደሩ ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር (management inefficient) የሚፈተንበት ጊዜ ይኖራል። እንዲህም ሲባል ለምሳሌ ተቆጣጣሪው አካል ራሱ ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር ማለት ነው። አንድ አካል ሲመጣ ሌላ ሕግ ያወጣል፤ በዚህ ውስጥ ደግሞ ሙስናው አለ። እነዚህ የሚያሳድሩት ማርኬት የተሳለጠ እንዳይሆን ያደርጋሉ። ማርኬት የተሳለጠ ካልሆነ ደግሞ ኢንቨስተሩ በራስ መተማመን አይኖረውም። ይህ እንግዲህ ሶስተኛው ችግር ሲሆን፣ ሬጉላቶሪ ቻሌንጅ በመባል ይታወቃል።

**አዲስ ዘመን፡- የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ የሚያሳየው ምንድን ነው ይላሉ? እርስዎ እንዳሉት ወደ እኛ ሀገር ስቶክ ማርኬት ዘግይቶ የመጣ እንደመሆኑ ከሌሎች የወሰድነው ልምድ ይኖር ይሆን?**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ሌሎች ሀገሮች ስማቸው የገነነውን ብንጠቀስ እንደ ለንደንና ኒዮዎርክ ስቶክ ማርኬት እንዲሁም የጃፓኑም ሆኑ የሕንዶቹ ስቶክ ማርኬትን በብዛት ይሠሩበታል። በኢትዮጵያ አንድ ተረት አለ፤ ይኸውም ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ነው፤ ለሃምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው የሚለው ሲሆን፣ ይህን አባባል በአግባቡ አልተጠቀምንበትም። ስቶክ ማርኬት እንደዚህ ዓይነት አባባል ነው ማለት ይቻላል። አንድ ሰው አንድ ኢንቨስትመንት ወይም ፕሮጀክት አሊያም ፋብሪካም ሊሆን ይችላል እከፍታለሁ ብሎ ካሰበ ለአንድ ሰው በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል፤ የማይቻልም ነው። ነገር ግን ከብዙዎች ገንዘቡ በስቶክ ማርኬት አማካይነት ተሰብስቦ ሊሠራ ይችላል፤ ይህ እንደ ኢንሹራንስ ማለት ነው፤ ኢንሹራንስ አንድ ሰው አደጋ ከደረሰበት ኢንሹራንስ ከሌለው ምን ያህል ሊከብደው እንደሚችል ይታወቃል። ስቶክ ማርኬትም ከብዙዎች የተሰበሰበውን በመጠቀም አንድ ሰው ሊቋቋምበት ይችላል።

በርካታ ሀገራት የአክስዮን ገበያን መጠቀም ከፍተኛ እድገት ላይ ደርሰዋል። አሜሪካ፣ አውሮፓ፤ ህንድ፤ ሜክሲኮ የመሳሰሉ ሀገሮች በስቶክ ማርኬት በመጠቀም እድገታቸውን አፋጥነዋል። ስለሆነም ስቶክ ማርኬት ለአንድ ሀገር እድገትን የሚያመጣ ነው።

እኔ ለምሳሌ በሕንድ ሀገር ሁለተኛ ዲግሪዬን በምማርበት ወቅት ማይነሬ መርቻንት ባንኪንግ ነበር። ሁሉም በስቶክ ማርኬት የተገኘውን ገንዘብ በማሰባሰብ ነው እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት ማለት ይቻላል። የእኛን ሀገር መለስ ብለን ስናስተውል በጣም መዘግየታችን ይገባናል።

ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚባል የኮሪደር ልማት እየተካሄደ እንዳለ የሚታወቅ ነው፤ የኮሪደር ልማቱን ለመሥራት እየተንቀሳቀስን ያለነው ተበድረን ነው። ይህ ዓይነት ብድር ደግሞ በጣም ውድ ብድር እንደሚሆን ይታመናል።

በስቶክ ማርኬት በተገኘ ገንዘብ ከሆነ ግን የሚከፈለው ወለድ ጥቂት ነው አምስት በመቶ አሊያም አስር በመቶ ሊሆን ይችላል እንጂ እንደዛኛው ውድ አይሆንም። ስለሆነም ስቶክ ማርኬት ከጠቀሜታው አንጻር ፋይዳ ያለው ነውና በሀገራችን መለመድ አለበት እላለሁ። ምክንያቱም ሌሎች ሀገሮች ያደጉት በዚህ ነው የሚል አተያይ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ኢትዮ ቴሌኮም አስር በመቶ የሚሆነውን የአክሲዮን ድርሻውን ሸጧል፤ ይህን እርስዎ የሚያዩት እንዴት ነው**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** በርግጥም የአክሲዮን ሽያጩ የተሸጠው አስር በመቶው ነው። አስር በመቶ ብቻ መሆኑ በተወሰነ መልኩ ገዥዎቹ መተማመን እንዳይኖራቸው የሚያደርጋቸው ነው። ብዙ ጊዜ አክሲዮን ሲሸጥ 51 በመቶ ለ49 በመቶ ድረስ ነው። ሻጩ ድርጅት 51 በመቶውን ሲይዝ፣ ገዥው አካል ደግሞ 49 በመቶውን ይይዛል። በዚህ ጊዜ ሻጩ አካል ብልጫ ስላለው ለውሳኔ ያመቸዋል። ሻጩ አካል 49ኙን በሚሸጥበት ጊዜ አላስፈላጊ ነገር ቢፈጠር እንኳ የገዛው 49 በመቶ በመሆኑ ሻጩን አካል ሊገዳደረው ይችላል ማለት ነው። ምናልባትም ደግሞ ከ51 በመቶው ውስጥ ገዥውን አካል ሊደግፍ የሚችል አካል ሊኖር ይችላል። በዚህ ጊዜ ሻጩ አካል ፈተና ውስጥ ሊገባ ይችላል። ስለዚህ ሁልጊዜ ትክክለኛ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው አክሲዮኖች በዚህ መልኩ ሲሸጡ ነው።

አስር በመቶ ሲሆን ግን ውሳኔ ላይ ሲመጣ እዚህ ግባ የማይባል በመሆኑ አንድ ውሳኔ በሚቀርብበት ጊዜ እጅ ወጣ አልወጣ ትርጉም የሚሰጥ አይሆንም ማለት ነው። ነገር ግን መጀመሩ በራሱ በጣም ጥሩ ነው የሚባል ነው። እንዲያም ሆኖ አክሲዮን ተሸጦ የሚገኘው ገንዘብ ለምን ዓይነት ኢንቨስትመንት ይውላል የሚለው መታወቅ አለበት እንጂ ጅማሬ ጥሩ የሚባል ነው። ምክንያቱም አክስዮን የመሸጡ ዋና ዓላማ ገንዘብን በማሰባሰብ እና ሌላ ኢንቨስትመንት ለመገንባት ነው። ነገር ግን ኢትዮ ቴሌኮም አክሲዮን ሸጦ ራሱን ለማስፋፋት ነው ወይስ ለሌላ ነው የሚለው ግልጽ ባይሆንም መጀመሩ በራሱ በጣም የሚደገፍና የሚበረታታ ነው።

ለሕዝብ ማስተላለፈ የምፈልገው መልዕክት አክሲዮን መግዛት ማለት ገንዘብን በባንክ እንደ ማስቀመጥ ማለት ነው። እንደዚያ ሲባል ገንዘብን በባንክ ስናስቀምጥ ማንም የማይወስድብን መሆኑንና ተዓማኒነት ያለው ስለመሆኑ አሳምረን እናውቃለን፤ አክሲዮንም ልክ እንደዚያ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ስቶክ ኤክስቼንጅ ማርኬት ውስጥ የተመዘገቡት ኩባንያዎች ናቸው ይህንን የሚሸጡት። ስለዚህም ተዓማኒነት ያለው ነው። ስለዚህ ተዓማኒ ስለሆነ ገንዘባችንን በባንክ ብቻ ተወስነን ከማስቀመጥ የዚህ ዓይነቶችንም በመግዛት ገበያችንን ከፍ ማድረግ እንችላለን። እነዚህን ስቶኮች በምንሸጥበት ጊዜ ገበያችን ከፍ እያለ ይሄዳል፤ የውጭዎችንም ኢንቨስተሮችን መሳብ ይችላል። የውጭ ኢንቨስተሮች ደግሞ የውጭ ምንዛሬም ይዘው ስለሚመጡ የውጭ ምንዛሪ እጥረታችንን እንቀርፋለን ማለት ነው። ስለዚህ በብዙ መንገድ የሚጠቅመን ስለሆነ ሁሉም ሊሳተፍበት ይገባል ለማለት እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን መረጃ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ጥቅም ላይ ያልዋለ የቤቶችና መሬት ልማት ማፋጠኛው አዲስ መንገድ

**እስመለዓለም**

ጥቅም ላይ ባልዋሉ ቦታዎችና አገልግሎት በማይሰጡ ህንጻዎች ላይ ከፍተኛ የንብረት ታክስ እንዲጣልባቸው የሚያደርግ ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው። ይህን አስመልክቶ በቅርቡ በተካሄደ ውይይት ላይ የገንዘብ ሚኒስቴር ኃላፊ የሰጡትን ማብራሪያ ዋቢ ያደረገ አንድ ዘገባ እንዳመለከተው፤ የረቂቅ አዋጁ ዓላማ ጥቅም ላይ ያልዋለ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ለሀገሪቱ ልማትና እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስቻል ነው።

ይህ ረቂቅ አዋጅ ጸድቆ ወደ ሥራ ሲገባ ሰፊ ቦታ ይዘው እንዲሁም ህንጻ ገንብተው ሳያከራዩ ያስቀመጡ ሁሉ ከፍተኛውን የንብረት ታክስ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል። ይህ አዋጅ እንደተባለው ሰፋፊ ቦታዎችን ያለ ምንም ሥራ አጥረው የያዙ አካላት ያሉባት አዲስ አበባ፣ ህንጻዎችን ገንብተው ወደ ሥራ ያላስገቡ ወገኖች በርካታ እንደሆኑ የሚነገርባት አዲስ አበባ ከተማ ቦታዎቹም ህንጻዎቹም በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

የቦታዎቹም ሆነ የቤቶቹ ወይም ህንጻዎቹ ወደ ሥራ መግባት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሚሆን ይታወቃል፤ ከተማዋ ከኪራይና ከመሳሰለው ግብር እንዲሁም ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚ እንድትሆን ያደርጋል። በከተማ የሚታየውን የመኖሪያ እንዲሁም የንግድና የመሳሰሉት ቤቶች እጥረትን በተወሰነ መልኩ በመፍታት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የከተማ አስተዳደሩ ቦታዎችን ምንም ዓይነት ጥቅም በማይሰጡበት ሁኔታ አጥረው ያስቀመጡ እንዲሁም መኖሪያ ቤት ህንጻ ገንብተው ለአገልግሎት ያላበቁ ዘግተው ያስቀመጡ ነዋሪዎች፣ ባለሀብቶች፣ ድርጅቶች ምን ያህል ስለመሆናቸው የተካሄደ ጥናት ቢኖር በጉዳዩ ላይ በደንብ መነጋገር የሚቻል ቢሆንም፣ ስለችግሩ አሳሳቢነት ለመናገር ግን የግድ ይህ መረጃ ያስፈልጋል ማለት አይደለም። እውነታው የአደባባይ እውነታ ነውና።

በከተማዋ ይህን ዓይነት ቦታዎችና ህንጻዎች ጥቂት እንዳልሆኑ ይታወቃል፤ በከተማዋ ለብዙ ዓመታት የኖረ ሰው በከተማዋ በጣም በርካታ ሥራ ላይ ያልዋሉ ቦታዎች እንዲሁም ህንጻዎች ስለመኖራቸው መመስከር አይቸገርም።

የአዋጁ መዘጋጀትም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኘው ቦታና ህንጻ ብዙ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ነው ብሎ መናገር ግን ይቻላል። ረቂቅ አዋጁ ቦታ የሚወርስ ወይም የሚነቅል አይደለም፤ ከዚህ ይልቅ ባለይዞታዎቹ ታክሱን ፈርተው መሬቱን እንዲሁም ባለህንጻዎቹ ህንጻውን ወደ ሥራ እንዲያስገቡ ግፊት የሚፈጥር ነው።

በግል መኖሪያ ቤት ይዞታዎች፣ አንዳንድ የግልና መንግሥታዊ ተቋማት ግቢ ውስጥ ምንም ዓይነት አገልግሎት የማይሰጥ ሰፊ ቦታ ዳዋ በልቶት ይገኛል። ይሄን ጉድ ሲያልፉ ሲያገድሙ ማየት ይቻላል፤ ከዚህ በተረፈ ደግሞ በአካባቢው ካለ ባለወለል ህንጻ ላይ ሆኖ መመልከት ይቻላል።

በግቢያቸው ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ እና ሊወገዱ የሚገባቸው አገልግሎት ካቆሙ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠሩ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽኖች፣ ወዘተ ዳዋ ለብሰው የሚታዩባቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኢንዱስትሪዎች ወዘተ. ተቋማት ጥቂት አይደሉም።

በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥም እንዲሁ ምንም አገልግሎት የማይሰጥ ሰፊ ቦታ ማግኘት ቀላል ነው። በዚህ ሰፊ ትርፍ ቦታ ላይ ቤት ተገንብቶ ለተለያዩ አገልግሎቶች አልዋለ ወይም አረንጓዴ ሥፍራ ሆኖ ለግቢውም ለከተማም ውበት አላገለገለ የከተማ ጢሻ የሆነ ቦታ በነባርም በማስፋፊያም የከተማዋ አካባቢዎች በሚገኙ ባለይዞታዎች ግቢ ውስጥ በብዛት ይታያል።

በከተማዋ ትላልቅ ቪላ ቤቶች ብቻ የሚታይባቸው ከዚያ በተረፈ የረባ ግንባታ የማይታይባቸው ግቢዎች በብዛት ይገኛሉ፤ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ግቢዎችም እንዲሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፤ ይህን ሁሉ በመመልከት እነዚህ የሀገር ሀብቶች እንዴት ወደ ልማት ይግቡ በሚል ወደዚህ ርምጃ ለመግባት መታሰቡ በጣም ጥሩ እይታ ነው፤ ትልቅ ሀብት እየባከነ መሆኑ በሚገባ ታይቷልና።

አንዳንድ ግቢዎች ውስጥ የረባ ቤት በሌለበት ሁኔታ ቦታው ለነዋሪውም ለሰፈሬውም ለከተማዋም በማይጠቅምበት ሁኔታ ባክኖ የሚታይበት ሁኔታ ከዚህም በላይ ርምጃ ቢወሰድ ተገቢ አይደለም የሚያሰኝ ሁኔታ አለ ብዬ አላስብም።

እነዚህ በመንግሥት እይታ ውስጥ የገቡት ቦታዎችና ህንጻዎች ባለቤቶችን ወደ ልማት ማስገባት የሚያስገድዳቸው ጠንካራ የሕግ ማሕቀፍ አልነበረም ብሎ ማለት አይቻልም። በየግቢው ያለውን ትርፍ መሬት ለሌላ ልማት ማዋል የሚያስችል ሥራ በቀደመው መንግሥት ተግባራዊ ሊደረግ ታስቦ ነበር ይመስለኛል። ያ አሠራር ትክክል ነው እያልኩ አይደለም፤ እሱም ቢሆን ከዚያ ወዲህ አልታየም።

መንግሥት እነዚህ ይዞታዎች ላይ ሊከተል የፈለገው አሠራር ልማቱን ያፋጥነዋል፤ የንብረት ረቂቅ አዋጁ ጸድቆ ወደ ሥራ ሲገባ ባለይዞታዎቹ መሬቱን እንዲያለሙት ግፊት ያሳድራል። የሚጣልባቸው ከፍተኛ ታክስ ይህን ወደ ማድረግ እንዲገቡ የሚያደርግ ነው። ይህን ከፍተኛ ታክስ እየከፈሉ መቆየት ይችላሉ ታብሎ አይታሰብም፤ ፈጥነው ወደ ማልማቱ ይገባሉ ተብሎ ይታሰባል፤ የመንግሥትም ርምጃ ይህን ማድረግ ነው። ይህ ሁኔታ ለባለይዞታዎቹም ከተማዋን በማልማት ላይ ትልቁን ኃላፊነት ይዞ ለሚሠራው መንግሥት ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ይህ አንድ አዲስ ነገር ነው።

አሁን ደግሞ መንግሥት ለአካባቢው ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ነው እንዲያለሙ የሚደረጉት። የእነሱ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የከተማዋ ፍላጎትም ታሳቢ ይደረጋል። እስከ አሁን ከተማዋ ያለ ፕላን የተመሠረተች ይመስል ብዙ የፕላን ጥሰቶች ተፈጽመዋል። በኮሪደር ልማቱ ለዚህ መፍትሔ ተቀምጧል። እነዚህ ቦታዎችም በዚሁ መሠረት እንዲለሙ የሚደረግ በመሆኑ ሳይለሙ መቆየታቸው የተሻለ ከተማ ለመገንባት ተጨማሪ እድል ይፈጥራል።

ወደ ትግበራው ከመግባቱ በፊት ግን ጥቅም ላይ ያልዋለ ቦታ ማለት ምን ማለት ስለመሆኑ በሚገባ ግልጽ መደረግ አለበት። ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ህንጻ መገንባት ብቻ ነው? ወይስ ሌላ ግንባታን ያካትታል? ይህም መታየት ይኖርበታል።

በከተማዋ ሰፋፊ ግቢ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች መኖራቸው የሚጠላ አይመስለኝም። ሰፋፊ ግቢ ውስጥ የተገነቡ፣ የአረንጓዴ ሥፍራ፣ መዋኛ፣ ወዘተ ያላቸው መኖሪያ ቤቶችን በከተማዋ መመልከት እንዳ ውበት ተደርጎ መታየትም ያለበት ይመስለኛል። በዞን ተለይቶ ይለማ ይሆናል እንጂ የውጭ ሀገሮች ተሞክሮም ይህን የሚፈቅድ ይመስለኛል።

በዚህ ዓይነት ግቢ ውስጥ ያለ ቦታም የባከነ ተብሎ የሚታይም አይመስለኝም። በአረንጓዴ ተክሎች ከሸፈኑ፣ ለእነሱም ለከተማዋም ውበት ከጨመሩ ጥሩ ነገር ነው፤ ይህ ግን በተቀመጠ ስታንዳርድ መሠረት የሚመዘን ይሆናል። ይህን ማድረግ ከቻሉ ባለይዞታዎቹ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቦታዎችን ይዘዋል የሚባሉ አይመስለኝም፤ ከዚያ ይልቅ በዚያ ደረጃ ያሉ ይዞታዎች ለመንግሥት መክፈል ያለባቸው ግብር ከፍተኛ መሆን ሊኖርበት ይችላል።

እንደተባለው ጥቅም ላይ ያልዋለ በሚል ብቻ ሰፋፊ ግቢ ያላቸውን ይዞታዎች በሙሉ ወደ ህንጻ መገንቢያነት እንዲቀየሩ ማድረግ አሉታዊ ጎን ይዞ እንዳይመጣም መገንዘብ ይገባል። ይህን ማድረግ ከተማዋ በግል ይዞታዎች ውስጥ ከፍት ቦታዎች እንዳይኖራት ያደርጋል። ዋናው ነገር ግን የግቢው መልማት መሆን አለበት። በግቢው ውስጥ ከከተማዋ ልማት ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ልማት እንዲካሄድ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ ውጪ ከተማዋ ያንን ዓይነት ግቢዎች ያላቸው መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም ድርጅቶች አያስፈልጋትም ወይ፣ የውጭ ሀገሮች ተሞክሮ ምን ይመስላል፣ የሚሉትን መመልከትም ይገባል። ያለውን ቦታ ሁሉ ግንባታ እንዲካሄድበት ማድረግ ትክክል ነው ብዬ አላምንም።

ከዚህ ውጪ መንግሥት ያለሙ ቦታዎች እወስዳለሁ አላለም፤ ፍላጎቱ ቢሆንማ አልሙ፤ ካላለማችሁ ለሌላ አልሚ አስተላልፋለሁ ይል ነበር። አሁን እያለ ያለው

> **በግል መኖሪያ ቤት ይዞታዎች፣ አንዳንድ የግልና መንግሥታዊ ተቋማት ግቢ ውስጥ ምንም ዓይነት አገልግሎት የማይሰጥ ሰፊ ቦታ ዳዋ በልቶት ይገኛል። ይሄን ጉድ ሲያልፉ ሲያገድሙ ማየት ይቻላል፤ ከዚህ በተረፈ ደግሞ በአካባቢው ካለ ባለወለል ህንጻ ላይ ሆኖ መመልከት ይቻላል**

ከፍተኛ ግብር እንዲከፍሉ በማድረግ ወደ ልማቱ እንደሚጡ እሰራለሁ ነው። እነዚህ አካላት እንዲያለሙ ጊዜ ይሰጣቸዋል? ወይስ የተጠላባቸውን ታክስ እየከፈሉ መቀመጥ ይችላሉ? እነዚህም መልስ ይፈልጋሉ።

ታክሱ አስመርሯቸው ቦታውን ያለሙታል ተብሎ ታስቦ ሊሆን ይችላል ወደዚህ ርምጃ የተገባው፤ ይሄ ትልቅ ለውጥ ያመጣል፤ ከእነዚህ አካላት ገንዘብ መሰብሰብ ትኩረት የሚደረግ ከሆነ ዳዋ የበላው ግቢ ገንዘብ እየተከፈለበት ባለበት ይቀመጥ ማለት እንዳይሆን እሰጋለሁ። የማያለሙት ከሆነ ከፍተኛውን ታክስ እንዲከፍሉ መደረጉ እንዳለ ሆኖ ቀጥሎ ምን ወደ ማድረግ እንደሚገባም ጠቆም ማድረግ ይገባል።

እንደሚታወቀው በከተማዋ ቦታ የለም እየተባለ ልማቱ ወደ ከተማዋ ዳርቻ ሲገፋ ኖሯል። እነዚህ መሠረተ ልማት በሚገባ የተዘረጋላቸው ቦታዎች ከተማዋ መሀል እያሉ መሠረተ ልማት ወዳልተዘረጋላቸው ቦታዎች አልሚዎችን በመውሰድ ልማቱን ለማስቀጠል ሲሠራ ቆይቷል።

በርካታ ህንጻዎች የውሃ፣ መንገድ፣ ኤሌክትሪክ፣ የቴሌኮም የጤና የትምህርት ወዘተ መሠረተ ልማት ባልዘረጋባቸው አካባቢዎች ህንጻዎች ተሠርተው የሚፈለግባቸውን አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ይታወቃል። ይህን አገልግሎት ለመስጠት እነዚህ መሠረተ ልማቶች የግድ ናቸው። በማስፋፊያ አካባቢ በርካታ ወጪ የወጣባቸው መኖሪያ ቤቶችና ግዙፍ ህንጻዎች ተዘግተው እንደሚገኙ ይገለጻል፤ እነዚህ ህንጻዎች ወጪ የተደረገባቸውን ታሳቢ ያደረገ ኪራይ በማያገኙበት ሁኔታ እንዲከራዩ ቢደረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል። ለማጠናቀቂያ ብዙ የወጣባቸው ህንጻዎች ለጉዳት ሊዳረጉ ይችላሉ።

መንግሥት ወደ አዋጁ ትግበራ ከመግባቱ በፊት እነዚህ ህንጻዎች የገጠማቸውን ችግር በቅድሚያ መፍታት ይኖርበታል፤ በማስፋፊያ ቦታዎች ውሃ ፣ የመጸዳጃ መሠረተ ልማት፣ ኤሌክትሪክ ባልተዘረጋበት እንዲሁም ሊፍት ለሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች ሊፍት ባልተገጠመበት ሁኔታ ህንጻዎቹ ያለ ጥቅም ተቀምጠዋል ብሎ መፍረድ ውስጥ መግባት አይገባም፤ ሊፍት የሚያስፈልጋቸው የ40 በ60 እና ባለ ሰባት ወለል ቤቶች ካለ ጥቅም ተቀምጠዋል ብሎ መፈረጅም እንዲሁ ትክክል ላይሆን ስለሚችል መንግሥት አስቀድሞ የእነዚህን ቤቶች የመሠረተ ልማት ችግር መፍታት ይኖርበታል።

እነዚህ ህንጻዎች በከተማዋ ያለ ምንም አገልግሎት በግለሰቦችና ድርጅቶች ተይዘው በተቀመጡ ቦታዎች ላይ ተገንብተው ቢሆን እንደተጠናቀቁ አገልግሎት መስጠት ይጀምሩ ነበር። ምንም እንኳ አሠራሩ ትክክል ነው ባይባልም በለሙት አካባቢዎች የተገነቡትን አንዳንድ ህንጻዎች ግንባታቸው ሳይጠናቀቅ ጭምር ምን ያህል ተፈላጊ ስለመሆናቸው ይታወቃል። ይህም የመሠረተ ልማቱን አስፈላጊነት ያመለክታል።

ከዚህ ውጭ ያሉ ሁሉም መሠረተ ልማቶች ባሉባቸው በከተማዋ መሀል ከተገነቡ አንዳንድ ህንጻዎች የተወሰኑትን ወለሎቻቸውን ወደ ሥራ በማስገባት የተቀሩትን ግን ያለቁ እንዲመስሉ ውጪያቸውን ብቻ አሳምሮ ውስጣቸውን ሳያጠናቅቁ ያስቀመጡ ባለህንጻዎች እንዳሉም ይታወቃል።

አዋጁ ወደ ሥራ ሲገባ በቀጥታ ሥራ ሊጀምርባቸው ይገባል ተብለው የሚታሰቡ ያለምንም ሥራ የተቀመጡ፣ ለከተማ ውብትም ደንቃራ የሆኑ የሀገር ሀብት በከንቱ እንዲበሰብስ እየተደረገባቸው የሚገኙ ያለ ጥቅም የተቀመጡ ቦታዎች ጥቂት አይደሉም፤ እነዚህ ቦታዎችና ህንጻዎች ላይ በሚገባ መሠረት ይኖርበታል።

ከዚያ ውጭ በሚገባ ሊታዩ የሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉ ይሰማኛል። ያለጥቅም የተቀመጡ ቦታዎችን መንግሥት እወስዳለሁ አላለም፤ ባለይዞታዎች እንዲያለሟቸው ግፊት የሚያሳድር አሠራር ነው ያስቀመጠው። ይሄ ጥሩ ነገር ነው።

ባለይዞታዎች በገዛ ቤቴ በገዛ ህንጻዬ በገዛ ይዞታዬ መንግሥት ምን አገባው ሊሉ አይችሉም፤ ቤቶቹም ይሁኑ ህንጻዎቹ የተገነቡት ለባለቤቶቻቸው ብቻ አይደለም፤ ለሀገርም ለከተማም ለሕዝብም ጭምር ነው። ከተማዋ በመኖሪያ ቤት እንዲሁም በንግድ ቤት እጥረት እየተቸገረች ባለችበት ሁኔታ ግንባታዎችን ቶሎ አጠናቆ፣ የተጠናቀቁትንም ፈጥኖ ለአገልግሎት አለማብቃት ሊያስጠይቅ እንደሚችል ለማስገንዘብ አዋጁ ሁነኛ መሳሪያ ይሆናል።

ለዚህ ማጠንከሪያ የሚሆን አንድ ጉዳይ ላንሳ። ብዙ ዓመታት ሆኖታል፤ ከሀዋሳ ወደ አዲስ አበባ በአውቶብስ እየተጓዝን ነበር። ጥቂት እንደተጓዝን ከታሪፍ ጋር በተያያዘ አንድ ተሳፋሪና ረዳቱ ጋር ውዝግብ ውስጥ ይገባሉ። ውዝግቡ እየተሟሟቀ መጣ፤ ሾፌርም ከረዳቱ ወገን ሆኖ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ጀመረ። አውቶብሱን አቁሞ ተሳፋሪው ወዳለበት ወንበር አካባቢ መምጣት ጀመረ፤ አሽከርካሪው የአውቶብሱ ባለቤት ሳይሆን አይቀርም፤ አነጋገሩ ይናገራል። እንዳውም ከመኪናዬ ላይ ውረድ ሲል ተሳፋሪውን በማሳሳብ ጎትቶ ሊያወርደውም ቃጣው።

ተሳፋሪውም ቆፍጠና ነበሩ፤ አልወርድም፤ አውቶብሱ ምንህም አይደለም፤ ሕዝብ ለማገልገል ያሰማራኸው ነው፤ አረፈህ ተቀምጥ ሲሉ መለሱለት። በመሀል ሰው ገባና ችግሩ ተፈታ። እኛ ቤታችን የኛ ቤት ብቻ ይመስለናል፤ የመንግሥትም የሕዝብም መሆኑን እንስታለን፤ ወይም ይህን ማሳወቅ ያለባቸው አካላት አላሳወቁን ይሆናል፤ ስለዚህ ቤታችን ድርጅታችን መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት ነው የሚተዳደረው፤ እኛም የምንተዳደረው።

ብዙ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቦታዎች ህንጻዎች በከተማዋ እንደመኖራቸው አዋጁ እነዚህ ቦታዎችና ህንጻዎች የሕዝቡን፣ የመንግሥትን እንዲሁም የተከራዮችንና የመሳሰሉትን ፍላጎቶች ሊያሟሉ ስለሚችሉ ያለሙት እንዲለሙ የለሙት ደግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ባለይዞታዎችና ባለንብረቶች ሊያስቡበት ይገባል። እንዲያለሙ ፣ ያለሙትም ወደ ሥራ እንዲያስገቡ የሚያስችል አዋጅ ነው እየተዘጋጀ ያለው። ይህን መልካም እድል በመጠቀም መሬታቸውን ያላለሙ ወደ ማልማቱ፣ ህንጻ ግንባታ ጨርሰው ወደ አገልግሎት ያላስገቡም እንዲሁ ህንጻዎቹን ወደ አገልግሎት ለማስገባት በፍጥነት መንቀሳቀስ አለባቸው።

ርምጃው የቤት፣ የመሬት ልማትን የሚያፋጥን አዲስ መንገድ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ሀገሪቱ ከመሬቷ፣ ከህንጻዎችና ቤቶች ተገቢውን ጥቅም ማግኘት ያለባት እንደመሆኑ፣ ካለማ፣ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ሥራ ካልገባ ህንጻ፣ ወዘተ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ብቻ አይደለም የሚያስችለው።

ሌሎች በቀጣይ ቦታ የሚወስዱ እንዲሁም ህንጻ የሚገነቡ አካላት ፈጥነው ግንባታ እንዲያካሂዱና ህንጻዎቹን ለአገልግሎት እንዲያበቁ፣ በዚህም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስችላል።

# ማህደረ ጤና

## የነርቭ ዘንግ ክፍተት ምንድን ነው?

**አስናቀ ፀጋዬ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ1ሺህ በሕይወት ከሚወለዱ ሕፃናት ውስጥ አንዱ በነርቭ ዘንግ ክፍተት የጤና ችግር እንደሚጠቃ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ጥቅል ዓለም አቀፍ አህዛዊ መረጃ በእድገት ላቅ ላሉት ሀገራት ሲከፋፈል ደግሞ 0 ነጥብ 8 አካባቢ እንደሆነ ይነገራል። ይህም የነርቭ ዘንግ ክፍተት በታዳጊ እንጂ በእድገት ግስጋሴ ውስጥ ባሉ ሀገራት ጉልህ የጤና ችግር እንዳልሆነ ያመለክታል። በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ2014 በተሠራ ጥናት በኢትዮጵያ ከ1ሺ በሕይወት ከሚወለዱ ሕፃናት መካከል ሰባት ሕፃናት የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግር እንዳለባቸው ተረጋግጧል። ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው አሃዝ ሰባት እጥፍ ይበልጣል ማለት ነው። ከዚህ አንፃር የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግር የጎላ የጤና ጉዳት እያስተከለ ስለመሆኑ መገመት አያዳግትም።

በየካቲት 12 ሆስፒታል የነርቭና ህብለ ሰረሰር ቀዶ ሕክምና ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ሳላዲን በድሩ እንደሚናገሩት፤ የወንዱ የዘር ፍሬ ከሴቷ እንቁላል ጋር ተገናኝቶ ፅንስ ከተፈጠረ በኋላ ሙሉ የሰውነት ክፍሎች መፈጠር ይጀመራሉ። በዚህ ሂደት ልብ ከተፈጠረ በኋላ ወዲያው መፈጠር የሚጀምረው የነርቭ ሥርዓት ሲሆን፤ የነርቭ ሥርዓት የሚፈጠረው ደግሞ እርግዝና ከተፈጠረ ከሶስተኛው ሳምንት በኋላ ነው። በዚህ ጊዜ አንጎልን፣ ህብለ ሰረሰርንና ነርቮች የሚሠሩት ክፍሎች በትክክል ሳይፈጠሩ ሲቀሩና ክፍተት ሲፈጠር የነርቭ ዘንግ ክፍተት / spinal bifida/ ይከሰታል። ስለዚህ ይህ የነርቭ ዘንግ ክፍት ከተለመዱ የአፈጣጠር ችግሮች ውስጥ የሚመደብ ነው።

ለነርቭ ዘንግ ክፍተት እንደ ዋና መንስኤ ሆኖ የተቀመጠውና በሳይንስም የተረጋገጠው የፎሊክ አሲድ ንጥረ ነገር እጥረት ሲሆን፤ ፎሊክ አሲድ ደግሞ የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጣቸው አስፈላጊ የምግብ ንጥረ ነገሮች ውስጥ አንደኛው ነው። ከቫይታሚን ቢ ኮምፕሌክስ ውስጥ ፎሊክ አሲድ ‹‹ቢ ናይን›› አንዱ መሆኑም ይታወቃል። ይህ ንጥረ ነገር አስፈላጊ ነው የተባለበትም ዋነኛው ምክንያት በሰውነት ውስጥ ስለማይመረት ነው። ስለዚህ የግዴታ ይህን ንጥረ ነገር ከምግብ ምንጭ ማግኘት ያስፈልጋል።


ፎሊክ አሲድ ሴሎች በሚራቡበት ጊዜ ዘረ-መል/ ዲ ኤን ኤ/ በትክክል እንዲፈጠርና እንዲዳብር ያደርጋል። ፅንስ ሲፈጠር ፈጣን የሆነ የሴሎች እድገት ይኖራል። ከፅንስ በኋላ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሲፈጠር ከባድ የሆነ የዘረ መል መባዛት ስለሚኖር በዚህ ላይ ፎሊክ አሲድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ስለዚህ የነርቭ ዘንግ ክፍተት ዋነኛ መንስኤ ነው ተብሎ የጠቀመጠው የፎሎክ አሲድ እጥረት ነው። ከዚህ ውጭ ግን በፅንስ ወቅት ለካንሰርና ለሚጥል በሽታ የሚወሰዱ መድኃኒቶች በተዘዋዋሪ በፎሊክ አሲድ ላይ ጣልቃ ስለሚገቡ ለነርቭ ዘንግ ክፍተት ሊያጋልጡ ይችላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቁጥጥሩ ጥሩ ያልሆነ የስኳር ህመምም ለነርቭ ዘንግ ክፍተት ሊያጋልጥ የሚችልበት እድል አለ። ከእርግዝና በፊት የሚከሰት ቅጥ ያጣ ውፍረት፣ የዘረ መል ችግሮች፣ ከዚህ በፊት በቤተሰብ ውስጥ የነበሩ እርግዝናዎች ላይ ችግሩ ከነበረ የነርቭ ዘንግ ክፍት የመከሰት አደጋን ከፍ ያደርገዋል። ከዚህ ውጭ ወጣት በሆኑና እርግዝና የመጀመሪያቸው በሆኑ ሴቶች ላይም ይህ ችግር ሲያጋጥም ይታያል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ሳላዲን ማብራሪያ፤ ፎሊክ አሲድ ንጥረ ነገር በምግቦች ላይ እንደልብ የሚገኝ ነው። ነገር ግን ካለው የሥነ ምግብ ባህሪ ችግር ጋር ተዳምሮ ድህነት፣ ጦርነትና ድርቅ ሲከሰት ፍላጎቱ በጣም ይጨምራል። ስለዚህ የፎሊክ አሲድ እጥረት የተመጣጠነ ምግብ ካለማግኘት ጋር የተያያዘ ነው። አብዛኛው እናቶች እርግዝና መከሰቱን እንኳን የሚያውቁት ከሁለትና ሶስት ወር በኋላ ነው። የነርቭ ዘንግ ክፍተት ደግሞ የሚፈጠረው ፅንስ ከተፈጠረ በሁለተኛው ሳምንት ነው። ያ ማለት እርግዝና ከተከሰተ ከሁለትና ሶስት ወር በኋላ እናቶች የፎሊክ አሲድ መውሰድ ቢጀምሩ እንኳን የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግሩን ሊያስቀሩ አይችሉም። ስለዚህ በተቻለ አቅም ከማርገዝ በፊት ከሁለት ወር ቀደም ብሎ፤ እርግዝና ከተከሰተ በኋላ ደግሞ በቀጣዮቹ ሁለትና ሶስት ወራት ፎሊክ አሲድ እንዲወስዱ ይመከራል።



ዶክተር ሳላዲን በድሩ፤




ፅንሱ በሆድ ውስጥ እንዳለ በአልትራሳውንድ በሚደረግ ምርመራ የነርቭ ዘንግ ክፍተት አፈጣጠር ችግር እንዳለ መለየት ይቻላል። በተለይ በሁለተኛው የእርግዝና ክፍል ላይ ማለትም ከአስራ ስድስት እስከ ሀያ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ችግሩ እንዳለና እንደሌለ ማረጋገጥ አያዳግትም። ህፃናት ከተወለዱ በኋላ የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግር ሲኖርባቸው በአከርካሪ አጥንታቸው ላይ ክፍተት ወይም እባጭ ነገር ይታይባቸዋል፤ የጭንቅላት መጠናቸውም ይገዝፋል።

የነርቭ ዘንግ ክፍተት ጤና ችግር ከተከሰተ በኋላ ሊታከም ይችላል። ሕክምናው የሚጀምረውም ልክ እናቲቱ እርጉዝ ሆና በፅንሱ ላይ የነርቭ ዘንግ ክፍት መኖሩ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ስለዚህ መጀመሪያ የሚሰጠው የምክርና አማራጭ የሕክምና አገልግሎት ይሆናል። ከቤተሰብ ጋር ውይይቶችም ይደረጋሉ። ይህም የልጁን ቀጣይ የሕይወት እጣ ፈንታ የሚወስን ነው።

በውጭ ሀገር ደግሞ ይህ የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግር ሲፈጠር ፅንሱን የማቋረጥ አማራጭ ይሰጣል። በኢትዮጵያም ይኸው አማራጭ አለ። ይሁንና ከማህበረሰቡ ባሕልና ሃይማኖትና ሥነ ልቦና ሁኔታ አንፃር አብዛኛው ቤተሰብ ፅንስ ማቋረጥን አይደግፍም። የነርቭ ዘንግ ክፈተት ችግር ብዙ የሰውነት ክፍሎችን ሥርዓት ያዛባል። በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ ህፃናት በእግራቸው ቆመው መራመድ ሊሳናቸውም ይችላል። ሽንት የመቆጣጠር ችግር ያጋጥማል። በጭንቅላት ውስጥ ውሃ መጠራቀም ይኖራል። የዳሌ መገጣጠሚያ ችግሮችና የእግር መቆልመም ያጋጥማል። ከፍተኛ የሥነ ልቦና ጫናም ያስከትላል። ከዚህ አንፃር በርካታ ሕክምናዎች የሚያስፈልጉት ነው።

ልጁ ከተወለደ በኋላ ደግሞ የመጀመሪያውና ለሁሉም ሕክምናዎች መሠረት የሚሆነው ሕክምና የነርቭ ዘንግ ክፍተቱን መዝጋት ነው። ነርቩ ቀድሞውኑ የአፈጣጠር ችግር ያለበት በመሆኑ ወደነበረበት መመለስ አይቻልም። ቤተሰብና እናት የሚጠብቁት ግን የነርቭ ዘንግ ክፍተቱ በቀዶ ሕክምና ከተስካከለ በኋላ የሽንት መቆጣጠር፣ የእግር መቆልመምና ሌሎችንም ችግሮች እንደሚያቆም ነው። ሆኖም ይህ ቀዶ ሕክምና በዚህ ላይ ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም። ነገር ግን የነርቭ ዘንግ ክፍተቱ በቀዶ ሕክምና ሲሞላ ልጁን ለመንከባከብ፣ በአከርካሪው ላይ የነበረውን እባጭ በማስወገድ በትክክል እንዲተኛ ለማድረግ፣ ኢንፌክሽን ለመቀነስ፣ የሌሎችን ነርቭ ሥራ ለመጠበቅና ሌላ ተጨማሪ ጉዳት እንዳያስተናግድ ይረዳዋል።

የነርቭ ዘንግ ክፍተቱን በቀዶ ሕክምና መድፈን የመጀመሪያው ሕክምና ቢሆንም ከቀዶ ሕክምናው በኋላ ሌሎች ሕክምናዎች ይኖራል። የዚህ ዓይነቱ አፈጣጠር ችግር ያለባቸው ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ህፃናት ጭንቅላታቸው ውሃ ይይዛል። ስለዚህ ቀጣዩ ሂደት የሚሆነው ውሃውን ማከም ነው። በመቀጠል ደግሞ የሽንትና ሰገራ መቆጣጠር ችግርን ለመቅረፍ ቤተሰብን የማስተማርና ልጆቹም ከፍ እያሉ ሲመጡ ተምረው ራሳቸው በራሳቸው እንዲያፀዳዱ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ። የተቆለመመው እግራቸው ደግሞ ሶስትና አራት ቀዶ ሕክምና ሊያስፈልገው ይችላል። ከፍ እያሉ ሲመጡ ደግሞ አብዛኛዎቹ ህፃናት ለመንቀሳቀስ የተሽከርካሪ ወንበርና ከራንች ድጋፍ ይፈልጋሉ።

ዶክተር ሳላዲን እንደሚሉት፤ የነርቭ ዘንግ ክፍት ዓይነቱና ደረጃው ይለያያል። አንዳንዱ ክፍተቱ አነስተኛ፤ ሌላኛው ደግሞ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶቹ አነስተኛ የሆነው ክፍተት ከተዘጋ በኋላ ሙሉ በሙሉ ጤናማ የሚሆኑበት ዕድል አለ። ሌሎቹ ደግሞ የነርቩ ዘንግ ክፍተቱ በጣም ሰፊ ይሆንና ከአዕምሮ እድገት ውስንነት አንስቶ ለተለያዩ የጤና ችግሮች ተጋልጠው ሙሉ በሙሉ በቤተሰብ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በየካቲት 12 ሆስፒታል በአብዛኛው ሕክምና የሚያገኙትም ድጋፍ የሚፈልጉት ናቸው።

በየካቲት 12 ሆስፒታል የነርቭ ዘንግ ክፍተት ቀዶ ሕክምና ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የነርቭ ሐኪሞች፣ የህፃናት ነርቭ ሐኪሞች፣ የሽንት ሐኪሞች፣ የአጥንት ሐኪሞች ቡድን አለ። በሆስፒታሉ በሚገኙ ሁለት የቀዶ ሕክምና ክፍሎች ውስጥ በሳምንት አራት በወር 16 ቀዶ ሕክምናዎች ይደረጋሉ። ነገር ግን የቀዶ ሕክምና አገልግሎቱ በጴጥሮስ፣ ዘውዲቱና አለርት ሆስታሎችም ይሰጣል። ይሁንና ከተጠቂዎቹ ቁጥር ከፍተኛነት አንፃር ይህን ሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር የሚመጣጠን አይደለም። ያሉትም ቢሆኑ አስፈላጊ የሕክምና ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ አሟልተዋል ማለት አይቻልም። በዚህ ዘርፍ ሕክምና የሚሰጡ ባለሞያዎች ቁጥርም በጣም ትንሽ ነው። በአሁኑ ጊዜ ይህን ሕክምና የሚሰጡ ባለሞያዎች 50 ብቻ ናቸው። ከዚህ አንፃር ገና ብዙ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ይህ የጤና ችግር በመንግሥት በኩል አስፈላጊውን ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ያለ አይመስልም። ከ100 ህፃናት ውስጥ ይህ የነርቭ ዘንግ ክፍተት ችግር ካላቸው ከ70 እስከ 80 ከመቶ ያህሉ የጭንቅላት ውስጥ ውሃ መጠራቀም ያጋጥማቸዋል። ከጭንቅላታቸው ውስጥ የተጠራቀመው ውሃ በትቦ አማካኝነት ነው የሚወጣው። ሆኖም ይህ ትቦ በመንግሥት በኩል በግዢ ቀርቦ አያውቅም። ሁሌም ቢሆን በርዳታ ድርጅቶች ላይ በመንጠልጠል ነው ቱቦው የሚቀርበው። አልፎ አልፎም ቱቦው ያልቃል። ያኔ ደግሞ ሕክምናው ይቋረጣል። ታካሚዎችም እንግልት ይደርስባቸዋል።

ሽንታቸውን መቆጣጠር ለማይችሉ የሚገባ ቱቦ / catheterization/ እንደ ልብ እየቀረበ አይደለም። የቀዶ ሕክምና ክፍሎቹ ለህፃናቱ የተመቹና የእነርሱን ፍላጎቱ ያሟሉ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። በሕክምና ሂደት ለቤተሰብ ወይም አስተማሚ መቆያ ቦታ አለመኖርና ሌሎችም የሕክምናው ተግዳሮቶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ችግሮች በደንብ ታይተው በመንግሥት በኩል ተገቢውን መፍትሔ ሊያገኙ ይገባል።

ይህ የነርቭ ዘንግ ክፍተት በህፃኑም ላይ ሆነ በወላጆች ላይ ከባድ ጫና የሚያስከትል ነው። ነገር ግን ችግሩን አስቀድሞ መከላከል ይቻላል። ፎሊክ አሲድ ከ70 ከመቶ በላይ በነርቭ ዘንግ የመጠቃት እድልን ይቀንሳል። ይህ ደግሞ በሕክምና ትልቁ ስኬትና ፎሊክ አሲድን በወሰዱና ባልወሰዱ ሴቶች መካከል ሰፊ ልዩነት እንዳለ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ በቅድሚያ በተቻለ አቅም የታቀደ እርግዝና ባሕል እንዲኖር ይበረታታል። ይህም ከእርግዝና ከሁለት ወር በፊትና እርግዝና ልክ እንደተከሰተ ፎሊክ አሲድንና ሌሎች በፎሊክ አሲድ የበለፀጉ ምግቦችን መመገብ ሊከሰት የሚችለውን የነርቭ ዘንግ ክፍተት አስቀድሞ ለመከላከል ያስችላልና መጠቀም ያስፈልጋል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የበለስ ማርማላት አምራቿ መውጫዎች

ማህሌት አብዱል

በትግራይ ክልል ሐውዜን ከተማ ነው የተወለደችው። ወላጅ አባቷ በሥራ ምክንያት ወደ ያኔዋ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ኤርትራ መዛወራቸውን ተከትሎ አብዛኛውን የትምህርት ዘመኗን በአስመራ ነው የተከታተለችው። የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሲከሰት እሷም ሆነች መላው ቤተሰቧ ወደ ትውልድ ቀያቸው ለመመለስ ተገደዱ።

የዛሬዋ የስኬት እንግዳችን ወይዘሮ ፀጋ ገብረኪዳን ከልጅነቷ ጀምሮ ፀሃፊ ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛ የመሆን ሕልም እንደነበራት ትናገራለች። ይህንን ሕልሟን ለማሳካት ስትልም ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳለች የኮምፒውተር ትምህርት ስልጠና ወስዳለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀችም በቀጥታ የግል ኮሌጅ ገብታ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች።

ዳሩ ግን ሕይወት እንዳሰበችው ቀላል አልነበረችምና በተማረችው ትምህርት ሥራ ማግኘት አልቻለችም። ከብዙ ልፋትና ጥረት በኋላ ማግኘት የቻለችው ሥራ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ በፅዳትና ተላላኪነት ተቀጥሮ ማገልገል ብቻ ነበር። እሱንም ቢሆን አልናቀቸውም፤ መሸጋገሪያ ይሆነኛል በሚል ተስፋ ሰንቃ ማገልገሏን ቀጠለች። በዚሁ ተቋም ውስጥ እያገለገለች ሳለ ግን የሕይወት መስመሯን ሙሉ ለሙሉ መቀየር የሚያስችል የስልጠና እድል አገኘች። ይህም በአንዲት የውጭ ዜጋ አማካኝነት ያገኘችው በበለስ ማርማላት መስራት የሚያስችል ክህሎት ነበር።

ከዚያ በፊት ግን በለስ በአካባቢያቸው ተወዳጅ የሆነ ፍራፍሬ ቢሆንም እሷም ሆነች ሌሎች ሰዎች የበሰለውን ልጠው ከመብላት ባሻገር በማርማላት መልኩ ተቀናብሮ ሊበላ እንደሚችል አታውቅም ነበር። ማርማላት ብቻም ሳይሆን ጁስና ወጥ መስራት እንደሚቻል እውቀት ቀሰመች። ይህ ስልጠና ደግሞ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ይመለከት የነበረውን ማንነቷን እንዳሰፋላት ታስረዳለች።

ከስልጠናው በኋላ ተቀጥራ ለመስራት ልቧ አልፈቀደምና ያገኘችውን ክህሎት በተግባር ለማዋል ቋርጣ ሥራዋን ለቀቀች። እናም ከወላጇቿ ባገኘችው አምስት ሺ ብር ለሥራ የሚያስፈልጋት ቁሳቁስ ገዛች፣ በተረፋት ቤት ተከራይታ የበለሱን ጭማቂ፣ ማርማላትና ወጥ ሰርታ በነጻ ቅመሱልኝ እያለች ለአካባቢዋ ሰዎች ሁሉ ማስተዋወቋን ጀመረች።

ጥቂቶች ምርቷን ቀምሰው ቢወዱትም፤ ምርቱ በተለይ በክረምት እንደልብ የሚገኝ በመሆኑ ምርቷ እንዳሰበችው ቶሎ ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም። ‹‹አንዳንዶቹ በጥሬው መብላት ስንችል ለምን በፋብሪካ የተቀነባበረ እንበላለን፤ እንደከብት ታሽጎ የቀረበ ቅጠል አንበላም›› የሚሉ አሉታዊ አስተያየቶች ይሰነዘሩ እንደነበርም ታስታውሳለች። እሷ ግን ራዕይዋ ካለችበት አስቸጋሪ ሁኔታ በላይ አሻግሮ የሚያይ በመሆኑ በአሉታዊ አስተያየቶቹ ተስፋ አልቆረጠችም፤ ይልቁንም ጆሮ ሳትሰጥ ምርቷን ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ማስተዋወቁን ተያያዘችው።

ሆኖም ምርቷን አምኖ የሚገዛ በማጣቷ ለኪሳራ ተዳረገች፤ ተመልሳም ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ገባች።የበለሱ ማርማላት ሰው እያወቀውና እየለመደው ሲሄድ ተቀባይነት ያገኛል የሚል ተስፋ ስለነበራት የተወሰነ ገንዘብ አጠራቅማ ተመልሳ ማምረቷን ቀጠለች። በኤግዚቢሽኖችና በየገበያው እየዞረች ምርቷን ለማስተዋወቅ ጥረት አደረገች።

ከሽያጩ የምታገኘው ትርፍ በጣም አነስተኛ በመሆኑ የቤት ኪራይ መክፈል እየተሳናት ከሁለትና ሶስት ጊዜ በላይ ወደ ቤቷ እየተመለሰች፤ መልሳ እየወጣች ለሰባት ዓመታት ቆየች። ሥራው ለብቻ መስራት ከባድ መሆኑን ተገነዘበች። እናም አራት አጋሮችን ጨመረችና አቅማን አጎለበተች።

ከሥራ አጋሮቿ ጋር በመሆን ሕጋዊ ፈቃድ አውጥተው ፤ የመስሪያ ቦታም ከከተማ አስተዳደሩ አግኝተው በስፋት ወደ ማምረት ገቡ፤ የማስተዋወቁንም ሥራ ተቀናጅተው ይሰሩ ስለነበረም ተቀባይነታቸው እያደገ መጣ።



ወይዘሮ ፀጋ ገብረኪዳን




ወይዘሮ ፀጋ ይህንን ማየቷ ይበልጥ ለመስራት አነሳሳት፤ ምርቶቿ ከከተማ አልፎ በአዲስ አበባ ሱፐርማርኬቶችና የዓለም ትልልቅ ገበያዎች ላይ ማግኘት ትመኝም ስለነበር፤ ለዚያ ይረዱኛል ያለቻቸውን የመንግሥትና የግለሰብ ቢሮዎች ሁሉ አንኳኳች። ልፋቷ ከንቱ አልቀረም፤ እንዳሰበችውም ለመጀመሪያ ጊዜ የበለስ ማርማላቱ ኢትዮጵያን ወክሎ ጣሊያን ገበያ ላይ ዘልቆ መግባት ቻለ፤ ጥሩ ተቀባይነትም አገኘ። እነ ወይዘሮ ጿጋ ሥራቸው እየሰፋ ሲሄድ አሁንም በእነሱ ብቻ የሚሰራ አለመሆኑን ተገነዘቡና 20 የሚደርሱ ወጣቶችን በጊዜያዊነት ቀጥረው እስከማምረት ደረሱ።

በለስ በትግራይ በስፋት የሚገኝ ቢሆንም፣ የሚመረተው ግን በባኅላዊ ዘዴና መሳሪያ በመሆኑ ቀጣይነት ባለው መልኩ የማርማላት ምርቱን በስፋት በአዲስ አበባም ሆነ በዓለም ገበያ ለማቅረብ አለመቻላቸውን ይረዳሉ።‹‹የፋይናንስ እጥረት ስለነበረብን የምንፈልጋቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች መግዛት አልቻልም›› የምትለው ወይዘሮ ፀጋ፤ ከአጋሮቿ ጋር በመመካከር ድርጅታቸውን ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የማሸጋገር ሕልም ሰንቀው ከሁለት ብድርና ቁጠባ ተቋማት አምስት መቶ ሺ ብር ተበደሩ።የጠርሙስ እጥረት ስለነበረባቸውም አክሲዮን ገዝተው በአካባቢያቸው ከሚገኝ ብርጭቆ ፋብሪካ ጋር ውል ፈፀሙ።

ይሁንና ሥራ ፈጣሪዋ ወይዘሮ ፀጋና ባልደረቦቿ ወደ ኢንዱስትሪ የማደግ ተስፋቸውን ከነጭራሹ የሚያጨልም ክስተት ገጠማቸው። ይኸውም በትግራይ የተቀሰቀሰው የሰሜኑ ጦርነት ነው፤ ‹‹በጦርነቱ ምክንያት ሼር የገዛንለት ብርጭቆ ፋብሪካ ሙሉ ለሙሉ ወደመ፤ የተበደርነውም ብር ጥቅም ላይ ሳናውለው አላግባብ ባከነ›› በማለት ቅስሟን የሰበረውንና ለኪሳራ የዳረጋትን አጋጣሚ ታስታውሳለች።ከሁሉ በፊት ሕይወትን ማዳን ይቀድማልና እሷም ሆነች አጋሮቿ ጦርነቱ እስከሚጠናቀቅ ያለሥራ ለመቀመጥ መገዳደቸውንም ትገልፃለች።

‹‹ ዋናው ሰላም ነው፤ ሰላም ካለ ሁሉንም እንደገና መመለስ ይቻላል›› የምትለው ወይዘሮ ፀጋ፣ እሷና አጋሮቿ ሃገር ስትረጋጋ እና በአካባቢያቸው የሰላም አየር መንፈስ ሲጀምር ያዘመመውን የንግድ ተቋማቸውን ዳግም ለማንሳት መከሩ፤ መክረው ብቻ አልቀሩም፤ ያለቻቸውን ጥሪት አሰባስበው ማምረታቸውን ቀጠሉ።

ልክ እንደ በፊቱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በእሷ መሪነት ምርታቸውን በየኤግዚቢሽኑና ሱፐር ማርኬቱ ማስተዋወቃቸውን ቀጠሉ።በተለይም የምርታቸውን ጣዕም ቀምሰው በሚገባ ያጣጣሙት የአካባቢው ሰዎች በመስሪያ ቦታቸው በመምጣት እንደሚገዟቸው ትናገራለች።

በአሁኑ ወቅት የእነ ወይዘሮ ፀጋን ጥረት የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ የገበያ ትስስር ፈጠረላቸው፤ በዚህም ምርታቸው አዲስ አበባ ከሚገኝ ሱፐርማርኬት ተቀባይነት ማግኘቱን ታስረዳለች።

እነ ወይዘሮ ጿጋ አስር ያህል ሰዎችን በጊዜያዊት በመቅጠር ሥራቸውን እያስፋፉ ይገኛሉ።ሥራው አሁንም በእጅ (በማኑዋል) የሚሰራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ባሰቡት መጠንና ጥራት ልክ ማምረት አለማቻላቸውን ወይዘሮ ጿጋ ትገልጻለች።

‹‹በለስ በተለይ በትግራይ በብዛት ይመረታል፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህንን ምርት እንደ ሃብት ቆጥረነው አናውቅም ነበር፤ እንደ ሜክሲኮ ያሉ ሃገራት ከራሳቸው አልፈው ለዓለም ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ እያገኙበት ነው›› የምትለው ወይዘሮ ጿጋ፤ በእጅ ያለ ወርቅ እንደመዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው ሁሉ ይህንን ሃብት በሚገባ ጥቅም ላይ ማዋል ያለመቻሉ ሁልጊዜም ቁጭት ይፈጥርብኛል ትላለች።

‹‹በለስን በማርማላት መልኩ የማቀነባበሩ ሥራ አድካሚ መሆኑን እያወቅሁ ስለገባሁበት ባጋጠሙኝ ችግሮች ሁሉ ተስፋ ሳልቆርጥ ነው የቆየሁት›› የምትለው ወይዘሮ ፀጋ፤ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ የለፋችበት የበለስ ማርማላት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ እውን እንደሚሆን፤ ለሃገርም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ገቢ የሚያስገኝ እንደሚሆን እርግጠኛ ነች። ለዚህም ቀን ከሌሊት እየሰራች ትገኛለች፤ በተለይም በምንም ማዳበሪያ ወይም ሰው ሰራሽ ግብዓት የማይመረት መሆኑም በዓለም ገበያ ተፈላጊ እንደሚሆን አትጠራጠርም።

ለዚህም ዋስትና የሰጣት ከዚህ ቀደም ምርቱ በጣሊያን ቀርቦ የተገኘው መልካምና አበረታች ግብረ መልስ እንደሆነ ትናገራለች። በሌላ በኩልም ለማምረት ምንም አይነት ጥሬ እቃ ከውጭ ማስመጣት የማይጠበቅ መሆኑም ከተሰራበት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሊያደርግ እንደሚችል ታምናለች።

‹‹ከቤቴ አጥር በሚገኝ ምርት ብቻ ማርማላቱ የሚመረት መሆኑ በዝቅተኛ ዋጋ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን የሚቻል ስለመሆኑ አልጠራጠርም›› ትላለች። ምርቱን በስፋት ማምረት ከተቻለ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለሚደረገው ሃገራዊ ጥረት አጋዥ እንደሚሆንም ትገልፃለች።

ከዚህ ባሻገር ከውጭ የሚገባውን ማርማላት የመተካት አቅም ያለው በመሆኑ ሃገሪቱ ማርማላት ከውጭ ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ በመታደግ ረገድ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ታስረዳለች። ‹‹ በአካባቢያችን ያለውን ምቹ እድልና ያለሥራ የተቀመጠ የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም ከራሳችን አልፈን ለሌሎችም ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ያስችለናል›› ስትልም ታመለክታለች። ‹‹ከአሁን በኋላም የቱንም አይነት አስቸጋሪ ሁኔታና ፈተና ቢያጋጥመን ወደ ኋላ እንደማንመለስ እርግጠኛ ነኝ›› ትላለች። አሁን ላይ ቀድሞ የነበሩት አሉታዊ አመለካከቶች መቀረፋቸውን ጠቅሳ፤ ማርማላቱ ከተመረተ የገበያ ችግር ያጋጥማል ብላ እንደማታስብ ትናገራለች።

በቅርቡ ምርቱ ለአንድ ሱፐርማርኬት እየቀረበ መሆኑን ጠቅሳ፣ ምርቱን በሌሎችም የንግድ ማዕከላት በስፋት ለማስገባት በዝግጅት ላይ መሆኗን ታስረዳለች። ከሁሉም በላይ ግን ራሱን የቻለ የበለስ ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ ለመገንባት መታቀዱንም ትናገራለች። ከማርማላት ጎን ለጎን ከበለስ የሚሰሩ የመዋቢያ ቁሳቁስ (ኮስሞቲክስ) ለመስራት ማሰቧን ጠቁማለች።ጥራቱን የጠበቀ የበለስ ምርት ወሳኝ በመሆኑ ለገበሬዎች ስልጠና በመስጠት ትስስሩን በማጠናከር ለሌሎች ማሳያ የሆነ ድርጅት እንዲኖራትም ትፈልጋለች።

በአሁኑ ወቅት መንግስት ከሰጣቸው የማምረቻ ሼድ በተጨማሪ፤ ማርማላቱን ለማምረት የሚያስችሉ ባኅላዊ መሳሪያዎችና ቁጥራቸው ከ500 ያላቀ የተመረቱ ማርማላታዎችንና በጥሬው ያለውን ጥሬ ገንዘብ ጨምሮ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋ ካፒታል እንዳላቸው ትጠቁማለች። ይሁንና ካፒታላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ከአጋሮቿ ጋር ቀን ከሌት እየተጋች መሆኑንም ታመለክታለች።

ይህ ሕልሟ እንዲሳካ ግን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ትጠቁማለች።በተለይ የቴክኖሎጂ አማራጮች፤ የፋይናንስ ተቋማት እና የመንግሥት አካላት በለስ ለሃገር ያለውን ፋይዳ ተገንዝበው የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጠይቃለች።

# ተናጋሪው ዶሴ

## አደራ መብላት...

**ሰሚራ በርሀ**

ገመቹ ተስፋዬ፣ ትውልድና እድገቱ በኦሮሚያ ክልል አሰላ ከተማ ነው፤ ቤተሰቦቹን ለመደገፍ የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ገንዘብ ለማግኘት ይሞክር ነበር። ነገር ግን በዚያ የሚሰራቸው ሥራዎች በቂ ገቢ ሊያመጡለት አልቻሉም። ገመቹ፣ ከዚህ በፊት አብሮት በመኪና ማጠብ ይሰራ የነበረ ጓደኛው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሥራ ላይ መሆኑን ያውቃል ። በዚያ የተሻለ ሥራ እና ጥሩ ክፍያ ይከፈለኛል የሚል ሀሳብም ስላለው ከብዙ ጊዜ ማመንታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሥራ ማፈላለጉን ጀመረ ።

አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ከጓደኞቹ ጋር በመኖር የተለያዩ ሥራዎችን ሞከሯል ። የተለያዩ የቀን ሥራዎችን ፣ እቃዎችን ለሰው ማድረስ እና ጓደኞቹ የሚውሉበት ቦታ በመዋል የቀን ገቢ ለማግኘት የተለያዩ አማራጭ መንገዶችን ይሞክራል ። አሁን የሚሰራበትን የቤተልሄም ሆቴልና አፓርትመንት ሥራ ያገኘው በአጋጣሚ ነበር ። ቂርቆስ ክፍለከተማ ወረዳ 03 ልዩ ስሙ ጨርቆስ ሰፈር አካባቢ እቃ ለማድረስ በሚሄድበት ጊዜ በተቋሙ በር ላይ የተለጠፈውን ማስታወቂያ በመመልከት የተሻለ ሥራ ለማግኘት እድሉን ይሞክራል።

ወደ ሥራው ለመግባትም አፓርትመንቱ ኃላፊዎች ያስቀመጡትን መመዘኛዎች ካሟላ በኋላ ተያዥ የሚለውን የቅርብ ጓደኛውን በማምጣት የሥራ ውሉን በመዋዋል ሥራውን ይጀምራል ።

ገመቹ ወደ አፓርትምንቱ አዲስ ሥራ ከጀመረ በኋላ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በአፓርትምንቱ ጊቢ ውስጥ ነው ። ከጥበቃ ባሻገር በአፓርትመንቱ የማረፊያ ክፍል ፈልገው የሚመጡ ሰዎች ለቀናት አንዳንዴም ሳምንታት የሚቆዩ በመሆናቸው መልካም የሆነ ተግባቦት አለው ። በሚሰራበት የጥበቃ ሥራ ውስጥ መኪና በማጠብ ፣ በአፓርትመንቱ በእንግድነት ለሚመጡ ሰዎች በመላላክ ተጨማሪ ገቢ ያገኛል ። ቆይታቸውን ጨርሰው የሚሄዱ የአፓርትመንቱ ተጠቃሚዎችም ገመቹ እንደማበረታቻ ጉርሻ (TIP) ሰጥተውት ይሄዳሉ ። ገመቹ በዚህ ሥራ ቦታ ሁለት ዓመት ያክል ጊዜን ቆይቷል ። ይህንን ሥራ ከማግኘቱ በፊት ሌሎች በርካታ ሥራዎችንም ለመስራት እና ሕይወቱን ለመሻሻል ሞክሯል ።

አብረውት የሚኖሩ የገመቹ ጓደኞች በተለያየ የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ናቸው ። ስንታየሁ አብረውት ከሚኖሩ ጓደኞቹ አንዱ ሲሆን የቀን ሥራዎችን በመስራት ተባራሪ እቃዎችን በመሸጥ ኑሯቸውን ይገፋሉ ።

ገመቹ የሚሰራበት ድርጅት ውስጥ በአፓርትመንቱ የተወሰኑ ቀናት የሚቆዩ ተጠቃሚዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ፣ እቃ የሚያመላልሱ ከአንድም ሁለት መኪናዎች በግቢው ውስጥ ይገኛሉ ። ገመቹ የጥበቃ ሥራው እነዚህን የአፓርትመንቱ ንብረቶች መጠበቅን ያጠቃልላል ። የእረፍት ጊዜውን ከእነዚህ ጓደኞቹ ጋር እነሱ የሚሰሯቸውን የተለያዩ ጥቃቅን የድለላ ስራዎችን ከሚሰሩ ጓደኞቹ ጋር ያሳልፋል ። ነገር ግን ገመቹ የሚያሳልፈው የሥራ ጊዜ ቀኑን ሙሉ በአፓርትመንት ውስጥ የሚውል በመሆኑ ከጓደኞቹ ጋር የሚገናኘው ከመሸ በኋላ ወደቤቱ ሲመለስ ነው። ገመቹ ከቀን ፈረቃ ባለፈ ምሽት ላይ አዳሪ የሚሆንባቸው የሥራ ቀናት አሉ። በአፓርትመንቱ ውስጥ በሚያድርበት ጊዜ ጊቢው ውስጥ የሚያድሩ የድርጅቱ መኪኖችን መጠበቅ ይጠበቅበታል ።

**ክፉ አመል**

አዳሪ በሚሆንበት ጊዜ የተወሰኑ ሰዓታትን ከጓደኞቹ ጋር በአፓርትመንቱ አካባቢ ያሳልፋሉ ። ታዲያ ከጓደኞቹ አንዱ ስንታየሁ አድማሱ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት በሚሰራበት የታክሲ ተራ አካባቢ ስልክ በመስረቅ በስርቆት ወንጀል ተጠርጥሮ የፍርድ ጊዜ በማረሚያ ቤት ውስጥ ጊዜውን ጨርሶ የወጣ ነው ።

ታዲያ ስንታየሁ ገመቹ የሚውልበት የሥራ ቦታ ትልቅ እና በጣም ጥሩ ነው የሚል አስተያየት ያቀርብለታል። በተደጋጋሚም በአፓርትመንቱ ውስጥ ለመጓጓዣነት የሚያገለግለውን መኪና ላይ አይኑን በመጣሉ ንብረቱን የራሱ ለማድረግ መጓጓቱ ለገመቹም ይህንን ሀሳብ ማጋራቱ አልቀረም። ነገር ግን



ገመቹ ይህንን ጉዳት አስቦት የማያውቀው በመሆኑ ለመስማማት ፍቃደኛ አልነበረም ። ነገር ግን በአነስተኛ ደሞዝ ተቀጥሮ ለሚሰራው ገመቹ ጓደኛው የሚሰጠው ምክንያት መኪናው ቢሸጥ ሊያገኝ የሚችለውን ገንዘብ እንዲጓጓ አድርጎታል ።

በእለቱም አዳሪ ተረኛ የነበረው ገመቹ አብሮት የሚኖረው ስንታየሁ ሌላ ጓደኛ የሆነው ደስታ ከአሰላ ከተማ መጥቶ አብሯቸው ይገኛል። ታዲያ ገመቹ የሥራ ቦታ ላይ የሚገኘውን መኪና ስርቆት ሀሳብ በተመለከተ የቀረበውን ሀሳብ ይበልጥ ግልጽ በማድረግ እና ሀሳቡን በመንደፍ ለገመቹ የሰውን ንብረት መውሰድ ቀላል ሆኖ እንዲታየሁ አደረገ። በሀሳቡ በመስማማት የሚመጡበትን ሰዓት ከወሰዱት በኋላ ወዴት እንደሚሄዱ በማስረዳት ገመቹ ወደ ሥራ ቦታው ሰዓቱን ጠብቆ በቦታው ተገኘ ።

**ጥፋት በሕብረት**

ሔለን ወደ ቤተልሄም አፓርትመንት የሚመጡ ተጠቃሚዎችን ከሚመጡበት ቦታ በመቀበል በዚያ በሚቆዩበት ጊዜ የሚፈልጉትን ነገር በማሟላት ሥራውን በቅርበት የምትቆጣጠር ናት ። በመሆኑም ደንበኞቹ የሚፈልጉትን አገልግሎት ከተሟላ በኋላ የምሽት ጊዜዋን ወደቤቷ በመሄድ ታሳልፋለች ። ገመቹ የአዳሪ ተረኛ በሆነበት በዚህ ቀን በቀጠሯቸው መሰረት ከለሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ የጉዳዩ ጠንሳሽ የሆነው ስንታየሁ እና ጓደኛው ደስታ በመሆን በቦታው ተገኙ ። ይህ ለገመቹ እና ለአባሪዎቹ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላቸዋል ። ገመቹ የአፓርትመንቱን በር ከከፈተ በኋላ በቅርቡ አብሯቸው መኖር የጀመረው ደስታ ወደመኪናው በመጠጋት እና መኪናው በቀስታ በመንዳት መኪናውን ይዞት ወጣ። በአደራ መልክ የተሰጠውን ኃላፊነት ያልተወጣው ገመቹም በዚህ መኪና ውስጥ በጋራ በመሆን መኪናውን ይዘው ወደ ማምለጥ አመሩ ።

**የወንጀሉ ዝርዝር**

በ2013 ዓ.ም ነሀሴ ወር ቀን 11 በግምት ከለሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ በቂርቆስ ክፍለከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው ጨርቆስ ቤተክርስቲያን ተብሎ የሚጠራው አከባቢ ንብረትነቱ የቤተልሄም ሆቴልና አፓርትመንት ውስጥ ተጠርጣሪው ገመቹ ካልተያዙት አባሪዎቻቸው ጋር በመሆን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3 – ኤ79876 ሀይውንዳይ ተሽከርካሪ ከቆመበት ቦታ ተሰርቆ ተወሰደ። የመኪናውን መሰረቅ የተመለከቱት የአፓርትመንቱ ሰራተኞች ወደ ፖሊስ በመቅረብ ቅሬታቸውን አቀረቡ። ፖሊስ የደረሰውን መረጃ በመከተል ምርመራው ማድረግ ጀመረ። ምርመራውን ተጠርጣሪ የሆነው ገመቹ ውሉን በሚፈርምበት ጊዜ ባስቀመጠው አድራሻ መሰረት ፍለጋውን ማድረግ ቀጠለ ። ፖሊስ በዚህ ማጣራት ውስጥ አንደኛ ተጠርጣሪ የሆነውን ገመቹን በዱከም ከተማ በቁጥጥር ስር ካዋለው በኋላ አግኝቶ በማጣራት ከአዲስ አበባ መንገዶች አስተዳደር መኪናው የተመዘገበበትን ባለቤት ትክክለኛ አድራሻ የቤተልሄም ሆቴልና አፓርትመንት ሰራተኛ የሆነችው ሔለን ስም የተመዘገበበ መሆኑን አረጋግጦ ማስረጃ በመያዝ ተጠርጣሪ ያላቸውን በስርቆት የተሳተፉ ግለሰቦች የሚጣቀሙባቸው የባንክ ሒሳብ ሕጉን በተከተለ መሰረት የእግድ ትእዛዝ በማውጣት እና ተጠርጣሪው ያደረጋቸውን የስልክ ልውውጦች ከኢትዮ ቴሌኮም መረጃ በመውሰድ የማጣራት ሥራውን አድርጓል ።

በመኪና ስርቆት የተሳተፉት ተጠርጣሪው ገመቹ እና አባሪዎቹ ስንታየሁ እና ደስታ መኪናው ከሰረቁ በኋላ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር የሚፈጀውን ገንዘብ ባነሰ ገንዘብ በመቶሺዎች በመሸጥ እና ገንዘቡን መከፋፈላቸውን ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪዎች ከሰጡት ቃል ማረጋገጥ ችሏል ። በቅሬታው መሰረት ፖሊስ ባደረገው ምርመራና ማጣራት አንደኛ ተጠርጣሪ በሰጠው ጥቆማ ተሽከርካሪው ቀን 23 ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ዱከም ከተማ የፊትና የኋላ ሰሌዳው እንዲሁም ሶስተኛ ወገን እንዲሁም ቦሎ ተነስቶ ነገር ግን በመኪናው የሞተር ቁጥር ከአንድ ዓመት በኋላ መኪናው ሊገኝ ችሏል ። ተሽከርካሪው ሲገኝ የፊትና የኋላ ሰሌዳው እንዲሁም ቦሎና ሶስተኛ ወገን ያልተገኘ በመሆኑ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በኤግዚቢትነት ተይዞ እንዲቆይ ተደርጓል ። ፖሊስ ባደረገው ማጣራት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በማጠናከር በመኪና ወንጀል ስርቆት ላይ የተሳተፉ አንደኛ ተከሳሽ ገመቹ ተስፋዬ እና ሁለተኛ ተከሳሽ ደስታ አበራ ጥፋተኛ መሆናቸውን አረጋግጧል ።

የውሳኔ ሒደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በኤግዚቢትነት የተያዘውን ተሽከርካሪ በስሟ የተመዘገበው ሔለን በድጋሚ እንዲረጋገጥ በማድረግ ንብረቱ እንዲመ ለስላቸው ጥያቄ በማቅረብ ተሽከርካሪውን መልሰው ማግኘት ችለዋል ።

**ውሳኔ**

አንደኛ ተከሳሽ ገመቹ ተስፋዬ እና ሁለተኛ ተከሳሽ ደስታ አበራ በተከሰሱበት የመኪና ስርቆት ወንጀል የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር ዘጠኝ ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስና ሰማስረጃ ከሕግ ጋር አገናዝቦ አንደኛ ተከሳሽ ገመቹ ተስፋዬን በ10 ዓመት ጽኑ እስራት ፣ ሁለተኛ ተከሳሽ ደስታን አበራን በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት ይቀጡ ሲል ውሳኔውን አስተላልፏል ።

# ዕውቀት ወይስ ገንዘብ?

**ዋለልኝ አየለ**

ይህ ክርክር እንደ ዋዛ አከራካሪ ሆኖ ቀረ እኮ! የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እያለን የክርክር ልምድ ለማዳበር በክፍል ውስጥ ከሚሰጡ አከራካሪ ጉዳዮች አንዱ ነበር። ይህ ርዕስ ሲሰጥ ገንዘብ ይበልጣል ብሎ መከራከር አስቸጋሪ ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ በነበረ የልጅነት አመለካከት ገንዘብ ይበልጣል ብሎ መከራከር ሰነፍ ተማሪ ያስመስላል የሚል ስጋት ነበር። መምህሮቻችን አዕምሯችን ላይ የገነቡት ዕውቀት ይበልጣል የሚለው ስለሆነ፤ ዕውቀት ይበልጣል ብሎ መከራከር የጎበዝ ተማሪ ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ብዙ ሰዎች ይህን ክርክር የሞኝነት ክርክር አድርገውት፣ ያኔ የነበራቸውን አቋም ሲስቁበትና ሲፈርዱበት ይሰማል። ‹‹ገንዘብ ሆይ ይቅር በለኝ! ዕውቀት ይበልጣል ብዬ የተከራከርኩት ያኔ ልጅነት ይዞኝ ነው!›› እያሉ በማህበራዊ ገጾች ላይ የሚቀልዱም ነበሩ። በየመድረኩ፣ በየሚዲያውና በየአጋጣሚው ዕውቀት ዋጋ እንዳጣ ተደርጎ ይነገራል።

ወደ ዋናው የትዝብት ጉዳዬ ስገባ፤ ‹‹ዕውቀት ይበልጣል ወይስ ገንዘብ?›› የሚለው ክርክር ኋላቀር ክርክር ይመስለኛል። የሚያሳዝነው ደግሞ በተለይም በዚህ ዘመን ከአከራካሪነትም አልፎ ገንዘብ ይበልጣል የሚል ስምምነት ላይ የተደረሰ ይመስላል። አንድ ሰው ‹‹ይሄ ደግሞ ምኑ ያከራክራል?›› ካለ፤ ምናልባትም ገንዘብ ይበልጣል እያለ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በተደጋጋሚ እየተነገረ ያለው ትርክት ‹‹ዕውቀት ዋጋ አጣ! ዕውቀት ምንም አይጠቅምም! ዋናው ገንዘብ ነው!›› የሚል በመሆኑ ነው።

ለመሆኑ ዕውቀት ምንድነው?

ትልቁን የትርክት ስህተት የፈጠረው ዕውቀትን በትምህርት ደረጃዎች መለካታችን ነው። ብዙ ጊዜ እንደ ማሳያ የሚጠቀሰውም፤ መምህራን፣ ሐኪሞች እና የመሳሰሉ ባለሙያዎች ድሃ ናቸው በሚል ነው። የ10ኛ ክፍል ውጤት ያልመጣላቸው፣ ወይም በተለያየ ምክንያት ትምህርት አቋርጠው ነጋዴ የሆኑ የተሻለ የገንዘብ አቅም አላቸው በሚል ነው።

በተለይም ብዙ ጊዜ እንደ ማሳያ የሚያገለግለው መምህራን ዝቅተኛ ኑሮ ነው የሚኖሩት፣ እስከ ፒ ኤች ዲ እና ፕሮፌሰርነት የደረሱ ሰዎች ይቸገራሉ በሚል ነው። ከዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች ሥራ አጥተው ምንም የትምህርት ዝግጅት የማይፈልጉ ልማዳዊ የአካባቢ ሥራዎችን እየሰሩ ነው በሚል ነው።

እዚህ ላይ ይመስለኛል ስህተቱ የተፈጠረው። ተማርን እንጂ አላወቅንም እኮ! ከ16 ዓመታት በላይ ትምህርት ቤት ቆየን እንጂ ምንም ጠብ ያደረግነው ነገር የለም እኮ። ከዩኒቨርሲቲ በግብርና የተመረቀ ሰው ለሺህ ዘመናት የኖረውን ልማዳዊ የግብርና ዘዴ አልቀየረውም። እስከ ፒ ኤች ዲ ድረስ ተምሮ ከ20 ምናምን ዓመታት በላይ ያስተማረ ሰው ከንድፈ ሃሳብ የዘለለ ጠብ ያስደረገው ነገር የለውም። ከፍተኛ በጀት ተመድቦላቸው በሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰሩ የምርምር ሥራዎች መደርደሪያ ከማሞቅ ያለፈ ጠብ ያደረጉት ነገር የለም፤ ችግር ፈቺ መሆን አልቻሉም።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ነው ገንዘብ ዕውቀትን ይበልጣል የምንለው? ሲጀመር ዕውቀትን የት አይተነው? ዕውቀት ቢኖረን ኖሮ እንዲህ ድሃ እንሆን ነበር ወይ? ለመሆኑ ተምረናል ወይ?

‹‹መማር›› የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በሦስት መሠረታዊ ነገሮች ላይ ይወድቃል። ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት (attitudes) ናቸው። በልማዳዊ አገላለጽ ግን ሦስቱንም ‹‹ዕውቀት›› ብሎ የመግለጽ ልማድ አለ። ክህሎትም ጥሩ አመለካከትም ያለው ሰው ‹‹አዋቂ›› ሊባል ይችላል። ስለዚህ ዕውቀት በሚለው ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ያም ሆኖ ግን ለየብቻ እንያቸው።

ዕውቀት ማለት ቃሉ ራሱ እንደሚያመለክተው አንድን ነገር ማወቅ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ደን ለምን ይጠቅማል? ቢባል፤ የአየር ንብረት መዛባትን ለመጠበቅ፣ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል... ምናምን እያለ ማንም ሰው ሊናገር ይችላል። ይሄ ዕውቀት ነው። ክህሎት ደግሞ ችግኝ መትከል፣ መኮትኮት፣ ውሃ ማጠጣት መቻል ነው። ይሄ ቀላል ስለሆነ ማንም ሊያደርገው ይችላል። ብቻ ግን ክህሎት ማለት አንድን ነገር ማድረግ መቻል ነው።

ሦስተኛው እና ዋናው፣ የአንድ ሰው የመሰልጠንና የመብሰል መለያ የሆነው፣ የአዋቂነት ዋና መለያ ነው የሚባለው አመለካከት (Attitude) ነው። በቅንፍ ውስጥ የእንግሊዘኛውን ቃል የተጠቀምኩት በአማርኛ አሻሚ ቃላት ሊኖሩት ስለሚችል ነው። አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ምናልባትም ቅንነት ልንለው እንችላለን።

ለምሳሌ፤ የደንን ጥቅም ማወቅ ዕውቀት ነው ብለናል፤ ዛፍ መትከልና መንከባከብ ክህሎት ነው ብለናል። የዚህ ሁሉ ጠቅላዩ ግን አመለካከት ወይም ቅንነት ነው። ዛፍ እንዳይቆረጥ ማድረግ፣ ሰዎች ዛፍ ሲቆርጡ መከልከልና ለሚመለከተው ማሳወቅ የመሳሰሉት ይሆናሉ።

አመለካከት (Attitude) አሳቢነትን የሚያመለክት ነው። ክፉ ደጉን የሚለይ፣ ለህሊና የሚኖር፣ ምን ቢደረግ ምን ሊገኝ እንደሚችል፣ ምን ስህተት ሲሰራ ምን ችግር ሊከሰት እንደሚችል የሚረዳ ማለት ነው። የሚሆኑ ነገሮችን አይቶ፣ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ማገናዘብ የሚችል ማለት ነው። በጥንቆላ ወይም በአስማት ሳይሆን መሬት ላይ ያሉ ነገሮችን አይቶ ነገ የሚሆነውን ነገር መገመት የሚችል ማለት ነው። የምክንያት ሰው የሆነ ማለት ነው።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ የተማርን ነን ወይ?

አብዛኞቻችን አላዋቂነታችንን በትምህርት ወረቀቶች ሸፍነን ‹‹ከዚህ ዩኒቨርሲቲ የተመረቅኩ ነኝ፣ ይህን ትምህርት የተማርኩ ነኝ፣ ይህን ያህል ዲግሪ ያለኝ ነኝ›› እንላለን እንጂ ትምህርቱ ግን ከላያችን ላይ አይታይም። መጸዳጃ ቤት ውስጥ ውሃ መድፋት እንዳለበት ማሳሰቢያ የሚለጠፍለት ሰው የተማረ ነው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም።

ገንዘብ ያላቸው ሰዎች የበለጡን ዕውቀት ስላላቸው ነው። የሆነ ነገር የማድረግ ዕውቀት አላቸው ማለት ነው። እኔ ጋዜጠኛ ነኝ። አንድ ጫማ የሚያጸዳ (ሊስትሮ) በገንዘብ ቢበልጠኝ፤ ይህ ሰው ከእኔ የተሻለ ዕውቀት ያለው ሰው ነው ማለት ነው። ለምን?

ጫማ ማጽዳት ይችልበታል፣ ጫማ ማጽዳትን ሥራዬ ብሎና በሥራ ክቡርነት አምኖ፣ የስንቱን ሰው ግልምጫ ችሎ እየሰራ ነው። በጠዋት ሥራው ላይ ተቀምጦ ፀሐይና ዝናብ ሳይበግረው እየሰራ ነው። የቁጠባ ልምድ ገብቶት እየቆጠበ ነው። ጫማ በማጽዳት ገንዘብ እንደሚገኝ አውቋል፣ አስፈላጊ ነገሮችን አሟልቶ ጫማ ማጽዳት ችሎበታል፣ ሥራ ክቡር መሆኑን የሚያምን የሰለጠነ ስነ ልቦና ገንብቷል። ይህ ጫማ የሚያጸዳ ሰው እኔን ቢበልጠኝ፤ የበለጠኝ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በዕውቀቱ ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ገንዘብ ነው ወይስ ዕውቀት ነው የበለጠ? ዕውቀት ነው የበለጠ! አንድ ሰው ‹‹ገንዘብ ነው የሚበልጥ›› ማለት የሚችለው ምናልባትም እጅና እግሩን አጣጥፎ ተቀምጦ በእርዳታ የሚኖር ከሆነ ብቻ ነው። ተሰርቶ የሚገኝ ገንዘብ የተገኘው በዕውቀት ነው።

ሌላው ዕውቀት የሚበልጥበት ምክንያት ገንዘብ ማስገኘቱ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ስነ ልቦና መገንባት የሚያስችል መሆኑ ነው። ገንዘብን ብቻ ግብ አያደርግም። ለምሳሌ፤ ፈላስፎች ማማረር እና ማለቃቀስ አይወዱም። ‹‹ይሄም የሕይወትና የኑሮ አይነት ነው›› ብለው በነፃነት ይኖራሉ። ዕውቀት ድሃ ሆኖ እንኳን በሰላምና በነፃነት ለመኖር ይጠቅማል ማለት ነው።

ከምንም በላይ ግን ገንዘብ የሚገኘው በዕውቀት ነውና ዕውቀት ይበልጣል፤ የትምህርት ደረጃዎቻችንን የዕውቀት ማሳያ በማድረግ ‹‹የተማሩት ድሃ ናቸው›› ማለት ስህተት ነው። ትምህርታችን አዋቂ ያላደረገን መሆኑ ልብ መባል አለበት!

## ዓለም አቀፍ

# የደቡብ ኮሪያ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት እንዲከሰሱ ጥያቄ ቀረበ

የደቡብ ኮሪያ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር እና ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሃን ዳክ-ሱን እንዲከሰሱ ጥያቄ አቀረቡ።ፓርላማው ወታደራዊ ህግ በመደንገግ ከስልጣን የተነሱትን የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮልን ለመክሰስ ድምጽ ከሰጠ ሁለት ሳምንታት እንኳን ሳይሞላ ነው የአሁኑ ክስ የቀረበው።

ጥያቄው የቀረበው ሃን በዋነኛው ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ዲፒ) የተጠቆሙት የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት ዳኞችን ለመሾም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው።"ሃን እራሱን ያቀረበው የአማጺ መሪ አድርጎ እንጂ እንደ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት አይደለም" ሲሉ የዲፒ ፓርቲው ፓርክ ቻን ዴይ ሐሙስ ዕለት ተናግረዋል።

ሃን ከጥቂት ሳምንታት በፊት የወጣውን የዩን ወታደራዊ ህግ የማስፈን ሙከራን ደግፈዋል ሲል ፓርቲው ከሷል። ህጉን ባለመቃወማቸው ሃን ቀደም ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል።ሃን ለአጭር ጊዜ የቆየውን ወታደራዊ ህግ ላይ ልዩ ምርመራ እንዲደረግ ፓርቲው ያቀረበውን ሃሳብ ጨምሮ በተቃዋሚ ፓርቲ የቀረቡ በርካታ ሃሳቦችን ውድቅ አድርገዋል ተብሏል።

የቀረበው ክስ ላይ በሚቀጥሉት ከ24 እስከ 72 ሰዓታት ውስጥ ድምጽ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ከ300 የፓርላማ አባላት 151ዱ ከደገፉት ተግባራዊ ይደረጋል። ተቃዋሚው ዴሞክራቲክ ፓርቲ ከሀገሪቱ 300 የፓርላማ መቀመጫዎች 170ውን ይዟል። ሁሉም የተቃዋሚው ፓርቲዎች ደግሞ 192 መቀመጫዎችን ይዘዋል። ሃን የሀገሪቱ ተጠባቂ ፕሬዚዳንት በሚሆኑበት ወቅት በመንገዳቸው ላይ እንደማይቆሙ እና ህጎችን ያለምንም ተቃውሞ እንዲፀድቁ ይፈቅዳሉ የሚል ተስፋን ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ሰንቀው ነበር። ይልቁንም በሃሳባቸው ጸንተው የፖለቲካ ውዝግቡን አባብሰውታል።

ሃን ማክሰኞ ዕለት የምክር ቤት ስብሰባ ቢያደርጉም ልዩ ኮሚቴ በወታደራዊ ህጉ እና በቀዳማዊት እመቤት ኪም ኪዮን ሂ ላይ የሙስና ውንጀላዎችን እንዲመረምር ተቃዋሚዎች ያቀረቡትን ሃሳቦች ሳይመለከቱ አጠናቀዋል። ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች መግባባት ላይ እንዲደርሱ ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት በሚል አጀንዳው ላይ አለመወያየታቸውን ገልጸዋል።

የዴሞክራቲክ ፓርቲው ፓርክ ቻን-ዴይ ግን "ጊዜን በመግዛት እና ችግሩን ለማራዘም እየተደረገ ነው" ሲሉ ነቅፈውታል።"በታሪክ ውስጥ አሳፋሪ ሥራ እንደሠራ፣ እንደ የአመጽ መሪ እና የዩን ሱክ ዮል አሻንጉሊት ወይስ በታማኝነት የሕዝብ አገልጋይ መሆኑን የሚለውን አማራጭ የመወሰን የጠቅላይ ሚኒስትር ሃን ዳክ ሱ ውሳኔ ነው" ሲሉ ፓርክ በቴሌቪዥን በተላለፈው የፓርቲው ስብሰባ ላይ ተናግረዋል።

ሃን ሐሙስ ዕለት በተቃዋሚዎች የሚመራው ብሔራዊ ምክር ቤት ለህገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን ሦስቱን ዳኞች ተቃዋሚ ፓርቲዎች መግባባት ላይ ካልደረሱ አልሾምም ብለዋል። "ሃን ዳክ ሱ ህገ መንግሥቱን ለመከላከል ብቃትም ሆነ ፍላጎት እንደሌለው ግልጽ ሆኗል" በማለት ተቃዋሚዎች የክስ ጥያቄውን "በፍጥነት" እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል።

ሃን አባል የሆኑበት ገዢው ፒፕል ፓወር ፓርቲ የተቃዋሚዎች ዛቻ በሃን "ህጋዊ ስልጣን" ላይ ጣልቃ ገብቷል ብሏል። የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት



ሃን ዳክ-ሱን

ከፍተኛ ባለስልጣን በበኩላቸው ዛቻውን "እጅግ በጣም የሚያሳዝን" ሲሉ ተችተዋል። ዮን በዚህ ወር መጀመሪያ ከስልጣን ከተነሱ በኋላ ነበር ሃን ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሆነው የተሾሙት። ህግ አውጭዎች ሃን እንዲከሰሱ ድምጽ ከሰጡ የፋይናንስ ሚኒስትር ቾይ ሳንግ-ሞክ ቦታውን የሚይዙ ይሆናል።

ሀገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት ባለችበት ወቅት የመጣው አዲሱ ጉዳይ የሴኡል ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ዩን ከስልጣን በቋሚነት መታገድ አለባቸው በሚለው ላይ እየተወያየ ባለበት ወቅት ነው። ፍርድ ቤቱ በዚህ ሳምንት መጨረሻ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ፊት ችሎቱ ይሰየማል ተብሎ ይጠበቃል። በችሎቱ ላይ ዩን ስለመገኘታቸው ግልጽ ባይሆንም ተቃዋሚዎች ግን በፍርድ ቤት ችሎት ወቅት ዮን በቋሚነት ስልጣን ከመያዝ እንዲታገዱ መጠየቃቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ቃል ገብተዋል።

ዩን ሀገሪቱን በወታደራዊ ህግ ስር ለማስተዳደር ያልተሳካ ሙከራ ፈጽመዋል በሚል ምርመራ እየተደረገባቸው ነው። በአካል እንዲቀርቡ የቀረበላቸውን ተደጋጋሚ ጥሪ ለመቀበል ፍቃደኛ ያልሆኑ ሲሆን፤ በዚሁ አቋማቸው የሚቀጥሉ ከሆነ መርማሪዎች የእስር ማዘዣ ሊያወጡ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል። የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስትር ኪም ዮንግ-ህዩን፣ የቀድሞ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ሊ ሳንግሚን እና የጦር ኃይል አዛዥ ፓርክ አን-ሱን ጨምሮ በርካታ ከፍተኛ ባለስልጣናትም ምርመራ ተከፍቶባቸዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# የምስጋና ኃይል

አስናቀ ፀጋዬ

አንዳንዴ እኮ ጎዶሎህ ብዙ ይሆናል። ያስጨነቀህ ነገር የማይገፋ ሊመስልህም ይችላል። ኑሮ ያሳስብሃል። የቤተሰብ ጉዳይ ሰላም ይነሳሃል። የሀገር ጉዳይ ያስጨንቅሃል። ብቻ ብዙ ነገር ይረብሽሃል። ማን የማይጨንቀው አለ ብለህ ነው። ማን የማያሳብ አለ? ሁሉም ያስባል። ሃሳብና ጭንቀት የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ማንኛውም ጤናማ የሆነ ሰው በሚገጥሙት የተለያዩ ችግሮች ምክንያት ያስባል፤ ይጨነቃል። ልዩነቱ ግን ሁሉም ሰው እኩል አያስብም፤ እኩል አይጨነቀም። አንዳንዱ አብዝቶ ይጨነቃል። ሌላው ደግሞ ብዙ አይጨነቅም። አንዱ ከመጠን በላይ ሃሳብ ይገባዋል። ሌላው ብዙ አያስብም።

ስለዚህ ሃሳብና ጭንቀት እንደየሰው ባህሪ፣ ችግሮችን የመጋፈጥና ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም ይወሰናል። ምንም እንኳን ሃሳብና ጭንቀት የሰዎች ባህሪ ቢሆንም ታዲያ ‹‹ሲበዛ በሽታ ነው›› ይላሉ የአእምሮ ሕክምና ባለሞያዎች። ስለሆነም አብዝቶ ማሰብንና መጨነቅን እንዴት ማቆም ይቻላል? አብዝቶ ማሰብና መጨነቅ የብዙ ሰዎች ችግር ነው። ሰዎች ነብስ ካወቁ ጀምሮ እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ማሰብና መጨነቅ እንደጥላ የሚከተላቸው ባህሪ ነው።

መጠኑ ይለያይ እንጂ አብዝቶ የማያስብና የማይጨነቅ ሰው የለም። ማሰብ መልካም ነገር ነው፤ ሕይወትንም ይቀይራል። ሲበዛ ነው መጥፎነቱ። ማሰብ ከበዛ እንቅልፍ የሚባል ነገር የለም። በዚህ ምክንያት አንዳንዴ ሰዎች የሚችሉትን ሁሉ መሥራት አይችሉም። ወይም ብዙ ከማሰባቸው የተነሳ ለመሥራት አቅም ያንሳቸዋል። ሲያስቡ ጊዜው ይሄድባቸዋል።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ተመሳሳይ ብዙ ሃሳቦችን አስበው ይደክማቸዋል። ሃሳባቸው ወይ የትናንት ትዝታ ነው፤ አልያም ደግሞ ቁጭትና የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ ነው። አንዳንዴ ምን እንደሚያስቡ ሁሉ አያውቁትም። ግን ሃሳባቸው ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን እየተሻማባቸው ነው። ከሰው በታችም እያደረጋቸው ነው። ጭንቀታምም እያደረጋቸው ነው። ምን ይሻላል ታዲያ? ማመስገን! ስታመሰግን ጎዶሎህ ይሞላልሃል። የምታመሰግነው ፈጣሪህ እስትንፋስ ስለሰጠህ ነው። ዛሬን እንድትኖር አንድ እድል ስለጨመረልህ ነው። ከጭንቀትህ ጀርባ ሌላ ሰላም የሚሰጥ ነገር እንዳለ ማወቅ ከፈለክ፤ የአእምሮ ሰላም ከፈለክ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ አመስግን።

ስታመሰግን ነገሮች እንደሚለወጡ ርግጠኛ ትሆናለህ። ከዛ ያላየኸውንም ማመን ትጀምራለህ። እንደው ሰምታችሁ ከሆነ አንዳንዴ ‹‹ማየት ማመን ነው›› ይባላል። ማየት ማመን አይደለም። ማየት ማረጋገጥ ነው። ማመን ያለብህ ያላየኸውን ነው። እምነት ማለት ያላየኸውን ማመን ነው። አመስጋኝ ስትሆን ገና ወደፊት የሚመጣውን ነገር ማመን ትጀምራለህ። አታመሰግንም እንጂ እኮ! ከስንት ጉድ አምልጠሃል። ከስንት ጣጣ ተርፈሃል። አንተ የምታስታውሰው ሰዎች ያደረጉብህን፣ የካዱህን፣ የጎዱህን፣ የጎደለህን ነው እንጂ የተደረገልህን አይደለም።

በነገራችን ላይ አእምሮህ አንተን ለማስደሰት አይደለም የተፈጠረው። አእምሮህ የተፈጠረው አንተን ለማቆየት ነው፤ ለማኖር ነው። ላዛ ሲል ይጨነቃል። ምን ማለት መሰላችሁ? የሆነ ነገር ተፈጠረ ሲባል ....እንዲህ ልትሆን እኮ ነው፣ የኑሮ ውድነቱ መጣ ሲባል እንኳን አንተ በበጎ አታየውም። ገንዘቤን ልጨምር፣ ገቢዬን ላሳድግ አትልም። የኑሮ ውድነቱ ጨመረ ሲባል አእምሮህ በቃ አለቀለህ፣ ቤተሰብህን ምን ልታበላ ነው፣ ደሞ አሁን የወር ኪራይ ይጨምሩብሃል ይልሃል። አእምሮህ ይጨነቃል። ብዙ ነገር ያመጣብሃል። ስለሚያስብልህ ነው።

ነገር ግን እሱን መቆጣጠር መቻል አለብህ። ለምሳሌ አይታችሁ ከሆነ ስለ አንድ ሰው እናትና ሚስቱ እኩል አይደለም የሚያስቡለት። ሁለቱም ይወዱታል። ለምሳሌ ሰውዬው አምሽቶ ከመጣ እናቱ መንገድ ላይ እያለ የምታስበው ‹‹ይሄ ልጅ ተጋጭቶ ይሆን፣ መኪና ገጨው፣ እንደው ተጣልቶ ይሆን፣ እንደው ፈንክተውት ይሆን፣ ከሰው ጋር ተደባድቦ ይሆን›› የሚለውን ሊሆን ይችላል። ሚስት ደግሞ ምንድን ነው የምትለው ባሏ ቢያመሽ? ‹‹አዩ ይሄኔ ከጓደኞቹ ጋር እየጠጣ ነው፣ ፈታ እያለ ነው፣ ከሆነች ሴት ጋር እኮ ሊሆን ይችላል›› ትላለች።




ሁለቱም ይወዱታል። እናት ስትጨነቅ ስለምትወደው ነው። ሚስት ብትቀናም ስለምትወደው ነው። አእምሯችን ግን እንደ እናት ነው የሚጨነቀው። እንዲህ ብትሆንስ እያለ ክፉ ክፉውን የሚያሳስብህ። ስለዚህ በሌለ ነገር ሁሉ እንድንጨነቅ ያደርገናል። ለዚህ ደግሞ መድኃኒቱ ምስጋና ነው። ልክ ስታመሰግን መጨነቅ ታቆማለህ። በነገራችን ላይ ሰው እያመሰገነ ሊጨነቅ አይችልም። ስለዚህ ማመስገን አለብህ። ጭንቀት ሲመጣብህ በአንድ ጊዜ ነው ተኖ የሚጠፋብህ።

የምታመሰግነው የምትፈልገው እንዲሰጥህ አይደለም። አትሸወድ! ከምትፈልገው በላይ የሚያስፈልግህን ፈጣሪህ ያውቃል። አንተ ብትጨነቅ የፀጉርህን ቅንጣት ያህል እንኳ አትጨምርም። አንተ ትለፋለህ ካላመሰገንክ የለፋኸውን ያህል እንኳን መብላት አትችልም። ፈጣሪ ካልፈቀደ አይሆንም እኮ! የሚያስደነግጥ ሀብት ገምብቶ ለጤናው ሲል ጨው የሌለው ሽሮ ሲበላ አላየህም? እሱ ካልፈቀደልህ ትለፋለህ ግን አትበላውም። የምትበላውን ልትገዛ ትችላለህ። ወደ ጉሮሮህ ግን አይወርድም። ባለቤቱ መፍቀድ አለበት። ባለቤቱን አመስግን።

እንደው ይመስልሃል እንጂ ካላመሰገንክ ከንቱ ሆነህ ነው የምትቀረው። ጓደኛሞቹ ፊልም ለማየት ሲኒማ ቤት ገቡ። በጣም አሪፍ የተባለ ምርጥ ፊልም ነው። ደሞም የሚገርመው ፊልሙ አጭር ነው። ፊልሙ ጀመረ። ጓደኛሞቹ ፊልሙን ማየት ጀመሩ። አንደኛው፣ ሁለተኛው፣ ሶስተኛው.... ደቂቃ ላይ ነጭ ሰሌዳ ነው የሚታየው። ምንድን ነው ብለው ቢጠብቁ ሶስተኛውም ደቂቃ ነጭ ሰሌዳ ነው። ሰዎች ማጉረምረም ጀመሩ። ፊልሙን አይጀምሩትም ምን አስበው ነው ማለት ጀመሩ። አሁንም ደቂቃዎች ነጎዱ። ስምንተኛው ደቂቃ ላይ አሁንም ነጭ ሰሌዳ እየታየ ነው። ልጁ ለጓደኛው ዞር ብሎ ‹‹ምንድን ነው? ምን ዓይነት ፊልም ነው ልታሳይኝ ይዘኸኝ የመጣኸው? ደሞ እኮ ምርጥ ፊልም ይላሉ አያፍሩም እኮ የማይረቡ ብሎ›› ተበሳጨ። ነጭ ሰሌዳ ብቻ ነዋ! የሚታየው።

ስምንተኛው ደቂቃ መጋመስ ሲጀምር ግን ካሜራው መራቅ ጀመረ። ያ ነጭ ሆኖ ሲታይ የነበረው የጣሪያው ነጭ ኮርኒስ ነበር። ከዛ አሁንም ካሜራው መራቅ ጀመረ። ከጣራው ተነስቶ ዝቅ ማለት ሲጀምር የሆስፒታል አልጋ ላይ አንድ ሰው ተኝቷል። እጁ፣ እግሩ፣ አንገቱ አይንቀሳቀስም። ፓራላይዝድ ሆኗል። ዓይኑ ማየት የሚችለው ጣራውን ብቻ ነው። አስረኛው ደቂቃ ላይ አንድ ጽሑፍ መጣ ‹‹አንተ ለስምንት ደቂቃ ማየት የሰለቸህን ጣሪያ እሱ እድሜ ልኩን አይቶታል›› ይላል።

አይታችሁ ከሆነ ችግሮቻችንን በየትኛውም ሚዛን ብንመዝን ከዚህ ሰውዬ ያለበት ሁኔታ አይበልጥም። ችግራችን ከዚህ አይበልጥም። ስለዚህ መጨነቁን፣ ማማረሩን ተወውና ተመስገን ማለት መጀመር አለብህ ወዳጄ! ቤትህን ዞር ዞር ብለህ እየው እስኪ። በርግጠኝነት ቤትህ ቀጥ አድርጎ ያቆመለህ መሃል ላይ ያለ አንድ ምሶሶ አለ። ያ ምሶሶ ከሌለ ምናልባት ቤትህ የቆመው በግድግዳ ነው ማለት ነው። አሁን ደግሞ ከቤት ውጣና ሰማዩን ተመልከት። ምሶሶ የለው፣ ግድግዳ የለው፣ ደጋፊ የለው ቀጥ ብሎ ቆሟል። ሰማይ ይደፋብኝ ይሆን ብለህ ፈርተህ ታውቃለህ? አታውቅም።

ፀሐይን ተመልከት አልወጣም ብላ አምፃ ታውቃለች። አንድ ሳምንት ፀሐይ ብትጨልም ምድር እንዴት እንደምትሸበር አስበው። አየር እንደ ወርቅ ተቆፍሮ የሚወጣ ነገር ቢሆን ማን እንደሚተነፍሰው አስበኸዋል? አቅሙ ያለው ነዋ። ጤናህን አስበው። ጤናህን ከሰው ለምነህ የምታገኘው ቢሆን ኖሮ የስንት ሰው ፊት እንደሚገርፍህ አስበኸዋል? ፈጣሪህ እንደሰው አቅመ ቢስ አይደለም። ሰማይን ያቆመ፣ ምድርን የዘረጋ፣ ፀሐይን ያወጣ፣ አየሩን ጤናውን በነፃ የሰጠህ እሱ ነው። እጅግ ውዱን ነገር በነፃ ሰጥቶሃል። አንተ ግን በገንዘብ ታማርረዋለህ። በሥራህ ታማርረዋለህ። እንዲህ አጎደልክብኝ እኮ ትለዋለህ።

አንዳንድ ነገሮች እንዳሉህ እንኳን የምታውቀው ሲጎድሉብህ ነው። ስታጣቸው ነው። ጤናህን የምታጣጥመው የታመምክ እለት ነው። ለካ ጤነኛ መሆን እንዴት ደስ ይላል የምትለው ከባድ ህመም ሲገጥምህ ነው። ስለዚህ ሲጎድልብህ እንዳታዝን፤ ሲጎድልብህ እንዳትነካ አሁን እጅህ ላይ ያለውን እይና ተደሰት። አመስግን። ውዱን ነገር በነፃ ሰጥቶህ በርካሽ ነገር ታማርረዋለህ። ሕይወት ከገባህ አመስግን ወዳጄ! ማማረሩን፣ ማዘኑን፣ ተስፋ መቁረጡን አቁምና ፈጣሪህን አመስግን። ላደረክልኝ ሁሉ ምን እከፍልሃለሁ ተመስገን! ከማለት ውጭ ምን እመልሳለሁ በልና ደጋግመህ አመስግን።

የዛሬ ሳምንት እንደምትሞት ቢነገረህ አሁን ያስጨነቀህ ነገር በሙሉ ተራ እንደሆነ ይገባሃል። ከጎደለህ ይልቅ የተደረገልህ ይበልጣል። ተመስገን በል ወዳጄ! ቀንህን አብራው። ሕይወትህን ተስፋ ለኩስባት። ያኔ መኖር ጀምረሃል። ያኔ ዓይንህን ገልጠሃል። ያኔ ከፊትህ የተገተረው ችግር ዓይንህ እያየ ይደረመሳል። ነፃ ትወጣለህ። ምስጋና ነፃ ያወጣሃል ወዳጄ!

አእምሮህ ውስጥ ሊበላህ ያሰፈሰፈ አውሬ አለ። አትችልም! የሚል። የሚመጣው ጊዜ አስፈሪ ነው፣ ይቅርብህ አርፈህ ተቀመጥ፣ ቁጭ በል የሚል አውሬ አለ። ሌላኛው አውሬ ደግሞ ትችላለህ! ጀግና ነህ አንተ እኮ ትሞክራለህ፣ ፈጣሪ ብዙ ነገር አድርጎልሃል የሚል አውሬ አለ። ትልቁ ነጥብ ምን መሰለህ? የትኛውን አውሬ ነው የምትመግበው? አብዝተህ የመገብከው አውሬ ማሸነፉ አይቀርም። አእምሮህ ውስጥ ትችላለህ! የሚለውን አውሬ አብዝተህ የምትመግበው ከሆነ ማሸነፉ አይቀርም። እሱን ልትመግበው የምትችለው ፈጣሪ ያደረገልህን እያሰብክ ማመስገን ከቻልክ ብቻ ነው። ምስጋና ብቻ ነው ኃይል የሚሰጥህ።

ከዚህ በኋላ አንተ አመስጋኝ ነህ። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆን አታማርርም፤ አትነጫነጭም፤ ብሶት አታወራም። ያኔ ነገሮች መስተካከል ይጀምራሉ። ፈጣሪማ ለእኔ እያደላ ነው ትላለህ። በኑሮህ አመስጋኝ መሆን ትጀምራለህ። ደስታህ ከማንም አይደለም ከራስህ ነው የሚመነጨው። የሆነ ሰው ከመሬት ተነስቶ ሊያስከፋህ አይችልም። የሆኑ ሁኔታዎች ደስታህን ሊነጥቁህ አይችልም። እውነተኛ ደስታ ያለው ውጭ አይደለም። ውስጥህ ነው። የመርከብህ ካፒቴን አንተ ነህ። የምትሾፍረው አንተ ነህ። ማንም አይደለም። ካጣኸው ይልቅ ያገኘኸው ይበልጣል። ከተደረገብህ ይበልጥ የተደረገልህ ይበልጣል። እጅህ ላይ ያለውን አላየህም እንጂ ካንተ በላይስ እድለኛ የለም። አንተ ላይ ሥልጣን ያለው ፈጣሪህ ብቻ ነው። ስለዚህ አመስግን ወዳጄ!

**አንዳንድ ነገሮች እንዳሉህ እንኳን የምታውቀው ሲጎድሉብህ ነው። ስታጣቸው ነው። ጤናህን የምታጣጥመው የታመምክ እለት ነው። ለካ ጤነኛ መሆን እንዴት ደስ ይላል የምትለው ከባድ ህመም ሲገጥምህ ነው። ስለዚህ ሲጎድልብህ እንዳታዝን፤ ሲጎድልብህ እንዳትነካ አሁን እጅህ ላይ ያለውን እይና ተደሰት። አመስግን**

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት በሩ ክፍት፤ መንገዱም ሰፊ ነው !

የኢትዮጵያ እና የግብፅ ሕዝቦች ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ታሪካዊ ትስስር ያላቸው፤ የረጅም ዘመን የሀገረ- መንግሥት እና የተለያዩ ስልጣኔዎች ባለቤቶች ናቸው። እንደ አፍሪካዊም ተመሳሳይ እጣ ፈንታ የሚጋሩ፤ ነገዎቻቸውን መተማመን በሚፈጥር ትብብር ብሩህ ለማድረግ ባለብዙ አማራጮች ናቸው።

ሀገራቱ የዓባይ ወንዝ በመካከላቸው የፈጠረውን ተፈጥሯዊ ትስስር የስትራቴጂክ አጋርነት ምንጭ በማድረግ፤ ለሕዝቦቻቸው የጋራ ተጠቃሚነት አብረው ሊሰሩ የሚችሉባቸው ሰፊ ዕድሎች አሉ። ዕድሎቹን በመጠቀም ለቀጣናው ከዚያም ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ የትብብር ምዕራፍ መፍጠር እንደሚቻል ይታመናል።

ይህም ሆኖ ግን በዓባይ ወንዝ ውሃ ዙሪያ በግብጽ በኩል የሚነሱ ፍትሐዊነት የጎደላቸው ፣ በብዙ ውዥንብሮች እና የሀሰት ትርክቶች የተሞሉ ጥያቄዎች ፣ የሀገራቱ ሕዝቦች የዕድሎቹ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ፈተና ሆነዋል። ያለመተማመንን በመፍጠርም በጋራ ተጠቃሚነታቸው ላይ ጋሬጣ ፈጥረዋል።

በየዘመኑ የነበሩ የግብጽ መንግሥታት በዓባይ ወንዝ ዙሪያ ለገዛ ሕዝባቸው ሳይቀር የተዛቡ እና የተሳሳቱ መረጃዎችን በመስጠት፤ በወንዙ ውሃ ጉዳይ ሕዝባቸው ተጨባጭ እውቀት እና ፍትሐዊ አቋም እንዳይኖረው አድርገዋል። የሀገራቱን ሕዝቦች ግንኙነት ስጋት ውስጥ የሚከቱ ትርክቶችን ፈጥረው በስፋት ሲያስተናግዱም ቆይተዋል።

ዘመን ባለፈባቸው አፈ ታሪኮች የግብጽ ሕዝብ መቼም ቢሆን በዓባይ ወንዝ ውሃ ጉዳይ ተኝቶ እንዳያድር አድርገዋል። የዓባይ ውሃን ጉዳይ ዋነኛ የሀገር ውስጥ የፖለቲካ አጀንዳ በማድረግ፤ ወደ ስልጣን መምጫ እና የስልጣን ዘመን መቆያ አድርገውታል። በዚህም ሕዝቡ ባልተገባ መንገድ ሀብቱን፤ ጊዜውን እና ዕውቀቱን እንዲያባክን አድርገውታል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አብዛኛው የግብጽ ሕዝብ ስለዓባይ ወንዝ መገኛ ስፍራ ተገቢውን መረጃ ሳያገኝ ቆይቷል። በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሳይቀር ትውልዶች በተሳሳተ አስተምህሮ ውስጥ ማለፋቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። በዚህ ሂደት የሀገሪቱ ምሁራን ተሳታፊ የመሆናቸው እውነታ ደግሞ የችግሩን ግዝፈት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

ከዓባይ ወንዝ ውሃ ጋር በተያያዘ ያለው የግብጽ መንግሥታት ኢ ፍትሐዊነት የረጅም ዘመናት ታሪክ ያለው ፣ ከማስፈራራት ጦር አሰልፎ ለወረራ እስከመሰለፍ የደረሰ እና በብዙ አንገት የሚያስደፉ የሽንፈት ታሪኮች ታጅቦ የተጠናቀቀ ስለመሆኑ የታሪክ መዛግብት የሚናገሩት የአደባባይ ምስጢር ነው።

በታሪክ መገራት ያልቻለው ይህ የግብጽ መንግሥታት ያልተገባ ባህሪ ፤ በዚህ ዘመንም በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል ያለመተማመን እና የጠላትነት መንፈስ ምንጭ እየሆነ ይገኛል። በ21ኛው የመረጃ ክፍለ ዘመን የሀገሪቱ መንግሥታት የገዛ ሕዝባቸውን ባልተገባ ትርክት በዓባይ ውሃ ያልተገባ ስጋት ውስጥ እንዲገባ አስበው እየሠሩ ነው ።

የዓባይን ውሃ የሀገር ውስጥ የፖለቲካ አጀንዳ በማድረግ፤ እነሱ ለስልጣናቸው ሲሉ ለሚፈጥሯቸው የተዛቡ ትርክቶች፤ የግብፅ ሕዝብ ገንዘቡን ፣ጊዜውን እና ጉልበቱን ኢንቨስት እንዲያደርግ እያስገደዱት ነው ። ላልተገባ ቅቡልነት ባልተገባ ትርክት ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል እያደረጉትም ነው።

ለዚህም ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በምርጫ ሆነ በመፈንቅለ መንግሥት ወደ ስልጣን የመጡ የግብጽ መንግሥታት በስልጣን ዘመናቸው ለሕዝቦቻቸው ባደረጓቸው ዲስኩሮች የዓባይ ወንዝ ውሃን የሀገር ስጋት ምንጭ ለማድረግ ያልሞከረ የለም። ለፈጠሯቸው ስጋቶች መፍትሔ አድርገው የወሰዷቸው አማራጮችም የኃይል እና የሴራ አማራጮች ነበሩ።

ይህ የግብጽ ፖለቲካ የቱን ያህል ቆሞ ቀር እና ዘመንን መዋጀት የተሳነው ስለመሆኑ ተጨባጭ ማሳያ ነው። ዛሬም በስልጣን ላይ ያለው የሀገሪቱ መንግሥት በተመሳሳይ መንገድ የዓባይን ውሃ የሀገር ስጋት ምንጭ አድርጎ ለማሳየት ረጅም ርቀት ሄዷል። በዚህም ከትናንት ስህተቶች ለመማር ፈቃደኛ እንዳልሆነ በተጨባጭ አሳይቷል።

ብዙ ሰላማዊ እና የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረጉ፤ ዘመኑን የሚዋጁ አማራጮች ባሉበት በዚህ ወቅት፤ እንደቀደሙት የሀገሪቱ መንግሥታት ከሴራ እና ግጭቶች ማትረፍ ይቻላል በሚል እየሄደበት ያለው መንገድ ከሁሉም በላይ የሕዝቦችን ፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነት አደጋ ውስጥ የከተተ ነው። መንገዱ እንደቀደመው ዘመን ለግብጽ ሕዝብ የሚያተርፈው ነገር አይኖርም።

የሴራ እና የግጭት መንገዶች አሁን ባለው ዓለም አቀፍ እሳቤ አትራፊ አይደሉም፤ አትራፊ ይሆናሉ ብሎ አስቦ መንቀሳቀስ ተመሳሳይ ታሪካዊ ስህተቶችን እና ስህተቶቹ የፈጠሩትን የታሪክ ስብራት ከመድገም ባለፈ የሚያስገኘው ትርፍ የለም። ይህን ቆም ብሎ ማሰብ ለሕዝብ ፍላጎት ቆሜያለሁ ለሚል መንግሥት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ሥራ ነው። በአጠቃላይ ለሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት አሁንም በሩ ክፍት፤ መንገዱም ሰፊ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓለም አቀፍ ተሰሚነት እንዲጎለብት

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር የነበራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ረጅም ዘመን ያስቆጠረና ታሪካዊ ነው። ኢትዮጵያን ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የነበሩ መሪዎቿ በየዘመናቸው የሀገሪቱን ሀያልነትና ዝና ብሎም ብሔራዊ ጥቅሟን ባስጠበቀ መልኩ ከበርካታ ሀገራት ጋር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል።

በመሪዎቿ የአመራር ጥበብና ብልሀት ከሌሎች ሀገራት ጋር የምታደርገው ሁለንተናዊ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በትውልድ ቅብብሎሽ አልፎ የኢትዮጵያን ከፍታና ዓለም አቀፍ ተሰሚነት ይበልጥ በማሳደግ ዛሬ ላይ ደርሷል።

እንዲህ አይነቱ የአመራር ጥበብና ብልሀት ከመሪዎቹ በኩል በመኖሩም ነው ኢትዮጵያ ከተቀረው ዓለም ጋር ያላት የዲፕሎማሲ ግንኙነት በጊዜ ሂደት አድጎና ጎልብቶ የዛሬው ዘመን ላይ የደረሰው። አሁንም ቢሆን የዚህ ዘመን የሀገሪቱ መሪዎች የዚችን ስመ ገናና እና የብዙ ታሪክ ባለቤት የሆነችውን ሀገር አደራ ከአባቶቻቸው ተረክበው ይህንኑ ዝናዋንና ታላቅነቷን ባስጠበቀ መልኩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቷን እያስቀጠሉ ይገኛሉ።

በተለይ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ ወዲህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በተለያዩ የአፍሪካ፣ እስያ፣ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ሀገራት ተጉዘው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በማስረዳትና ከዚህ በፊት ሀገሪቱ የነበራትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠናከርና ዳግም እንዲታደስ በማድረግ ትልቅ የዲፕሎማሲ ሥራ ሠርተዋል።

በምላሹም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሄዱባቸው ሀገራት ታላላቅ መሪዎች በተከታታይ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣትና የሀገሪቱን ትክክለኛ ምስልና ገፅታ አይተውና ተረድተው ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሁለንተናዊ መልኩ አጠናክረው ለማስቀጠል ይሁንታቸውን ገልጸዋል።

የሰሞኑ የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የኢትዮጵያ ይፋዊ የሥራ ጉብኝትም የዚሁ ጠንካራ ዲፕሎማሲ ውጤትና ኢትዮጵያ በነዚህ ሀገራት ታላላቅ መሪዎች ያላት የተሰሚነት አቅም እያደገ ስለመምጣቱ ምስክር ነው።

ኢትዮጵያ ከተቀረው የዓለም ሀገራት ጋር አሁን ላይ እያደረገችው ያለው ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከፍ ወዳለ ደረጃ ተሸጋግሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት ተሰሚነት ይበልጥ እንዲጎለብትና ከዚህ በላይ እንዲቀጥል ከመንግሥትና ከዚህ ጋር በተያያዘ ከሚጠቀሱ አካላት ተጨማሪ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃል።

አሁን ባለው ወቅታዊ የዓለም ሁኔታ የዲፕሎማሲው አቅጣጫና አካሄድ እለት በእለት እየተቀያየረ መጥቷል። ለዚህ ተቀያያሪና ተለዋዋጭ ዲፕሎማሲ መስመር ደግሞ ራስን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መሄድ ይጠይቃል። ሀገራት እርስ በርስ የሚያደርጉት ግንኙነት በአብዛኛው ብሔራዊ ጥቅምን፣ የሰጥቶ መቀበልና የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ለዚህ ወቅታዊና ተለዋዋጭ የዲፕሎማሲ አቅጣጫ የተለየ ስልት ይዞ መቅረብ ይጠይቃል። በተለይ የታላላቅ ሀገራትን ልብ ለማሸነፍና በእነርሱ ዘንድ ያለንን ተሰሚነትና ተቀባይነት ከፍ ለማድረግ በእነሱ ደረጃ የሚመጥን የዲፕሎማሲ አቅም መገንባት ያስፈልጋል።

ለዚህ የሰላ አንደበትና እውቀት ብሎም የማሳመን ብቃት ያላቸው ዲፕሎማቶችን ማብቃትና መመደብ ያስፈልጋል። በእውቀትና በልምድ የበሰሉ ዲፕሎማቶችን የማፍራቱ ጉዳይ ገና ከታዳጊነት ጀምሮ ሊሠራበት ይገባል። እንዳውም ፖለቲካን ሳይሆን ሙያን ብቻ መሠረት አድርገው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ጥብቅና የሚቆሙና የሚሟገቱ ዲፕሎማቶችን ነው በብዛት ማፍራት የሚጠበቅብን።

በሌላ በኩል ደግሞ የዲፕሎማቲክ ሥራውን ሊያሳልጡ የሚችሉ ሰዎችን ብቻ በትክክለኛው መስፈርት መርጦ ትክክለኛው ቦታ ላይ መመደብ ይገባል። በምጣኔ ሀብት የበሰለና ቁንጮ የተባለ ምሁር በዲፕሎማሲው ጎራ ይሳካለታል ማለት አይቻልም።

ባይሆን የዲፕሎማሲ እውቀቱን ቢያሰፋ ከምጣኔ ሀብት እውቀቱ ጋር አዛምዶ ኢትዮጵያን ከተቀረው ዓለም ጋር በምታደርገው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ዙሪያ የራሱን ሙያዊ አብርክቶ ሊያደርግ ይችላል።

የዲፕሎማሲ ሥራ ሁሌም ቢሆን ወጥነት ያለው፣ ተከታታይና ወቅቱን የዋጀ ጠንካራ መሆን ይጠበቅበታል። በዲፕሎማሲ ሥራ እንቅልፍ የለም። መዘናጋት ብዙ ሀገራዊ ጥቅሞችን ያሳጣል። የተሰሚነትን አቅም ያስነጥቃል።

የዲፕሎማሲ ሥራውን ይበልጥ በማዘመንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አቅም ገንብቶ ተሰሚነትን ለመጨመር መንግሥት ሌት ተቀን መሥራት ይጠበቅበታል። ከዚሁ ጎን ለጎን በዲፕሎማሲው መስክ ቱባ እውቀት ያላቸውን በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እውቀታቸውን በሚገባ መጠቀም ይገባል።

ኢትዮጵያውያን ምሁራኑ ከሀገሪቱ ጎን መቆም ይጠበቅባቸዋል። የመንግሥትን ጥያቄ ተቀብለውና ከጎኑ ቆመው በማገዝ የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ አቅም ማሳደግና ተሰሚነቷም እንዲጨምር የማድረግ ሀገራዊ ኃላፊነት አለባቸውና ለዚህ ሊሠሩ ይገባል።

በተመሳሳይ በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ሊህቃንም ያላቸውን እውቀትና ልምድ ተጠቅመው የበኩላቸውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የተሰሚነት አቅም ከመጨመር ባለፈ ክብሯንና ዝናዋን ጠብቃ እንድትቀጥል ያስችላታል። የዲፕሎማሲ ሥራውን ከማጠናከር ባለፈ ግን የኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት ይበልጥ ለማሳደግ በሀገር ውስጥ ተጨማሪ የቤት ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል።

ለአብነትም በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ማምጣት ዋናውና ትኩረት ተደርጎ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ገበያ አንዱ ራስን ለመሸጥ የሚያስችለው መንገድ በሀገር ውስጥ አስተማማኝ ሰላምና ደህንነት መኖር ነው። ይህ ደግሞ አሁን ላይ እየተሠራበት ያለ ጉዳይ ቢሆንም አሁንም አስተማማኝ ሰላም ለማረጋገጥ ተጨማሪ ሥራዎች መሥራት አለባቸው።

ሀገራት የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ይከተላሉ። ከፖሊሲና ስትራቴጂያቸው ባለፈ ግን በውስጣቸው ያለው ሰላምና መረጋጋት ሌሎች ሀገራት በቀላሉ ገብተው በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ በር ይከፍታል።

በኢትዮጵያም አሁን ላይ አንፃራዊ ሰላም በመኖሩ የተለያዩ ሀገራት በተለያዩ አማራጮች መዋእለ ንዋያቸውን ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እያሳዩ ነው። ሆኖም የተሟላ የሰላም ሁኔታ ማረጋገጥ አሁንም ይቀራል፤ በዚህ ላይም ሊሠራ ይገባል።

ያኔ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ያላትን ተሰሚነት ማሳደግና ማጎልበት ትችላለች። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት ተሰሚነት በጎለበተ ቁጥር ደግሞ የባሕር በር ጥያቄዋን ጨምሮ ሌሎችም ጥቅሞቿ ይከበራሉ። በሌሎችም ሀገራት መሪዎች የመጎብኘት እድሏን ታሰፋለች። ያላትን ታሪካዊ ዝና እና ክብርም አስጠብቃ ትቀጥላለች!!

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት €€እንዲህም ይኖራል እንዴ?« ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም €€እንዲህም ይኖራል« ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ዓይናማ ልቦች...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### እንደ መነሻ

በአንድ ሥፍራ ለአንድ ዓይነት ዓላማ በቀጠሮ የተገናኙት እናቶች ዛሬም ስለልጆቻቸው ልዩ ወግ ይዘዋል። እነሱ ሁሌም ቢሆን ስለነዚህ ልጆች ማውጋትና ማሰብን አያቆሙም። ስለ እነርሱ እንርሳ፣ እንተው ቢሉ እንኳን ፈጽሞ አይቻላቸውም። በጀርባቸው፣ ባያዝሏቸው በልባቸው ያኖሯቸዋል። በእጅ ባይዟቸው፣ በሃሳብ ከእነሱ ጋር ናቸው። ለእነዚህ እናቶችና የሌሎቹ ኃላፊነት ተመሳሳይ አይደለም። ልጆቹ እንዳሻቸው የሚሮጡ፣ የሚጫወቱ፣ የሚናገሩ አይደሉምና ልዩ ትኩረትን ይሻሉ።

አብዛኞቹ የጨቅላነት ዕድሜያቸውን በተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና አሳልፈዋል። ይህ ወቅት ለእነዚህ ዕንቦቀቅላዎች አዲስ ዓለምን መተዋወቂያና መግባቢያ ብቻ አይደለም። አብዛኞቹ ይህን ምዕራፍ በታላቅ ስቃይና ህመም ይሻገሩታል። ከልጆቹ እናቶች አብዛኞቹ ሕይወትን በፈታኝ ኑሮ የሚገፉ ብቸኞች ናቸው። አባወራዎቻቸው የጤና ችግር ያለባቸው ልጆች አባት መባልን አይሹም። ይህ እውነታ ገና በጠዋቱ ጥለዋቸው እንዲሸሹ ምክንያት ነው።

ጥቂት የማይባሉት እናቶች ኑሯቸው ጎስቋላና ከእጅ ወደ አፍ የሚባል ነው። ጉልበታቸውን ገብረው፣ በላባቸው ወዝ የሚያድሩ በመሆናቸው ውሏቸው በችግር ይገፋል። እነዚህ ሴቶች በእርግዝና ጊዜያቸው የፎሊክ አሲድን በአግባቡ ባለመውሰዳቸው በወለዷቸው ልጆች ላይ የጤና እክል እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

የነርቭ ዘንግ ክፍተትና የጭንቅላት ውሃ መቋጠር በሳይንሳዊ አጠራሩ ‹‹ስፓይናቢፊዳና ሀይድሮሴፋለስስ›› በአብዛኛው ችግሩ የሚታወቀው በእርግዝና የመጨረሻ ጊዜያት በመሆኑ ከነችግሩ የሚወለዱ ህጻናት ቁጥር ይጨምራል። እናቶቹ ስሜታቸውን አመሳስሎ ቋንቋቸው አንድ ባደረገው ቆይታ ስለልጆቻቸው ኑሮና ሕይወት እየተወያዩ ነው። ሁሉም በሚባል መልኩ ኑሯቸው በአንድ ይጋመዳል። የአንዳቸው ችግር ግልባጭ ለሌላቸው የሕይወት መስታወት ነው። አብዛኞቹ በችግር ማስነው፣ በመከራ ታግለው ሕይወትን ይገፋሉ። ሙሉ ማንነታቸውን ለልጆቻቸው ሰጥተዋልና ጌጥና ውበት አያምራቸውም።

እነሆ! በ ሆፕ ኤስ ቢ ኤች /Hop SPH/ ቅጥር ግቢ ተገኝተናል። በበርካታ ወላጆች፣ እንግዶችና ህጻናት መሀል። በሥፍራው የመገኘታችን ሚስጥር የአዲሱን ዓመት መግባት ተከትሎ ወቅቱን በታላቅ ተስፋና ብሩህነት ለመቀበል ነው። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ወላጆችን አገናኝቶ ልብ ለልብ ያወያያል። ሁሉም ብሶታቸውን፣ ሀዘንና ደስታቸውን ያወጋሉ። ስላለፈው ትናንት ሰላሉበት ዛሬና ስለመጪው ነገ እንዲያወጉ እድል ይፈጥራል።

እያንዳንዱ ጊዜ በሁሉም እናቶች ልቦና በዋዛ የማይፈዝ ዐሻራን አኑሯል። ሁሉም ስለልጆቻቸው ወጥተው የወረዱበት፣ በቤት ኪራይ የተንገላቱበት፣ በቀን ሥራ የደከሙበት፣ በችግር የተፈቱበት እውነትን ሰንቀዋል። አብዛቹ ዛሬም በጉስቁልና ውስጥ ናቸው። ስለ ልጆቻቸው መኖር ታላቅ ዋጋን ከፍለዋል። የእናቶቹ በሕይወት መቆም ለልጆቹ ታላቅ ዋስትና ነው። እነሱ ከሌሉ የእስትንፋቸው መቀጠል አደጋ ውስጥ ይወድቃል። ልጆቹ እንደ እናት ሁሉን ችሎ የሚያሳድግ፣ ነገን የሚሻግር አለኝታ ከጎናቸው የለም።

ይህን ሀቅ ሲያስቡት እናቶች ቅስማቸው ተሰብሮ ከሀዘን ይወድቃሉ፣ ይተክዛሉ። እናም የአብዛኞቹ ስሜት ተመሳስሎ በአንድ ይጋመዳል። ሁሌም የልጆቻቸው ሞት ከእነሱ ህቅታ በአንድ ቀን እንዲቀድም ይመኛሉ። ልጆቻቸውን ቀብረው እነሱ ቢከተሉ እፎይታቸው ነው። ይህ ይፈጸም ዘንድ አብዛኞቹ ለፈጣሪያቸው ይጸልያሉ፣ ይማልዳሉ።

**ዕለቱን በእውነታ...**

በዚህ ቀን በሥፍራው የተገኙ ወገኖች በድርጅቱ የሚታገዙ እናቶች ብቻ አልነበሩም። ስለህመሙ ግንዛቤ የሚሰጡ ባለሙያዎችና ድርጅቶች፣ አጋር አካላትና ተባባሪ ተቋማት፣ ልበ ቀና በጎ ፈቃደኞችና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች ተሳታፊ ሆነዋል። ዕለቱ ወላጆች እርስ በእርስ ለመወያየት ዕድል ያገኙበት ቀን ነው። ጥቂት ቢሆኑም አንዳንድ ጠንካራ አባቶች ከሚስቶቻቸው ጋር በሥፍራው ታድመዋል። እነሱ በልጆቻቸው ላይ የሆነውን እውነት በእኩል ሲጋሩ ልባቸው የቀና አባወራዎች ናቸው።



ወይዘሮ ሰላምና ልጆቻቸው

ጥቂት የማይባሉ እናቶች የሕይወት ተሞክሯቸውን ማጋራት ይዘዋል። አብዛኞቹ ልጆቻቸውን ያለ አባት የሚያሳድጉ፣ በችግርና መከራ ሕይወትን የሚገፉ ናቸው። ብዙ አሳዛኝ፣ አስገራሚ ድምጾች እየተሰሙ ነው። ሁሉም መልከ ብዙ ገጽታን በተላበሱ ሀቆች ተሸፍነዋል። ሽፍናቸውን ሲገለጥ ዓይንን በዕንባ ይሞላሉ። ውስጥን አሸብረው አንገት ያስደፋሉ።

ማህሌት ሽቶ የህጻን ያሬድ ወላጅ እናት ነች። የብቸኝነት ሕይወትን የጀመረችው ባለቤቷ የስድስት ወር ነፍሰጡር ሆና ጥሏት ከሄደ ጊዜ ጀምሮ ነው። በብዙ ችግሮች አልፋ ልጇን ወልዳ ብትስምም ደስታዋ ሙሉ አልሆነም። ትንሹ ያሬድ በዕድሜው ቆሞ ለመሄድ፣ ለመዳህ አልሆነለትም። እግሮቹ እየዛሉ ሰውነቱ ይንቀጠቀጣል። ያለአንዳች ለውጥ ጥቂት ጊዜያት ተቆጠሩ። የአንድ ዓመት ልደቱን ባከበረ ማግስት እናት ቆሞ መሄዱን፣ እንደ እኩዮቹ መሮጥ፣ መንገዳገዱን ጠበቀች። ዓይኖቿ የተመኘችውን አላሳይዋትም። ሁለት ዓመታት ሊሞላው ጥቂት ወራት ሲቀረው ልጇ በሀይድሮሴፋለሰስ መጠቃቱ ታወቀ። ይህ ጊዜ ኑሮን በደባልነት ለምትገፋው ማህሌት እጅግ ከባድ ይሉት ነው። አብረዋት ከሚኖሩ ጓደኞቿ በቀር ‹‹አለሁሽ›› የሚላት ወዳጅ ዘመድ ጎኗ የለም። የልጁን መወለድ እንኳን የማያውቀው ባሏ ድምጹ አይሰማም። ህጻኑ አስቸኳይ ሕክምና ያስፈልገዋል። ይህን ለማድረግ በቂ ዝግጅትና የገንዘብ አቅም ግድ ነው።

ማህሌት ገንዘብም ረዳትም የላትም። ልጇን አዝላ ልብስ አጠባ ብትውልም ገቢዋ ከቤት ኪራይ በላይ አያሻግራትም። እንዲያም ሆኖ ልጇን ካጋጠመው ህመም መታደግ አለባት። እናት በሆነባት ሁሉ ተጨነቀች፣ ግራ ገባት። አሁን ተአምር ከመጠበቅ ውጭ ስለራሷ ርግጠኛ አልሆነችም። በሀዘን ተውጣ ሳለ አንድ ቀን ከልበ መልካሞች ጋር ተገናኘች። እነሱ እውነታውን አይተው ዝም አላሏትም። ትራንስፖርት ሰጥተው ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል አመላከቷት። ማለዳውን ሆስፒታል የደረሰችው ማህሌት ልጇን ሐኪሞች ፊት ለማቅረብ መረጃ ጠየቀች። በእጇ የሪፈራል ወረቀት እንደሚያስፈልግ ተነገራት።

መላ መፍትሔው ቢጠፋት በግራ መጋባት ማልቀስ፣ ማንባት ያዘች። አሁንም ልበ መልካሞች አልጨከኑባትም። ካርድ አውጥታ ወደ ነርቭ ክፍል ተላከች። ህጻኑ ለተመሳሳይ ሕክምና ወደ ሌላ ሆስፒታል መሄድ ነበረበት። ከወራት ቆይታ በኋላ ተራው ደርሶ ሕክምናው ተጀመረ። ለትንሹ ልጅ የቀዶ ሕክምና ማድረግ ግድ ሆኗል። ለዚህ ሕክምና አስፈላጊ ወጪዎች ይጠበቃሉ። ማህሌት እንኳን ለሕክምና ለትራንስፖርት የሚረዷት ሌሎች ናቸው። ሆስፒታል ልጁን ይዛ በቆየች ጊዜ በርካቶች ምሳ እየቋጠሩ ጠየቋት፤ አይዞሽ ሲሉ አበረቷት። አሁንም በሐኪሞች ቀናነት የታሰበው ሁሉ ተከወነ። እንዳያልፉት የለም ልጇ ከአስር ጊዜ በላይ የቀዶ ሕክምና ተደርጎለት ማገገም ያዘ።

ዛሬ ህጻን ያሬድ ለመራመድ፣ ለመሮጥ እየታገለ ነው። የንግግር ችግር የለበትምና ከእናቱና ከሌሎች ጋር ይግባባል። እናት ማህሌት ልጇ ዕድሜው ለትምህርት መድረሱን ስታይ እንደ እኩዮቹ ትምህርት ቤት እንዲሄድ ተመኘች። ግን እሱን ለማስተማር ዛሬም አቅም የላትም።

**ሁሉም እንደ አንድ ...**

ገና በማለዳው እንግዶቻቸውን በክብር መቀበል የጀመሩት የሆፕ ኤስ ቢኤች ግብረሰናይ ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ቤዛ በሻህ ለታዳሚዎቹ የልባቸውን ለማውጋት ወደ መድረኩ ብቅ አሉ። ወይዘሮ ቤዛ ይህን ድርጅት ለመመስረት ምክንያት የሆናቸው የሁለተኛው ልጃቸው እውነታ ነበር። ትንሹ ህዝቅኤል ሲወለድ ጀምሮ አብሮት የዘለቀው ህመም የንግግር፣ የመስማትና የማየት ችሎታውን ነጥቆታል። ዘወትር ከእናቱ የሚግባባው በንግግር አልባው ደማቅ ፈገግታ ብቻ ነው። በፈገግታው ውሎ ያድራል። በፈገግታው ከሁሉም ይኖራል። ይህ ማንነት በእናቱ ቤዛ ዘንድ ትርጉም አላጣም። ውስጣቸው ዘልቆ የማይፈዝ የተስፋ ብርሃን ፈነጠቀ። ይህ ብርሃን ከትናንት አልፎ ነገን ሲያሻግር ምክንያት ነበረው። ዛሬ ለብዙኃን እሱን መሰል ልጆች በድርጅቱ መጠሪያ ተስፋን ሰይሞ ሕይወታቸውን ይጋራ ይዟል። እናት ቤዛ ይህን ድርጅት ሲያቋቁሙ የበርካታ እናቶችን ስሜት በወጉ አውቀውት ነው።

እሳቸው ከማንም በላይ በእነሱ ጫማ እግራቸውን አስገብተው ችግራቸውን ለክተዋል። ህመም ስቃያቸውን ለይተዋል። የእሳቸው ልጅ ህመም የሌሎች መሰሎቹ፣ እኩዮቹ ስሜት ነው። በእሱ ውስጠት አሻግረው የብዙኃኑን ስቃይና ችግር አስተውለዋል። ቤዛ ካሏቸው ሁለት ልጆች የመጀመሪያዋ ሳሮን ትባላለች። እሷ ከታናሽ ወንድሟ ህዝቅኤል በእጅጉ የተለየች ናት። እንደ ማንኛውም ጤነኛ ልጅ ታወራለች፣ ትሮጣለች። እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስም ትምህርት ቤት ገብታ ዕውቀት እየቀሰመች ነው።

ህዝቅኤል ግን ምግብ ከመመገብና ከመሳቅ ውጭ የሚጠበቀው ለውጥ እየታየበት አይደለም። ለእናት ቤዛ ሁለቱም ልጆች የራሳቸው ፍሬዎች ናቸው፤ በእነሱ መኖር በእጅጉ ደስ ይላቸዋል። ሁሌም እንደሚሉት ግን ከሁለቱ የሚጠበቁት የየዕለት ውጤት ፍጹም የተለያየ ነው። እንዲህ መሆኑ ግን ለልጆቻቸው የሚገባውን ዕድል እንዲነፍጉ አላስገደዳቸውም። ለሳሮን ካሰበችው ግብና ዓላማ እንድትደርስ፣ በትምህርቷ፣ በጤናዋ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቷ፣ ከሌሎች ጋር በሚኖራት ማህበራዊ ግንኙነትና በሌሎችም እንደ እናት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ለህዝቅኤል ደግሞ ምግቡ እንዳይጎድልበት፣ ጤናው እንዳይዛባበት፣ ኢንፌክሽን ተፈጥሮ እንዳይጎዳ፣ እንዳይታመም ደማቅ ፈገግታው እንዳይፈዝ ግዴታቸውን ይወጣሉ። ይህ እውነት የወይዘሮ ቤዛ የእናትነት ግዴታና ድርሻ ሆኖ አብሯቸው ይዘልቃል።

**ስምን ?**

የሥራ ቦታዋ በዘውዲቱ ሆስፒታል እንደሆነ የገለጸችው ወይዘሮ ሰላም የሁለት ልጆች እናት ነች። ሁለተኛው ልጇ የአብስራ ይባላል። እሱን በማግኘቷ ደስተኛ መሆኗን ደጋግማ ትገልጻለች። የአብስራ ባጋጠመው የሀይድሮሴፋለስስ ችግር ብዙ ተፈትኗል። እናት እሱን ለማስተማር ያልሆነችው የለም። ያለበትን የጤና ችግር የተመለከቱ ትምህርት ቤቶች እንደሌሎች በደስታ ተቀብለው ሊያስተምሩት አልፈቀዱም። «ልጄን አስተምሩልኝ» ስትል በርካታ ትምህርት ቤቶችን ጠይቃለች። ከአንዳቸውም ግን በጎ ምላሽ አላገኘችም። እንዲያም ሆኖ ተስፋ አልቆረጠችም።

እግሯ እስኪቀጥን እየዞረች የአስራ ሁለት ትምህርት ቤቶችን ደጃፍ አንኳኳች። ‹‹ግቢ›› ብለው በሩን የከፈቱላት ፈቃደኞች አልነበሩም። የአብስራ ዛሬ 10 ዓመት ሆኖታል። አይናገርም፣ አይሰማም። እይታውም እምብዛም አይደለም። እዚህ ዕድሜው እስከሚደርስ በመውደቅ መነሳት መሀል ተንገላቷል። እናት ሰላም ከልጇ ጋር በርካታ ፈተናዎችን ተሻግራለች። ዛሬም ግን ልጆቿን ግራና ቀኝ ሳትለይ እኩል እያኖረች ነው።

ሰላም የእሷን ሕይወት መነሻ አድርጋ ስለሌሎች እናቶች ኑሮ ታስባለች። እንዲህ ዓይነት ወገኖች ችግራቸው የበዛ ነው። በተለያዩ ጉዳዮች ይፈተናሉ። አብዛኛዎቹ ልጆች የዳይፐር ተጠቃሚዎች ናቸው። ጥቂት የማይባሉትም በዊልቸር እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። ለእነዚህ ዜጎች የትምህርትና የሌሎች ጥቅሞች ድጋፍ ማድረግ አልተለመደም። እንዲህ መሆኑ በወጣትነት ዕድሜ የሚገኙ በርካቶች ሳይቀር ደጁን እንዳያዩ ቤት ተዘግቶባቸው እንዲኖሩ ተገደዋል። አንዳንዶች ለእነዚህ ልጆችና ቤተሰቦቻቸው ያለው አመለካከት የተንጋደደ ነው። ችግሩን ከመካፈል ይልቅ አጋጣሚውን ርግማንና ቁጣ አድርጎ ማሳቀቅን ልምድ አድርጓል።

ይህ ዓይነቱ እውነት ሁሌም ለእናት ሰላም የየዕለት ሀዘንና ቁጭትን ፈጥሯል። መልስ ባታገኝም ለምን ስትል ራሷን ትጠይቃለች። ሰላም ሁሌም እነዚህንና ሌሎች ህጻናትን በበጎ ፈቃደኝነት ለማገዝ፣ ለማገልገል ልቧ ይፈቅዳል። ልክ እንደ እሷ ሁሉ የመንግሥት አካላትና፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው ሁሉ ትኩረት እንዲሰጡት ምኞቷ ነው።

በድርጅቱ ሸክማቸው ከከበዳቸው፣ ኑሮና ሕይወት ከፈተናቸው ቤተሰቦች ጎን ቆመው ‹‹አለናችሁ›› የሚሉ አጋሮች በርካታ ናቸው። እነሱ የብዙኃን እናቶችና ልጆቻቸው ድምጽ ጎልቶ ይሰማቸዋል። ባገኙት ዕድልና አጋጣሚ ሁሉ ቀኝ እጅ ለመሆን ወደ ኋላን አያውቁም። የእነሱ ክፍያና ጥቅም የሰዎችን ዕንባ ማበስ፣ የተቸገሩትን ጎን መዳበስ ነው። ዘወትር በጎደለው ሁሉ ተገኝተው ባዶውን ይሞላሉ። ሸንቁሩን ይደፍናሉ።

**ዓይናማ ልቦች ...**

አቶ እስክንድር ላቀው የሆፕ ኤስ ቢ ኤች /Hop SPH/ የክብር አምባሳደር ናቸው። አቶ እስክንድር በእነዚህ ቤተሰቦችና ልጆቻቸው መካከል መገኘታቸውን እንደ ታላቅ ዕድል ይቆጥሩታል። እንደ እሳቸው እሳቤ ድርጅቱ የተስፋ ማሳያ እንደመሆኑ ሕይወትን አለምልሞ ያቆያል። ትዕግስትና ጥረት ደግሞ ኑሮን ታግሎ የማሸነፊያ መንገዶች ናቸው። የሰው ልጅ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ ብዙ ውጥኖቹ ይበላሻሉ። ማሸነፍና መሸነፍ ደግሞ ከማንነት ይመነጫል። አንድ ሰው ውስጡን ካሸነፈ በሁኔታዎች ሁሉ አሸናፊ ነው። በተቃራኒው ውስጡ ለሸንፈና እጅ ለሰጠም ተስፋ፣ ኑሮና ሕይወት ይሏቸው እውነታዎች እንደታሰቡት አይሰምሩም።

አቶ እስክንድር እነዚህን ሀቆች መሠረት ማድረግ የውስጥ ስኬትን ለማስመር እንደሚያግዝ ያምናሉ። ይህ እምነታቸውም ከድርጅቱ ጎን እንዲቆሙና በርካቶችን ‹‹አይዟችሁ›› ብለው እንዲያበረቱ አግዟቸዋል። አንዳንዴ ሰዎች ከፍ ያለ ሀዘን ሲያገኛቸው ክፉኛ ይሰበራሉ የሚሉት እስክንድር እንደ ወይዘሮ ቤዛ ያሉ ጠንካሮች ደግሞ ስብራቱ ሳይብስባቸው ራሳቸውን ጠግነው ለሌሎች ጭምር ወጌሻ መሆናቸው እንደሚያበረታ ርግጠኛ አድርጓቸዋል።

የክብር አምባሳደሩ ድርጅቱን በእግሩ ለማቆም፣ ዕውቀት፤ ጊዜያቸውን ላዋጡ፣ ጉልበት አቅማቸውን ለከፈሉ ሁሉ ምስጋናን ችረዋል። እሳቸውም እንደ ክብር አምባሳደርነታቸው ለልጆቹና ለወላጆቻቸው ጉዳይ በየትኛውም መድረክና አጋጣሚ ሁሉ ድምጽ ለመሆን ቃል ገብተዋል። በዕለቱም አቶ እስክንድር የእናት ማህሌትን ችግር በመረዳት ለልጇ መማሪያ ቁሳቁሶች ለማበርከት መዘጋጀታቸውንና እገዛው ለሌሎችም ጭምር እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ለአንድ ዓላማ ለተመሳሳይ ተግባርና ግብ በአንድ ሥፍራ የታደሙ ወገኖች በሚተያዩ፣ በሚናበቡ ልቦቻቸው በወጉ ይግባባሉ። የትናንቱ የሕይወት መንገዳቸው ለዛሬ አሻግሮ ሲያሳድራቸው በተደላደለ መንገድ አልፈው አይደለም። ነገ የልጆቻቸው ዓለም የተሻለ ይሆን ዘንድ ትግላቸው እንዲህ ቀጥሏል። ብርቱዎቹ፣ ጠንካራዎቹ ወላጆች።

# መሠረተ ልማት

## የከተማዋን የካዳስተር ምዝገባ ሥርዓት ወደ ሙሉ ትግበራ የሚያሸጋግረው የመጨረሻው ምዝገባ

**በኃይሉ አበራ**

በሀገሪቱ የትኛው አካባቢ ለየትኛው ተግባር መዋል እንዳለበት የሚያሳይ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እንደሌለ ይገለጻል። በከተሞች ኢንዱስትሪው፣ መኖሪያ መንደሩ፣ የንግድ ማዕከሉ፣ ሆቴሉ ወዘተ. ተቀይጦ ከኖረበት ሁኔታም መረዳት የሚቻለው ይህንኑ ነው። የከተማ ልማት ባለሙያዎች ይህን ዓይነቱ የመሬት አስተዳደር ትክክል እንዳልሆነ ሲያገነዝቡ ኖረዋል፤ የአንድ ከተማ መሬት ለመኖሪያ ቤት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለንግድ፣ ለአረንጓዴ ስፍራ፣ ወዘተ በሚል ተለይቶ መተዳደር እንዳለበት ያሳስባሉ። ይህ ብቻም አይደለም የከተማ መሬት በሚገባ ተመዝግቦ ባለቤት ኖሮት ሊቀመጥ እንደሚገባም ይገልጻሉ።

በኢትዮጵያ በከተሞች ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚታየውን ስር የሰደደ ችግር ለመፍታትም ሆነ ዜጎችም ከተሞችም ሀገሪቱን ከመሬት ተገቢውን ጥቅም ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ የመሬት ምዝገባው ለማዘመን የተለያዩ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እስካሁን ከ670 ሺህ በላይ ማኅደሮች ዲጂታላይዝ ተደርገዋል። እነዚህ መረጃዎች በ11 ክፍለ ከተሞች ተለይተው ወደ አንድ ቋት ገብተዋል። በመረጃ ቋት ውስጥ የገባ መረጃ ማንም ሊያጠፋው ሊሰርዘው ሊደልዘው አይችልም።

በመዲናዋ በስፓሻል ዳታም የመሬት ባንክ፣ የካሣና የመሬት ዝግጅት መረጃዎች አንድ ላይ ተደራጅተው እንዲቀመጡ ተደርጓል። ይህም የመዲናዋ ክፍት ቦታዎች ለሚፈለገው ዓላማ እንዲውሉ እያስቻለ ነው። ይህ ሁኔታ የከተማዋ ክፍት ቦታዎች "ለምን ለምን አገልግሎት ይውላሉ?" የሚሉትን መረጃዎች በመጠቀም በቀላሉ ለሚፈለገው ዓላማ እንዲውሉ የጎላ እገዛ ያደርጋል። የትኛውም አካባቢ ያለ መሬት ባለቤት ካለው ለመሬት ወረራ እና መሰል ችግሮች መጋለጡ ይቀራል።

መንግሥት በዋናነት እያደረገ ያለው ቦታውን ማወቅ ባለቤትነትን ማስከበር ነው። ደኖች፣ የወንዝ ዳርቻዎች ወዘተ በሙሉ ለመሬት ወረራ ተጋልጠው ቆይተዋል። ከእነዚህ ቦታዎች መካከል ለልማት የሚሆኑትን በማልማት፣ ለልማት የማይበቁትን የመንግሥት እንደሆኑ ለማድረግ ተለክተው መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚቀመጡበት ሥርዓት መዘርጋቱን መረጃው ያመላክታል።

መሬት ውስንና ውድ የሕዝብ ሀብት ነው። ይህን ሀብት በሚገባ ለማስተዳደርና ከሀብቱ ተጠቃሚ ለመሆን በቅድሚያ ዘመኑን የሚመጥን የመሬት ምዝገባ ማካሄድ/ሕጋዊ የካዳስተር ሥርዓት መዘርጋት/ወሳኝ ነው። በመሬት ማስተዳደር በኩል ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የታመነበት ይህ የካዳስተር ሥርዓት ምዝገባ በተለያየ ደረጃ ላይ ቢገኝም በተለያዩ ከተሞች ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፤ እየተደረገም ነው። እንደ አዳማና ቢሾፍቱ ባሉት ከተሞች ይህን ሥርዓት በመዘርጋት ለውጥ ማምጣት እንደተቻለም መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ካዳስተር በከተሞች ከመሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል። ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ተቋማት ድረስ ያለውን የመሬት ይዞታ ባለቤትነት የማረጋገጥ ሥራ በመሥራት ከመሬት ጋር ተያይዞ በዜጎች ላይ ሲፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን በዘላቂነት ይፈታል። መሬቱ የመንገዶች ባለሥልጣን ከሆነም የመንገድ መሬት የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ለተቋሙ ይሰጠዋል፤ ይህም ከወሰን ማስከበርና ከመሳሰሉት ጋር ያሉ ችግሮችን ይፈታል፤ በዚህ ይዞታ ላይ ምንም አይነት ሌላ ግንባታ እንዳይካሄድ ለማድረግ ይጠቅማል።

በአዲስ አበባ ከተማም ይህ የምዝገባ ሥርዓት በየዓመቱ ለሰባት ዓመታት ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህ ዓመት ስምንተኛው የካዳስተር ምዝገባን ማካሄድ የሚያስችል እወጃ ሰሞኑን በይፋ ተደርጓል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ይህን የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ እወጃን አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥቷል።

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፋወሰን ዴሲሳ በመግለጫው ላይ እንዳስገነዘቡት፤ በከተሞች ከመሬት ይዞታ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት የሕጋዊ ካዳስተር ግንባታ ሥርዓት ዋነኛ መሣሪያ ነው። የከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ይህንን ዘመናዊ ሁለገብ ካዳስተር ግንባታ ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2022 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል። ኤጀንሲው የይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ ከጀመረበት 2007 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2016 በጀት ዓመት ድረስ ሰባት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጥ እወጃ በማካሄድ በ337 ቀጣናዎች ላይ የማረጋገጥ ሥራ አካሂዷል።



አቶ ግፋወሰን ዴሲሳ

በዚህም በቁራሽ መሬት 219 ሺህ 722፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች 173 ሺህ 136 መብት በአጠቃላይ 400 ሺህ 84 ይዞታዎች ላይ የይዞታ ማረጋገጥ ሥራ መሠራቱን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ በዚህም ሥራ በመብት ደረጃ 80 በመቶውን የሠራ ሲሆን፣ የሚቀረው 20 በመቶ መሆኑን፣ በዚህ ሥራ ከአዲስ አበባ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 54 በመቶውን መሸፈን መቻሉን አስታውቀዋል።

ኤጀንሲው በተያዘው በጀት ዓመት ለመጨረሻ ጊዜ ለስምንተኛ ዙር ቀሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉት ባልተረጋገጡ 136 ቀጣናዎች የሚገኙ ቁራሽ መሬቶችን ለመመዝገብ ዝግጅቱን ማጠናቀቁን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ኤጀንሲው በዚህ ላይ ታኅሣሥ 10 ቀን 2017 ዓ.ም እወጃ አካሂዷል። የይዞታ ማረጋገጡ ሥራም በተመረጡ ስድስት ክፍለ ከተሞች የሚከናወን ነው። ከእነዚህ ስድስት ክፍለ ከተማዎች በዝርዝር ሲታይ በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት፣ ሦስት፣ ዘጠኝ፣ 10፣ 11 እና 12 በ25 ቀጣናዎች ይከናወናል። በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት፤ ሶስት፤ አምስት፤ ዘጠኝ 10 እና 13 በ44 ቀጣናዎች የማረጋገጥ ሥራው ይካሄዳል።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 12፣ ሦስት፣ ስድስት፣ ዘጠኝ፣ እና ወረዳ 13 በሚገኙ 19 ቀጣናዎች ይከናወናል። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በወረዳ ስድስት፤ ሰባት፤ 10፤ 11 እና 14 የሚገኙ በ22 ቀጣናዎች የሚከናወን ነው። በቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሦስት፣ 12 እና 13 በ15 ቀጣናዎች እንዲሁም በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሦስት በሚገኙ 11 ቀጣናዎች የሚካሄዱ መሆኑን አስታውቀዋል። በእነዚህ ስድስት ክፍለ ከተሞች በሚገኙ አጠቃላይ በ136 ቀጠናዎች፣ 467 ሰፈሮች ያልተረጋገጡ ይዞታዎችን የማረጋገጡ ሥራ በስልታዊ ዘዴ ወይም በመደዳ የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ሥራውም ከታኅሣሥ 15 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አምስት ወራት ውስጥ እስከ ሚያዝያ 15 ቀን 2017 ዓ.ም ጠቅሰው፣ ሙሉ ወጪውም በመንግሥት የሚሸፈን መሆኑን በመግለጫው ጠቁመዋል።

ኤጀንሲው ከዚህም ጋር ተያይዞ ለይዞታ ማረጋገጥ በተመረጡ ቀጣናዎችና ሰፈሮች የሚገኙ ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጥ እወጃው ከተላለፈ በኋላ የይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄያቸውን ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚያወጡት ፕሮግራም መሠረት ቀርበው እንዲያመለክቱ ጥሪ አስተላልፏል። አመልካቾች ለይዞታ ማረጋገጥ የተመረጡ ቀጣናዎችንና ሰፈሮችን ዝርዝር መረጃ በየክፍለ ከተማው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እንደሚያገኙም አስታውቀዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ ለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ በተመረጡ ቀጣናዎችና ሰፈሮች ውስጥ ብቻ ሥራው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ባለው አምስት ወራት ውስጥ የመረጃ ልዩነት እንዳይፈጠር ሲባል ምንም ዓይነት የስመ-ንብረት ዝውውር እንዲቆም መደረጉንም አሳስበዋል። የይዞታ ማረጋገጥ ሥራው በሚከናወንባቸው ቀጣናዎችና ሰፈሮች ውስጥ ያሉ ባለይዞታዎችም ኤጀንሲው አረጋግጦ ላልመዘገበው ይዞታ ሕጋዊ ዋስትናና ከለላ የማይሰጥ መሆኑን በዚህ ወቅት ተናግረዋል። በመሆኑም አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ከታኅሣሥ 20 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አሥር የሥራ ቀናት በክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ የይዞታ ይረጋገጥልኝ ማመልከቻ እንዲያቀርቡም ጥሪ አስተላልፈዋል።

አቶ ግፋወሰን ከመገናኛ ብዙኃን ለቀረቡላቸው ጥያቄዎችም ምላሽ እንዳብራሩትም፤ ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው የሚመዘግበው ሕጋዊ ካዳስተር ባለመብቱ ያለውን የመብት ክልከላ እና ኃላፊነት ነው። ባለመብቱ ሲባልም ለምሳሌ መንገዶች ሰፍተው ከሆነ መንገዶች ባለመብት ነው። እያንዳንዱ መንገድ ላይ የሕጋዊ ካዳስተር ምዝገባ ሥራ ይከናወናል። ስለዚህ ከሰፋ የመንገዱ መብት ክልከላ ኃላፊነትን በኤጀንሲው በኩል የመመዝገብ ሥራ ይከናወናል ማለት ነው። አዳዲስ የማዘመን ሥራዎችም ሲመጡ በተመሳሳይ አሠራር ላይ አፕዴት የሚደረጉ መሆኑን ታሳቢ ሊደረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሳተላይት መረጃ /ኢሜጅ/ የሚጠቀመው መቼ ነው በሚል ለቀረበው ጥያቄም ምላሽ ሰጥተዋል፤ የከተማ አስተዳደሩ በ2003 ዓ.ም በጀርመን ኩባንያ አማካይነት በመዲናዋ የአየር በረራ በማድረግ የአየር ፎቶግራፍ ካስነሳ በኋላ የመስመር ካርታዎችን በ2003 ለከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሠረታዊ ካርታ ሆኖ እንዲያገለግል መሠራቱን አስታውሰዋል። ከዚያ ወዲህም ማሻሻያዎች መደረጋቸውን ጠቅሰዋል። የ2014ቱን ወቅታዊ ለማድረግም አሁን እየተሠራበት መሆኑን አመልክተው፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከሳተላይት ምስል ጋር ከተያያዘው ይልቅ የበለጠ ግልፅነት ባለው የመሬት ሰርቬይ እየተሠራበት መሆኑን አመላክተዋል።

እንደ አቶ ግፋወሰን ማብራሪያ፤ የከተማ መሬት በጣም ውስን ከመሆኑ የተነሳ የተረጋገጠ ሥራ ይፈልጋል። የሳተላይት መረጃ /ኢሜጅ/ን በመጠቀም ሲሠራ ሰፊ በሆነ እና የእርሻ መሬት አካባቢ በሚገኝ መሬት ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። በመሆኑም እርገጠኛነትን /ፕሪሲሽን/ በማይፈልጉ ቦታዎች የመሬት ሰርቬይ ጥቅም ላይ እንዲል የሚያስችሉ መሣሪያዎች አሉ።

እንደ ዲፈሬንሻል ጂፒኤስ ያሉ መሣሪያዎችም አሉ። አዲስ አበባ ዓለም እየተጠቀመበት ያለውን እንደ "ኮርስ ስቴሽን" ያለውን የቅየሳ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ እንደምትጠቀም ገልጸዋል። ይህ መሣሪያ ዘንድሮ እንደሚተከልም ጠቁመዋል። በዚህም ምክንያት በከተማዋ የሳተላይት ኢሜጆችን የመጠቀሙ ዕድል ከፍተኛ ይሆናል ብለዋል።

አቶ ግፋወሰን እንዳስረዱት፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ2022 ሁለገብ ካዳስተር ይገነባል። ይህ ሲባል እነዚህ የሚገነቡ ሁለገብ የካዳስተር ሥራዎችን እንደ አነባበሮ በማድረግ ሲወሰዱ ሦስት ንብርብሮች ይኖራሉ። የመጀመሪያው ንብርብር ሕጋዊ ካዳስተር ነው። ከተማው ውስጥ ያለው መብት ክልከላና ኃላፊነትን እንዲሁም ምድረ ገፃዊ ካርታ መረጃው ይሰበሰባል።

ከዚህ በመቀጠልም ፊዚካል ካዳስተር የሚባል አለ፤ ጣራና ግድግዳ፣ ንብረት ግመታ እና የመሬት ግመታን የሚያካትት ሁለተኛ ንብርብር አለ። በሦስተኛ ንብርብርነት የሚያዘው የመሠረተ ልማት ካዳስተር ነው። በመሆኑም ከአምስት ዓመት በኋላ የሚደረስበት ሁለገብ ካዳስተር እንጂ ሕጋዊ ካዳስተር አይደለም። አሁን የተጠናቀቀው ያለው ሕጋዊ ካዳስተር ነው፤ በየደረጃው የሚጠናቀቅ ስለሆነ በዚህ ልክ መያዝ ይገባል።

የዘንድሮው የካዳስተር ምዝገባ ለመጨረሻ ጊዜ ሲባልም የከተማውን መረጃ፣ የመብት መረጃ፣ ፊዚካል መረጃ ሙሉ ለሙሉ ዘንድሮ እንደሚሸፈን አስታውቀዋል። የካዳስተር ምዝገባው ከመሬት ሊዝና ሕገ ወጥነት ጋር ተያይዞ ሕጋዊ ካዳስተር ሀብታችንን ቆጥረን የምናውቅበት ሥርዓት ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ምን መሬት አለ? ማን ምን ያህል ይዟል? መብት ክልከላና ኃላፊነቱ ምንድነው? በሚል የማረጋገጡ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ለዜጎች በይዞታቸው ላይ ዋስትና የሚሰጥበት ሥርዓት ነው።

ተቋሙ ከቅድመ ምዝገባ በኋላ በ24 የተለያዩ ርዕሶች አገልግሎት የሚሰጥበት ራሱን የቻለ አሠራር እንዳለው ዋና ዳይሬክተሩ አመላክተዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በዚያም አገልግሎት ይሰጣል፤ አገልግሎት ከሚሰጥበት አሠራር ውጪ ገቢ ያመነጫል ማለት ነው። በዚህ በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘለትን ወደ 10 ቢሊዮን ብር አካባቢ ከአገልግሎት የሚገኝ ገቢ ይሰበሰባል። የማረጋገጥ ሥራውን በመሥራት፣ ምዝገባ በማከናወን፣ አገልግሎት በመስጠት ገቢ የሚገኝበት ሥርዓት መከናወኑን አስረድተዋል።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች- በ2024 የመካከለኛና ረጅም ርቀት ውድድሮች

ብርሃን ፈይሳ

ለመጠናቀቅ ቀናት ብቻ በቀሩት የፈረንጆች ዓመት 2024 ኦሊምፒክን ጨምሮ በአትሌቲክስ ስፖርት በርካታ ቻምፒዮናዎች ተከናውነዋል። ይህንንም ተከትሎ የዓለም አትሌቲክስ በዓመቱ በተለያዩ ርቀቶች እንዲሁም በሜዳ ተግባራት የተመዘገቡ ውጤቶችን በማወዳደር ደረጃ አውጥቷል። ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም በዓመቱ በተካፈሉባቸው ውድድሮች ያገኙትን ውጤትና ያስመዘገቡትን ነጥብ መሰረት ያደረገ ደረጃቸው ተቀምጧል። በዚህም በተለይ በመካከለኛና ረጅም ርቀቶች አሁንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቀዳሚዎቹ መካከል እንዲገኙ አስችሏቸዋል።

በመካከለኛና ረጅም ከ800 ሜትር እስከ 10ሺ ሜትር ባሉት ርቀቶች የዓመቱ የመጀመሪያ ውድድር ከነበረው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና እስከ ፓሪስ ኦሊምፒክ ያሉትን በዳሰሰ መልኩ ደረጃው ተቀምጧል። በ800 ሜትር ሴቶች ዓመቱ ሲከለስ አትሌቶች በሰበሰቧቸው ነጥቦች መሰረት ኢትዮጵያዊቷ ወጣት አትሌት ጽጌ ድጉማ ከዓለም ሶስተኛ ደረጃ ላይ ልትቀመጥ ችላለች።

በኦሊምፒክ በአንድ ሰከንድ ብቻ በመቀደሟ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀችው አትሌት ፅጌ፣ ግላስኮ ላይ በተካሄደው የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ደግሞ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ የሆነ ድል ማስመዝገቧ አይዘነጋም። ከሳምንታት በኋላም በአፍሪካ ጨዋታዎች ቻምፒዮን ነበረች። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ውድድሮች የሰበሰበችው 1ሺ383 ነጥብ በመሆኑ እንግሊዛዊቷን ኬሊ ሆድኪንሰን እና ኬንያዊያን ሜሪ ሞራን ተከትላ በዓለም አትሌቲክስ ደረጃ ሶስተኛ ላይ ልትቀመጥ ችላለች።

በመካከለኛ ርቀት ወንድ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሳትፎ የሌላቸው መሆኑን ተከትሎ በደረጃው አልተካተቱም። በሴቶች 1ሺ500 ሜትር ሴቶች ግን በርካታ አትሌቶች ስኬታማ የሚባል ጊዜን አሳልፈዋል። በዓመቱ በርቀቱ በተመዘገበው ሰዓት መሰረት ከዓለም ክብረወሰን በአንድ ሰከንድ ብቻ የዘገየችው አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ሁለተኛዋ ፈጣን አትሌት ናት። በአጠቃላይ በዓመቱ በተሰበሰበ ነጥብ ግን ድርቤ ወልተጂ እና ፍሬወይኒ ኃይሉ ናቸው 3ኛ እና 4ኛ ደረጃን የያዙት።

በኦሊምፒክ እና ዳይመንድ ሊግ አሸናፊ በመሆን እንዲሁም በርቀቱ ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ በአጠቃላይ የርቀቱን የበላይነቱን የያዘችው ኬንያዊቷ አትሌት ፌይዝ ኪፕዬጎን ናት። በውድድር ዓመቱ መጀመሪያ የቤት ውስጥ ቻምፒዮን በመሆን በድል የጀመረችው ፍሬወይኒ በበኩሏ፤ የዚመን እና ዶሃን ጨምሮ በዳይመድ ሊጉ ስኬታማ ተሳትፎ ስታደርግ ብትቆይም በፓሪስ ኦሊምፒክ አለመሳተፏ በሰበሰበቻቸው ነጥቦች ላይ ተጽእኖ አድርጎባታል።

በ5ሺ ሜትርም በተመሳሳይ ፍሬወይኒ ባስመዘገበችው ሰዓት ከሀገሯ ልጆች ጽጌ ገብረሰላማ፣ እጅጋየሁ ታዬ እና መዲና ኢሳ ጋር በሰንጠረዡ አናት ልትቀመጥ ችላለች። በዓለም አትሌቲክስ አዘጋጅነት በተካሄዱ ቻምፒዮናዎች ላይ ውጤታማ ባይሆኑም በዳይመንድ ሊግና ሌሎች ውድድሮች በነበራቸው ብቃት በዓመቱ ቀዳሚ ከሆኑ 10 አትሌቶች መካከል 7ቱ ኢትዮጵያዊያን ሊሆኑ ችለዋል። በ10ሺ ሜትርም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተሳትፎ እየተዳከመ በመምጣቱ በደረጃ ሰንጠረዡ በብቸኝነት የተካተተችው አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ብቻ ሆናለች።



የኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ አሸናፊው በሪሁ አረጋዊ በ2024 የ10ሺ ሜትር ውድድር ከዓለም 2ኛ ደረጃን አግኝቷል፤

ኢትዮጵያ በወንዶች ተጽእኖ ፈጣሪ በነበረችባቸው የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀት የሚመዘገበው ሜዳሊያ ቁጥር ቢያሽቆለቁልም በዓመቱ በተለያዩ ውድድሮች የነበረው ተሳትፎ ድምር ውጤት ግን የተሻለ የሚባል ነው። በ5ሺ ሜትር በታሪክ ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበው ሃጎስ ገብረህይወት ቀዳሚው ሲሆን፤ ዮሚፍ ቀጄልቻ በሁለት ሰከንድ ዘግይቶ ይከተለዋል። በአጠቃላይ ነጥብም ሃጎስ ኖርዌያዊውን ተፎካካሪውን ጃኮብ ኢንግብሪስተን በማስከተል የበላይነቱን ይዟል። የዳይመንድ ሊግ አሸናፊው በሪሁ አረጋዊ፣ ዮሚፍ እና ሰለሞን ባረጋ ደግሞ በቀጣዮቹ ደረጃዎች ላይ ተቀምጠዋል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በ10ሺ ሜትር የፓሪስ ኦሊምፒክ የሰዓት ማሟያ ውድድር ባስመዘገቡት ሰዓት ከአንድ እስከ አምስት ያሉትን ደረጃዎች ይዘዋል። ይሁንና በኦሊምፒኩ ከአትሌት በሪሁ አረጋዊ የብር ሜዳሊያ ባሻገር በርቀቱ ውጤት አልተመዘገበም። በዚህ ርቀት ኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮና በቀር ውድድሮች ባለመኖራቸው ምክንያትም በፓሪስ ኦሊምፒክ የተገኘው የዓመቱን የአትሌቶች ደረጃ ሊለይ ችሏል። በዚህም የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀው ዩጋንዳዊው ጆሹዋ ቺፕቴጊ በሪሁንን በማስከተል በመሪነት ላይ ተቀምጠዋል። ዮሚፍ ቀጄልቻ ደግሞ አምስተኛው አትሌት ነው።


## የስም ማስታወቂያ

የሀዲያ ዞን ሙስሊም ወጣቶች በጎ አድራጎት ኢስላማዊ ማህበር የተባለው ሀገር በቀል ኢስላማዊ ማህበር ተቋም ሆኖ ለመመዝገብ ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት የምዝገባ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ከ19/04/2017 እስከ 24/04/2017 ድረስ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት ይቅረብ፡፡

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ከተማው ጌትነት ማዘንጊያ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C26121 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር MBHCZC63S00A49266 የሞተር ቁጥር K12MP1414960 ሞዴል CZC635 የሊብሬ ቁጥር 441188 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2017 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- ፍሬት ኢን ታይም ሎጂስቲክስ ኃላ/የተ/የግ/ማ /,<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ/3h, ቦሌ, አዲስ አበባ /ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/17865/2017<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 02/03/2017 E.C | | |
| 3 | ምልክት፡- FIT | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- (image of globe) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምደብ፡- 39 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | አስተላላፊነት, መርከብ ስራ, ውክልና ፣እና የወደብ ስራዎች (ምድብ 39) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረትባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIV No-109 19/04/2017 (28/12/2024)**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## ጨረታ ቁጥር 001/2017

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በምዕ/ሐረርጌ ዞን የጨርጨር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ 2017 በጀት አመት ለየተለያዩ ት/ክፍሎች የሚውሉ ቋሚና አላቂ የቴክኒክና ሙያ የስልጠና እቃዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ የሚከተለዉን መስፈርት የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. እቃውን በጥራት ለማቅራብ የሚያስችል ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ፡፡
2. ተጫራቾች የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT)ተመዝጋቢዎች ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅርብ ይኖርባቸዋል::
3. ተጫራቾች በአቅራቢዎች/በመስኩ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ መሆን አለባቸው::
4. አቅራቢዎች ከአስመጪው ድርጅት ሰርተፍኬት (ጋራንቲ) ማቅረብ አለባቸው ::
5. የጨረታ ማስከበሪያ 20000(ሃያ ሺህ) ብር በባንክ በተረጋገጠ (CPO) ወይም በጥሬ ገንዘብ ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማስያዝ አለባቸው ::
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 500(አምስት መቶ) በመክፈል ከላይ በተገለጸው የጽ/ቤቱ አድራሻ (ጭሮ ወይም አሰበ ተፈሪ ከተማ በኮሌጁ ፋይናንስ ቢሮ) በመቅረብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት መግዛት ይቻላል ::
7. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት እስከ 6/5/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ለተጫራቾች ክፍት ይሆናል ::
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚጫረቱበትን መወዳደሪያ የ አንዱን ዋጋ በመጥቀስ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ አድርጎ እስከ 6/5/2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ድረስ በጭሮ ከተማ በኮሌጁ ፋይናንስ ቢሮ ገቢ ማድረግ አለባቸው:: ጨረታው በዚሁ 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
9. አሸናፊው የጨረታ ተወዳዳሪ ማሸነፉ ከተገለጸበት በኋላ በአስር (10) ቀናቶች ውስጥ ከግዢው ጠቅላላ ዋጋ ላይ 10% የውል ማስከበሪያ ማስያዝ አለበት፡፡
10. ለጨረታ ከቀረቡ ዕቃዎች ዝርዝር ዉስጥ ኮሌጁ እስከ 20% ለመጨመር ወይም ለመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው ::
11. ተወዳዳሪዎች በጨረታው ሰነድ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተምና ፊርማቸውን ማኖር አለባቸው ::
12. ኮሌጁ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻችን፡- በም/ሐረ ዞን ጨርጨር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ**
**ጭሮ አሰበ ተፈሪ**
**0255511349/0944141498**
**ጨርጨር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ**
**ጭሮ አሰበ ተፈሪ**

**የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በምዕ/ሐረርጌ ዞን የጨርጨር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ**